በወቅቱ መስተዳድሩን በመወከል ፕሮጀክቱን ይከታተል የነበረው የትግራይ ምክትል አስተዳደሪ ጸጋይ በርሄ በጉዳዩ ሳይገፋበት ከስብሰባው ወጥቷል። ሆኖም የገንዘብ አያያዝና አወጣጥን በተመለከተ የነበረው ችግር ተነሥቶ ክትትል እንዲደረግና የደረሰበት ደረጃ እንዲታወቅ ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር። ግለሰቦች ስለፈጸሙት ሙስና ከዚያ በኋላ የተባለና የተሰማ ነገር ባይኖርም በተቋም ደረጃ የተፈጠረ ብክነት ግን ተስተውሏል። ለምሳሌ ብዙ ሚልዩን ብር ወጪ ተደርጎበት ከዴንማርክ የተገዛው እጅግ ግዙፍና ዘመናዊ የጭቃ ብሎኬት ማምረቻ መሣሪያ በዳንሻ ሁለት ሺሕ ያህል ቤቶችን ለመሥራት ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ሥራ ላይ ሊውል ስላልቻለ ተጨማሪ የጭቃ ቤቶች እንዲሠሩበት ተወስኖ መቀሌ ላይ የተወሰኑ የቁጠባ ቤቶች ሲሠሩበት ዓድዋ ላይ ደግሞ አልመዳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ውስጥ ተሰማርተው ለነበሩት ታጋዮች ቤት ለመሥራት አገልግሏል። ከዚህ በኋላ በዚህ ግዙፍ መሣሪያ የሚሠሩ ተጨማሪ ቤቶች ስላልነበሩ መሣሪያው ባለቤት አጥቶ ለዓመታት መቀሌ ላይ ተጥሎ ሥራ ላይ ሳይውል መቆየቱ ይታወቃል።

የመልሶ ማቋቋሙ ሥራ ከአገር ውስጥ ግምጃ ቤት በሚገኝ ገንዘብም እየተኪያሄደ በየዞኖችና በየወረዳዎች ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ተቋማት፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሌሎች መሠረተ ልማቶችም ይገነቡ ነበር። ለዚህ የሚመደበው ገንዘብ በቂ ስላልነበር የሕዝቡ የገንዘብ፣ የጉልበትና የቁሳቁስ አስተዋፅኦ ታክሎበት ውጤታማ ሊሆን ችሏል። በወቅቱ በበጎ ፈቃድ ወደ ክልሉ የተሰማሩ የመንግሥት ሠራተኞች ፈራርሶ የነበረውን የመንግሥት መዋቅር ለምሳሌ የትምህርት፣ የጤና፣ የመጓጓዣ፣ የንግድ፣ የፋይናንስ፣ ወዘተ... ቢሮዎች ዳግም በማቋቋም ሥራ አስጀምሯል። ይህ የሕዝብና የመንግሥት ሠራተኞች እንቅስቃሴ የመልሶ ማቋቋሙን መርሐ ግብር በስኬት እንዲፈጸም አስተዋፅኦ አድርጓል። የክልሉ አመራርም ሕዝቡን በማስተባበርና የተገኘውን ውሱን በጀት አብቃቅቶ ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ አመርቂ ተግባር ፈጽሟል።

6. የርዕዮተ ዓለም ውሸንብር "በህወሓት/ኢሕአዴግ

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደሞከርኩት ህወሓት/ኢሕአዴግ ደርግን አቸንፎ ሥልጣን በተቆጣጠረበት ወቅት መንግሥት ለመምራት የሚያስችለውን ተገቢ ዝግጅት አላደረገም ነበር። የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ከምዕራቡ የሊበራል አስተሳሰብ ጋራ ተዳቅለው እንዲቀጥሉ ለማድረግ ሲሞክር በድርጅቱ ውሸንብር ተፈጥሮ ይህን ለማስተካከል በ1985 ዓ.ም· እና በ1986 ዓ.ም· መላውን ካድሬ በዙር ያሳተፈ ሰፊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ተኪያሄደ።

ደርግ ቀድሞ ወታደሮቹን ያሠለጥንበት የነበረው የታጠቅ ጦር ሰፈር ወደ ካድሬ ትምህርት ቤት ተለውጠ በርካታ ነባርና አዲስ ካድሬዎችን ማሠልጠኑን ተያያዝነው። የሥልጠናው ትኩረት አብዮታዊ ዴሞክራሲና ርዕዮተ ዓለሙን ሊፈታተኑ የሚችሉ ተግዳሮቶች ላይ ነበር። በዚህ ሥልጠና ከፍተኛው ተግዳሮት ኢምፔሪያሊዝም በኢኮኖሚ እንቅስቃሴያችን ላይ ሊያሳድረው የሚችለው ተጽዕኖ እንደሆነ እንገለጽ ነበር። ኢምፔሪያሊዝም የኢሕአዴግን የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ተግባራዊ እንዳይሆኑ ሊያደርግ እንደሚችልና ይህን ፈተና ለመወጣት ዝግጁ መሆን እንዳለብን በአጽንዖት እንናገር ነበር። ለካድሬው የሚሰጠው ትምህርት ይህ ይሁን እንጂ የኢምፔሪያሊስት ተቋማት ከሚባሉት ዓለም ዐቀፍ የገንዘብ ድርጅትና ከዓለም ባንክ ጋራ አብረን ለመሥራት በመንግሥት ደረጃ ተስማምተን ነበር። ለዚሁም በየደረጃው ተግባራዊ የሚሆኑ የካፒታሊስት ሥርዓቱን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያዎች መቀበል የግድ ይል ነበር። እነዚህ ተቋማት ኢሕአዴግ በኢኮኖሚው ዘርፍ መዋቅራዊ ማሻሻያዎችን እንዲያደርግ አስገዳጅ መመሪያ ሲሰጡንም ያለ ምንም ማንገራገር ተቀብለነው ነበር። ከመመሪያዎቹ መካከልም፤ ሀ/ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የነበሩትን የንግድና የኢንዱስትሪ

ተቋማት ወደ ግል ማዘዋወር *(privatization)*፣ ለ/ ለመንግሥት ብቻ ተከልለው በነበሩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የግል ባለሀብቶች እንዲሳተፉ ማድረግ *(liberalization)*፣ ሐ/ ያለፈው መንግሥት ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠር አውጥቷቸው የነበሩትን መመሪያዎች ማሻሻል *(deregulation)* ይገኙበታል።

እነዚህ በውጭ ተጽዕኖ የመጡብን የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሐ ግብሮች እንከተለዋለን ከምንለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋር ይጻረሩ ስለነበር ውዥንብር ማንሣታቸው አልቀረም። በመሆኑም በካድሬው ትምህርት ቤት ድርጅታዊ ፕሮግራማችንን ሳናዛንፍ ማሻሻያዎቹን ልንተገብራቸው እንደምንችል ማስረዳት ነበረብን። አብዮታዊ ዴሞክራሲ መንግሥት ገዢ የኢኮኖሚ ተቋሞችን መቆጣጠር አለበት ይላል፤ ዓለም ዐቀፍ የገንዘብ ድርጅትና ዓለም ባንክ ደግሞ መንግሥት ወሳኝ የኢኮኖሚ ተቋሞችን መቆጣጠር የለበትም እንዲያውም መንግሥት ከምርትና ከንግድ ተቋሞች እጁን አስወጥቶ መድረኩን ለግል ባለሀብቱ ክፍት ማድረግ አለበት ይላሉ። ኢሕአዴግ የፕራይቬታይዜሽንንና የሊበራላይዜሽንን ፖሊሲ የተቀበለውም መንግሥት በኢኮኖሚው ያለውን ሚና በመገደብ ለባለ ሀብቱ በቂ የኢኮኖሚ ምኅዳር ለመስጠት ነው። ታድያ ይህ አኪያሄድ የፕሮግራማችንን ምሰሶ አይንድም ወይ? ለሚለው ጥያቄም ከዓለም የገንዘብ ድርጅትና ከዓለም ባንክ የምናገኘው ጥቅም እንዳይጓደልና ከነዚህ ተቋማት ጋራ እንዳንፋጠጥ ፖሊሲዎቻቸውን መቀበልና ተግባራዊ ማድረግ አለብን የሚል መልስ አዘጋጅተን ነበር። ኪአሁን በፊት አንግበነው በነበረው ፕሮግራማችን የሰፈረውን መንግሥት በኢኮኖሚው የሚኖረው ወሳኝ ሚና መጫወቱን እውን ለማድረግ በፓርቲዎች ሥር በሚደራጁ የኢኮኖሚ ልማት ተቋማት አማካይነት እንንቀሳቀሳለን እንል ነበር። እነዚህን በፓርቲዎች ሥር የሚቋቋሙ የኢኮኖሚ ድርጅቶችም ከዓለም ገንዘብ ድርጅትና ከዓለም ባንክ ተቃውሞ እንዳይገጥማቸው ለበጎ አድራጎት ተግባር የሚሰማራ ፋውንዴሽን ስም አስመዝግበን የመንግሥት ኢኮኖሚያዊ ተቋማት የሚጫወቱትን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ ይቻላል እንልም ነበር።

ፀህወሓት ሥር ትካል እግሪ ምትካል ትግራይ /ትእምት/ ወይም የትግራይ መልሶ ማቋቋም ድርጅት *(Endowment Fund for the Rehabilitation of Tigrai - EFFORT)*፣ በብአዴን ሥር ጥረት፣ በደኢሕዴግ ሥር ወንዶ፣ በኦሕዴድ ሥር ቱምሳ፣ በሚል የተቋቋሙት የንግድ ድርጅቶች በዋናነት ከዚህ አስተሳሰብ የመነጩ ነበሩ። እነዚህ የፓርቲ የኢኮኖሚ ተቋማት መንግሥትን ተክተው ገዢ የኢኮኖሚ ተቋማትን በመቆጣጠር የኢንዱስትሪ ልማቱን ያፋጥናሉ ቢባልም በተጨባጭ ግን በተባለው ዓላማ ዙሪያ ሊንቀሳቀሱ አልቻሉም። የኦሕዴዱ ቱምሳ በጫት ንግድ፣ የብአዴኑ ጥረት በማዳበሪያ ንግድ፣ የህወሓቱ ትእምት ፀሕንፃ መሣሪያና በምግብ ፍጆታ ዕቃዎች ንግድ፣ ጭምር ተሰማርተዋል። በኢንዱስትሪውም ፀሆን ከፕላስቲክ ጀምሮ እስከ ቢራ ምርት ተሰማርተው ነበር። በነዚህ ኩባንያዎች አማካይነት ገዢ ኢንዱስትሪዎችን የማቋቋሙ ተልእኮ እንደተባለው ሊሳካ አልቻለም። ፀእርግጥ ሲቋቋሙ በኢንዱስትሪ ልማት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ ሲባል በኬሚካል፣ ሜታለርጂ፣ ሜካኒካል፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ኮምፕዩተር ምሕንድስና፣ ወዘተ... ፀመሳሰሉት ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥተው ይሠራሉ ተብሎ ታስቦ ነበር። ኋላ ላይ ግን ሁኔታው ከተመቻቸ ተራ ነጋዴው ሊሠራው በሚችለው በችርቻሮና ዝቅተኛ ሽቀጦችን ፀማምረት ሥራ ላይ ተሰማርተው ነበር። አብዮታዊ ዴሞክራሲ የኢምፔሪያሊዝምን ተጽዕኖ ለመቋቋም በፓርቲ ባለቤትነት ሥር ያሉ የኢኮኖሚ ድርጅቶች ያቋቁማል ተብሎ የድርጅቱን አባላት ቢያደናግርም በተጨባጭ ግን መንግሥት ጠንካራ አገራዊ ኢኮኖሚ ፀመገንባት ረገድ ያለውን የተወሰነ ሚና አኮላሽቶ በሙስና የተተበተቡ የኢኮኖሚ ድርጅቶችን አቋቁሟል።

በኢኮኖሚው ረገድ ለካድሬዎች ሲሰጥ የነበረው ራስን የመቻልና የውጭ ተጽዕኖን የመቋቋም መርሕ ከላይ የተጠቀሰው ሆኖ፣ በፖለቲካው ረገድም ኢሕአዴግ አውራና ብቸኛ የአገሪቱ ፓርቲ ሆኖ የሚወጣበት አቅጣጫ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን ለካድሬው ትምህርት ይሰጥ ነበር። በዚህ የካድሬ ትምህርት ቤት እጅግ አከራካሪ ከነበሩት ጉዳዮች አንዱ የጎብረ ፓርቲያዊ ሥርዓት በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ላይ ሊያሳድረው የሚችለው ተጽዕኖ ነበር። በዚህ ዙሪያም ኢሕአዴግ እንዴት መጓዝ እንዳለበት አቅጣጫ ተቀምጦ፣ ጎብረ ፓርቲያዊ ሥርዓት ባለበት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የበላይነት *(hegemony)* እንዴት ማረጋገጥ እንደሚቻል ይገለጽ ነበር። በዚህ ንድፈ ሐሳብ መሠረት አብዮታዊ ዴሞክራሲ በአብዛኛው የጎብረተሰብ ክፍል ተቀባይነት ካገኘ ኢሕአዴግ ኖረም አልኖረም የሕዝቡ የፖለቲካ አስተሳሰብ መመሪያ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ ይቻላል ይባል ነበር። ለዚህ ማረጋገጫ በአብነት ይጠቀስ የነበረውም የእንግሊዝ ሌበርና ኮንሰርቫቲቭ ፓርቲ አስተሳሰቦች በሕዝቡ ተቀባይነት በማግኘታቸው ሕዝቡ ከነዚህ አማራጮች ውጭ ሌላ አያስብም የሚለው ነበር። ኢሕአዴግም የሚገዳደረው ፓርቲ ሳይኖር ለዘለዓለም ለመኖር ለካድሬው ሕዝቡ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ውጭ ሌላ አማርጭ እንዳያስብ እንዲያደርግ ኃላፊነት ሰጥቶት ነበር።

በተራ አባላት ብቻ ሳይሆን በካድሬውና በአመራሩ ጭምር ብዥታና ውዥንብር የፈጠረውን አብዮታዊ ዴሞክራሲ እኛ በፈለግነው አግባብ ልንተረጉመው ብንሞክርም ሊሳካልን አልቻለም። ይህ የሆነበት ምክንያትም አብረው ሊሄዱ የማይችሉና የማይስማሙ አስተሳሰቦችን አንድ ላይ ለማበን ልንጓዝ በመሞከራችን ነው። በአንድ በኩል የብረቶን ውድስ ተቋማት የሆኑት የዓለም ገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ ያስቀመጧቸውን የነጻ ገበያና የጎብረ ፓርቲያዊ ሥርዓት መመርያዎች ተግባራዊ ለማድረግ ግዴታ ገብተን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ሲል የጨበጥነውንና የሊበራሉን ርዕዮተ ዓለም የሚቃወመውን የአንድ ፓርቲ የበላይነትንና ገዥ የኢኮኖሚ ተቋማትን በመንግሥት እጅ ይሁኑ የሚለውን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮትን መከተል ቃል ገብተን ነበር።

አኪያሄዳችን ሁሉ የተመሠረተው አንድ ወጥ በሆነ ርዕዮተ ዓለምና ስትራቴጂ ላይ ሳይሆን እንደየሁኔታው በሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚያስችለንን ፖሊሲና አቅጣጫን በመከተል ነበር። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው አገራችን ውስጥ የአብዮቱ ጠላቶች ያልናቸውን ለመፈረጅ የተከተልነው ስልት ነበር። ቀደም ሲል እንደ ጠላት የፈረጅናቸው መደቦች ማለትም ፊውዳሎች፣ ጥገኛ ከበርቴዎችና ኢምፔሪያሊስቶች በጎብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቦታ ነበራቸው። የተዳቀለውን ፖለቲካ ማራመድ ከጀመርን በኋላ ግን ጠላት ያደረግናቸው ትምክሕተኞችና ጠባቦች ሲሆኑ መደባዊ ወይም ማኅበራዊ መለያ አልነበራቸውም። ስልቱ በደፈናው እኛን የሚቃወሙና የሚቀናቀኑ ፓርቲዎችን፣ ቡድኖችንና ግለሰቦችን ለመምታት የምንጠቀምበት ብቻ ነበር። ማርክሲዝም ሌኒኒዝም በምንከተልበት ወቅት ትምክሕተኝነት ማለት ገዥው መደብ የሚያራምደው ሌሎች ብሔሮችና ብሔረሰቦችን ከኛ በታች ናቸው ብሎ የሚያምን አደገኛ አመለካከት ነው እንል ነበር። ጠባብ ብሔርተኝነት ማለት ደግሞ የጭቁን ብሔር ተወላጆች የሚያራምዱት ገዥውንና ተራውን ሕዝብ ሳይለይ ሁሉንም በደፈናው በጠላትነት የሚፈርጅ አመለካከት ነው እንል ነበር። በተለወጠው አጋጣሚ ደግሞ ይህን ሁሉ ሽምጥጠን ክደን ከበርቴውን የሥርዓቱ ዋነኛ የእድገትና የልማት ኃይል አድርገን ወስደን በከበርቴው መደብ የሚመራ የከበርቴ ሥርዓት እንገነባለን ስንል ትምክሕተኛና ጠባብ የምንለው ማንን እንደሆነ ግልጽ አልነበረም። ይህ ሆኖ ይመስላል በንድፈ ሐሳብ ላይ ያልተመሠረተው ጠላትን የመፈረጅ ትንታኔያችን በዘፈቀደ ተቀናቃኞቻችንን ለመድፈቅ የሚያገለግል ስልት ሆኖ ቀርቷል።

በተለያዩ ጊዜያት የኢሕአዴግን ፖሊሲ ከመሠረቱ የሚቃወሙ ግለሰቦችና ቡድኖች በትምክሕተኝነት አልያም በጠባብነት እየተፈረጁ መዋከባቸው አጠያያቂ አይደለም። ዓሰብ የኢትዮጵያ ናት፤ የኢትዮጵያና የኤርትራ ግንኙነት ለኤርትራ የሚያደላ ነው፤ እስከ መገንጠል የሚለው መብት በሕገ መንግሥቱ መካተት የለበትም፤ ይሉ የነበሩ ወገኖችን በትምክሕተኝነት ተፈርጀዋል። በሌላ በኩል በሕገ መንግሥቱ የሰፈረውን የመገንጠል መብት ተጠቅመን ብሔራችንን ነጻ ለማድረግ እንፈልጋለን፤ ብሔረ ሰባችን የራሱን ክልል ለመመሥረት ይፈልጋል፤ የኢሕአዴግ አገዛዝ ለብሔር ብሔረሰቦች አይበጅም፤ ብሔራችን በማዕከላዊ መንግሥት በቂ ሥልጣን ይሰጠው፤ የሚሉትን ከአማራው ብሔር ውጭ የሆኑትን ወገኖች በጠባብነት ተፈርጀዋል። ኢሕአዴግ እነዚህን ፅንሰ ሐሳቦች በብሔሮች መካከል ውጥረት ሲፈጠር ሽምጋይና አስታራቂ መስሎ የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘም ተጠቅሞባቸዋል። ኢሕአዴግ አማራው ክልል ውስጥ ሲንቀሳቀስ ጠባቦች መጥተው ሊውጡህ ስለሆነ ከእነርሱ ከሚያድንህ ከኢሕአዴግ ጎን ተሰለፍ ብሎ ይቀሰቅሳል። በኦሮሚያ፣ በትግራይና በሌሎች ክልሎች ደግሞ ትምክሕተኞች ዳግም አንሰራርተው ሊውጡህ ነው፤ ኢሕአዴግን ካልተቀበልክና ካልደገፍክ መቀመቅ ትገባለህ እያለ በማስፈራራት ይቀሰቅሳል። እንግዲህ የትምክሕትና የጠባብ ብሔርተኛ ፖለቲካ መነሻና ስልት ሥልጣን የመቀጠል አባዜ ያመነጨው ካልሆነ ሌላ የረባ ትርጉም የለውም። የኢሕአዴግ ካድሬም የሠለጠነው በዚህ ፖለቲካ ስለነበር የፖለቲካው አቅጣጫ በዜጎች የፖለቲካ ሕይወት ላይ የሚኖረው አስከፊ እንድምታ ቢገባውም ባይገባውም የተሰጠውን መፎአክት ሰንቆ በየቀኑ ማስተጋባቱ ግን አልቀረም።

በአጠቃላይ ለለጋሾችና ለሕዝቡ የሚነገረው፣ በሽግግር ቻርተሩ የሰፈረው ዴሞክራሲና ለካድሬው የሚሰበከው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አቅጣጫ፣ እየተጋጨ ካድሬውንና የድርጅቱን አባል ብዥታ ውስጥ አስገብተውት ነበር። ካድሬውም የድርጅቱን መርሐ ግብር ተቀብሎ መሄድ ግዴታው ስለነበር ጠላት ተብሎ የተፈረጀው ዜጋ ሲገደል፣ ሲታሰር፣ ሲገረፍ፣ ሲሰደድ፣ ከኑሮው ሲፈናቀል፣ ይህ ተገቢ ነው ይል ነበር። የካድሬው ትምህርት አንዱ መሠረታዊ ችግርም ዴሞክራሲም ይሁን ሰብአዊ መብት ለወዳጅ የሚሰጥ እንጂ ለጠላት የሚተርፍ አይደለም ማለቱ ነበር። ቻርተሩ ኢትዮጵያውያንን በሙሉ ዜጎች በማለት የዜግነት መብት ሲያጎናጽፋቸው ኢሕአዴግ የተከተለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ደግሞ ጠላት የተባሉትን ዜጎች የሚያፍን፤ የሚያዋክብና የሚያሳድድ ነበር። እነዚህን እርስ በእርስ የሚቃረኑ አቅጣጫዎችም ተከትለን በመሄዳችን በማያባራ ውዥንብር ውስጥ ተጉዘናል ለማለት ይቻላል።

7. *የትእምት ባለቤትነት ጥያቄ*

የትጥቅ ትግሉ አብቅቶ ሰላማዊ ኑሮ ሲጀመር በአመራሩ መፈታት የነበረባቸው በርካታ ከባድ ችግሮች ነበሩ። ከነዚህ አንዱ በጦርነት የፈራረሰውን አካባቢ መልሶ ማቋቋምና ሕዝቡ ተረጋግቶ ሰላማዊ ኑሮውን የሚመራበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነበር። ለመልሶ ማቋቋሙ የሚሆነውን ሀብት ማሰባሰብም አንድ ትልቅ ተግዳሮት ነበር። ከለጋሾች መጠነኛ እርዳታና ብድር ሊገኝ እንደሚችል ብንገምትም ይህ እጅግ የደቀቀውን መሠረተ ልማት መልሶ ለማቋቋም በቂ እንደማይሆን እንረዳ ነበር። ከዚህ በመነሣትም ይህን መልሶ የማቋቋሙን ሥራ ለማከናወን የተለያዩ ዘዴዎችን መቀየስ እንዳለብን ተገንዝበን ነበር። በየክልሉ ሕዝቡ ፅውቀቱን፣ ገንዘቡንና ጉልበቱን ለግሶ በመልሶ ማቋቋምና በልማት የሚሳተፍበት አቅጣጫም ተነድፎ ነበር። የትግራይ ክልልም ይህን አቅጣጫ ተከትሎ ቀደም ሲል በትጥቅ ትግሉ ግብቅያ ዋዜማ አሜሪካን አገር የተቋቋመውን «*የትግራይ ልማት ማኅበር /ትልማ/*» በአገር

ውስጥ ካሉ ምሁራን ጋራ አቀናጅቶ እንዲደራጅ ተደረገ። በዚህ መሠረትም በቅድሚያ አዲስ አባባ የነበሩትን፣ ከዚያ በኋላ ደግሞ በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የነበሩትን ምሁራን፣ ባለሀብቶችና ሌሎች የክልሉ ተወላጆች በማደራጀት በመልሶ ማቋቋሙ ሥራ እንዲሰማሩ ተደረገ።

የገጠሩን ሕዝብ ለልማት በማሰባሰብና በማደራጀት ረገድም በትጥቅ ትግሉ መጀመሪያ ገደማ ማለትም በ1970 ዓ.ም. የተቋቋመው ማረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ውሳኔ ተላለፈ። ማረት የተራቆተውን የተፈጥሮ ሀብት እንዲንከባከብና እንዲያለማ፣ በዕለት ደራሽ ሥራ እንዲሰማራ ተደርጎ ከውጭ ለጋሾች የሚገኘውን እርዳታ እያስተባበረ በአገሪቱ ሕግ መሠረት መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሆኖ ተመዘገበ።

ከነዚህ ድርጅቶች ውጭ ሌላ የልማት ድርጅት ለማቋቋምም ሐሳብ ቀርቦ ነበር። በትጥቅ ትግሉ ጊዜ ከንግድ፣ ከእርዳታና ከሙር ምርኮ ያሰባሰብነው የተወሰነ ሀብት ስለነበር እንዴት ሥራ ላይ ልናውለው እንችላለን የሚለው ጉዳይ በህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ አነጋገሪ ሆኖ ነበር። ይህንን ገንዘብ ለተሠው ታጋይ ቤተሰብ በማከፋፈል ወይም ደግሞ በተደራጀ መንገድ ልማት ላይ ማዋል ይሻላል የሚሉ አማራጮች ቀርበው ውይይት ከተደረገ በኋላ በመጨረሻ ገንዘቡ ለልማትና የኢኮኖሚ ለውጥ ለማምጣት እንዲውል ተስማማን። ይህ ሲሆን ግን ገንዘቡ በአካባቢው የኢኮኖሚ ለውጥ በሚያስከትል መንገድ ጥቅም ላይ መዋል አለበት ተብሎ አንድ የኢንቬስትመንት ተቋም እንዲመሠረት ተወሰነ። የዚህ ተቋም መመሥረት ፋይዳ በእኛችን የነበረውን ገንዘብ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ብቻ ሳይሆን የልማት ሐሳቦቻችንም ሥራ ላይ ማዋልና ልማት ማረጋገጥ ነበር። ይህን ተግባራዊ ለማድረግም በመለስ ዜናዊ የቦርድ ሊቀመንበርነትና በስብሓት ነጋ ሥራ አስኪያጅነት የሚመራና የተወሰኑ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን በቦርድ አባልነት ያካተተ አንድ ቡድን ተቋቋመ። በወቅቱ በዚህ ቦርድ አባላት ሆነው የተሰየሙት፤ 1ኛ/ ተወልደ ወልደ ማርያም፣ 2ኛ/ ዓለም ሰገድ ገብረ አምላክ፣ 3ኛ/ ስብሓት ነጋ፣ 4ኛ/ ቴዎድሮስ ሓጎስ፣ 5ኛ/ አባዲ ዘሞና 6ኛ/ አርከበ ዕቁባይ ሲሆኑ፣ ስብሓት ሥራ አስኪያጅ ሲሆን በእርሱ ሥር የድርጅቱን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚመሩት ቴዎድሮስ፣ አባዲና አርከበ ነበሩ።

በዚህ መሠረትም «ትካል እግሪ ምትካለ ትግራይ /ትእምት/» ወይም «የትግራይ መልሶ ማቋቋም ተቋም» የሚል ድርጅት ተቋቋመ። ፓርቲዎች በንግድ ሥራ እንደማይሰማሩ የተለያዩ አገሮች ልምድ ያመለክት ስለነበር በኢትዮጵያ የተለየ አኪያሄድ አይኖርም በሚል የዚህ ዓይነቱ የልማት ተቋም ሊመሠረት የሚችልበትን ሕጋዊ ማዕቀፍ ተነጋግረንበት ነበር። ይህን መሰል ተቋም የሚያስተናግድ የበጎ አድራጎት ድርጅት (foundation) ማቋቋምያ ሕግ እንዳለ የሕግ ባለሙያዎች ጠቁመውንም የበጎ አድራጎት ድርጅት እንዲሆን ተወሰነ። የበጎ አድራጎት ድርጅት ሀብት ለግለሰቦች እንደማይከፋፈልና ለልማት ሥራዎች ብቻ እንደሚውል ሕጉ ይደነግግ ነበር። በዚህ መንገድ የተቋቋመው ትእምት አንዳንድ የልማት ሥራዎችን ለመጀመር የጥናት እንቅስቃሴ አድርጎ በመጀመሪያ የማዕድንና የግብርና ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት አድርጎ የሲሚንቶ፣ የዕብነ በረድና የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎችና የግብርና ኩባንያ ሊያቋቁም ቻለ።

ሌሎች የኢሕአዴግ አባል ደርጅቶችም ተመሳሳይ ተቋማት እንዲያቋቁሙ ተወስኖ የተመደበላቸውን የገንዘብና የንብረት መጠን ባላስታውስም ብአዴን ጥረትን ሲያቋቁም በህወሓት እጅ ከነበረው የትጥቅ ትግሉ ገንዘብ አርባ ሚልዮን ብርና በርከት ያሉ መኪኖች እንደተሰጠው አስታውሳለሁ። ይህን ገንዘብ መነሻ በማድረግ ጥረት የተለያዩ ኩባንያዎችን ለማቋቋም ጥናት አኪያሂዶ የቢራ ፋብሪካ፣ የእርሻ፣ የትራንስፖርትና ሌሎች ኩባንያዎችም

አቋቁሟል። የኦሕዴዱ ዲንሾም ሥራውን የጀመረው በጫት ንግድ ሲሆን ወደ ሌሎች የንግድ ዘርፎችም ለመሰማራት ቢዘጋጅም እስከማውቀው ድረስ ተለቅ ያለ የኢንቬስትመንት ኩባንያ አላቋቋመም።

የኢሕአዴግ የልማት ተቋማት ከታለመላቸው ስትራተቴጂያዊ ኢንዱስትሪዎች የማቋቋም ዓላማ አንጻር ያሳዩት እድገት እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ከዚህ የበለጠ የሚያሳስበው ግን እስከ አሁን ድረስ የነዚህ ድርጅቶች ባለቤት፣ ተቆጣጣሪና ተጠቃሚ ማን እንደ ሆነ በውል አለመታወቁ ነው። ከነዚህ የኢሕአዴግ የኢኮኖሚ ተቋማት መካከል እጅግ ጎልተውና ፕዝፈው የሚታዩት የህወሓቱን ትእምት እና የብአዴኑን ጥረት የሚያሽከረክሯቸው የፓርቲዎቻቸው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ናቸው። ለረጅም ጊዜ የትእምት የቦርድ ሊቀመንበር መለስ ዜናዊ፣ ዋና ሥራ አስኪያጁ ደግሞ ስብሓት ነጋ ሆነው ቆይተዋል። ከህወሓት ክፍፍል ጥቂት ዓመታት ቀደም ብሎ ደግሞ ስብሓት ነጋ በስዬ አብርሃ ተተክቶ፣ ከክፍፍሉ በኋላ ስብሓት ነጋ ቀደም ሲል ደካማ ነው ተብሎ ተገምግሞ ያጣውን የትእምት ሥራ አስኪያጅነት ቦታ እንደገና እንደ ስጦታ አግኝቶታል። የትእምት ቦርድ ሊቀ መንበርነትም በወቅቱ የአምቦ ውሃ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድና የሙገር ሲሚንቶ የቦርድ ሊቀመንበር ለነበረው ለሥዩም መስፍን ተሰጥቶ ነበር። ሥዩም መተካካት በሚለው የኢሕአዴግ አዲስ ፈሊጥ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱ ተነሥቶ በቻይና የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆኖ ሲሾም በምትኩ የህወሓቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ቴዎድሮስ ሓጎስ የትእምት ቦርድ ሊቀመንበር ሆኖ ተሰየመ። የህወሓት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆነው አባዲ ዘሞ ስብሓትን ተክቶ የሥራ አስኪያጅነቱን ቦታ ይዞ ከቆየ በኋላ ወድያውኑ ተሸሮ የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ባለቤትና የህወሓት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል በሆነችው በአዜብ መስፍን ተተካ።

ትእምት በቢልዮኖች የሚገመት ካፒታል ባለቤት ቢሆንም፣ በበርካታ የኢኮኖሚ ዘርፎች ቢሰማራም ሙያዊ ብቃት ያለውና በሥነ-ምግባር የታነጸ አመራር ባለማግኘቱ በተደጋጋሚ ለኪሳራ፣ ለብክነትና ለዝርፊያ ተዳርጓል። ከትእምት ጋራ ከተያያዙት አስገራሚ ዝርፊያዎች እንዱ በ1993 ዓ.ም. ጉና በተባለው የትእምት የንግድ ክንፍ የታዘዘው አንድ መርከብ ሙሉ የተጫነ የግንባታ ብረት የት እንደደረሰ ሳይታወቅ መቅረቱ ነው። ይህ ከስድስት ሚልዮን ብር በላይ ያወጣል ተብሎ የሚገመተውን ብረት የትኛው ውቅያኖስ ውጦት እንደቀረና ለዚህም ማን ተጠያቂ እንደሆነ አይታወቅም። ይህን ድርጅቱ ራሱ ያመነውን ዝርፊያ እንዲየው ለናሙና አወሳኹት እንጂ የዋናውን ዝርፊያ መጠን የሚያመለክት አይደለም።

ያም ሆነ ይህ በትእምት የባከነውንና የተዘረፈውን ሀብት አስመልክቶ እስከ ዛሬ ድረስ ተጠ ያቂ የሆነ ግለሰብም ይሁን ቡድን የለም። ትእምት ውስጥ ዝርፊያ እንደሚካሄድ በተለያዩ ወቅቶች በተደረጉ ግምገማዎች ይፋ ቢደረጉም በጥፋተኝነት የተገመገሙት ግለሰቦች አንዱም በሕግ አልተጠየቁም። አንዳንድ ትእምት ውስጥ ይሠሩ የነበሩ ግለሰቦች እጅግ ባለጸጋ እንዲያውም ሚልዮኔሮች ሆነው ያለምንም ተጠያቂነት በአገሪቱ ሲኖሩ ይታያሉ። አንዳንዶቹ ከምንም ተነሥተው በአጭር ጊዜ ውስጥ ትላልቅና ብዛት ያላቸው መኪኖች ግሰማራት ሲጀምሩ፣ የተወሰኑትም ከተጠያቂነት ለማምለጥ አገር ጥለው ጠፍተዋል። ሲሚንቶ ውድ በሆነበትና ምርቱንና ስርጭቱን የትእምት ድርጅቶች በተቆጣጠሩበት ወቅት አየር ባየር ንግድ ውስጥ በመግባት ከፍተኛ ሀብት ያካበቱት ወገኖችም ከትእምት አመራር ዕይታ ውጭ ነበሩ ለማለት አይቻልም። መጨረሻ ላይ ለእስር የተዳረጉት ጥቂቶቹም መከታ ያጡ ምስኪን ዘራፊዎች ነበሩ።

ትእምት የማን ነው? ለሚለው ጥያቄ እስከ አሁን ድረስ መልስ አልተገኘለትም። በእርግጥ ከሕግ አንጻር ትእምት የፓርቲ፣ የመንግሥት ወይም የሕዝብ ሳይሆን በበጎ አድራጎት ስም የተቋቋመ ድርጅት እንደሆነ ታውጇል። ከሕግ አንጻር ይህን ይባል እንጂ አጠቃላይ እንቅስቃሴውን የሚመራውና የሚቆጣጠረው ግን ሕዝቡን እወክላለሁ፣ የክሉልን መንግሥት እመራለሁ፣ የሚለው ህወሓት ነው። በመሆኑም ህወሓት ፓርቲም፣ ሕዝብም፣ መንግሥትም ስለሆንኩ የሁሉንም ጥቅም በሚያካትት ሁኔታ ሀብቱን እያስተዳደረኩ ነው፤ እያለ ነው። ያም ሆኖ የሁሉም ነው እየተባለ የማንም ሳይሆን ቀርቷል።

ትእምት በትክክል የህወሓት ሀብት ከሆነ እያንዳንዱ የድርጅቱ አባል ከካፒታሉ ድርሻ ኖሮት በድርሻው መሠረት ውሳኔ መስጠትና በስምሪቱ መሳተፍ ነበረበት። ትእምት የትግራይ ሕዝብ ሀብት ነው ከተባለም ሕዝቡ በድርጅቱ የቀጥታ ባለቤትነት መብት ሊኖረው በተገባ ነበር። ለምሳሌ ሩሲያኖች በመንግሥት እጅ የነበረውን ሀብት ወደ ግል ለማዘዋወር ሲወስኑ በመጀመሪያ ሀብቱን አስገምተው ግምቱን ለምልአተ ሕዝቡ በአክስዮን መልክ አከፋፍለው፣ ባለ አክስዮኖቹ ሲያሻቸው አክስዮኑን ሸጠው አልያም ባለድርሻዎች ሆነው ቀጥለዋል። በተመሳሳይም ትእምት የሕዝብ ነው ከተባለ የተረከበውን ሀብት አስገምቶ በአክስዮን መልክ ለሕዝቡ ማከፋፈል ነበረበት።

በሌላ በኩል ትእምት የሕዝብ ነው ከተባለ ባለቤትነቱም ሕዝቡን እወክላለሁ የሚለው መንግሥት ማለትም የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መሆን ነበረበት። ምናልባት ትግራይ ውስጥ ፓርቲውና መንግሥቱ አንድ መሆናቸው ሀብቱ የመንግሥት ይሁን የፓርቲው አጠያያቂ ሊያደርገው ቢችልም ቢያንስ ከሕግ አንጻር ግን ግዙፉን የትእምት ሀብት በመንግሥት እጅ ቢሆን የተሻለ ነበር። ይህ ባለመሆኑም ትእምት የሕዝብ ነው ሲባል ምን ማለት እንደሆነ መጠየቅ አለበት።

ህወሓት ትእምት የኢትዮጵያ ሕግ ፈሚፈቅደው መሠረት የተቋቋመ በጎ አድራጎት ድርጅት ነው ቢልም ትእምት የተቋቋመበት ዓላማ፣ አኪያሄዱና አሠራሩ ከዚህ ፍጹም የተለየ ነው። ትእምት፣ በቀጥታ ህወሓት፣ በተለይ አመራሩ እንዲያውም ከአመራሩ ውስጥ የተወሰኑ ግለሰቦች የሚያዙበት ሀብት ሆኗል። ለዓመታት በስብሓትና በመለስ እንዲሁም በቤተሰቦቻቸው ቁጥጥር ሥር የነበረው ትእምት በመጨረሻ የበጎ አድራጎት ድርጅት ሀብት መሆኑ ቀርቶ የቤተሰብ ኩባንያ ሆኗል። ከተቋቋመበት ዓላማ አንጻር እንኳ ሀብቱ ለበጎ አድራጎት ተግባር ይዋል ቢባልማ ዋናዎቹ ተጠቃሚዎች የተሠው ታጋዮች ቤተሰቦች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ሥራ ዐጥ ታጋዮችና ሌሎች የተጎዱ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሆኑ ነበር። እስከ አሁን ድረስ የተሠዉ ታጋይ ቤተሰቦች አንድ ጊዜ ከተወረወረላቸው በጣም ትንሽ እርዳታ ውጭ ከትእምት ያገኙት ጥቅም የለም። ካካበተው ሀብት አንጻር ሲታይ በአካባቢ ልማት ረገድም እዚህ ግባ የሚባል አስተዋፅኦ አላደረገም።

8. የ1985 ዓ.ም. የህወሓት ግምገማና ውዝግቦቹ

ህወሓት ካድሬዎቹና ታጋዮቹ ለአዲሱ የመንግሥት ሥልጣን እንዲዘጋጁ ሰፊ ሥልጠናና ትምህርት ቢያካሂድም በድርጅቱ ውስጣዊ አንድነትና መረጋጋትን ሊፈጥር አልቻለም ነበር። ለዚህም ምክንያቱ የመንግሥት ሥልጣን ሲያዝ ተከትለው የመጡት ለውጦች በአብዛኛዎቹ ተቀባይነት ያለማግኘታቸው ነበር። በትግሉ ዘመን ታጋዮች በአመጋገባቸው፣ በአለባበሳቸው፣ በአኗኗራቸውና በአስተሳሰባቸው ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነበሩ። ብዙ ወጣቶች ትግሉን እንዲቀላቀሉ የገፋፋቸው አንዱ ምክንያትም ይህ ሰፊ ልዩነት ያልነበረው የገዳም ወይም የምሽግ ሶሻሊዝም ነበር። በትጥቅ ትግሉ ማብቅያ ገደማ የሚከፋፈለው

መቁነን *(Ration)* እንደየሥራው ክብደትና እንደየሁኔታው መለየት አለበት ተብሎ መጠነኛ ለውጥ ቢደረግም በአመዛኙ ግን የሚገኘውን ምግብና ልብስ እኩል የሚከፋፈሉበት ነበር። ኋላ ላይ በተዋጊውና በድጋፍ ሰጪው፣ እንዲሁም በአእምሮና በጉልበት ሥራ በተሰማሩት መካከል የመቁነን ልዩነት ሲደረግ መጠነኛ ተቃውሞ ቢያጋጥምም አብዛኛው ታጋይ ይሽን ተቀብሎት ነበር።

ህመሓት/ኢሕአዴግ ከተማ ሲገባና ሥልጣን ሲቆጣጠር ምን ዓይነት የኑሮ ልዩነት ሊከሰት እንደሚችል መገመት አይቻልም ነበር። ደርግ ተቸንፎ ኢሕአዴግ ሥልጣን ሲይዝ ግን በተዋጊው ሠራዊት የነበሩት ታጋዮች መጀመሪያ ላይ እንዳሉ በመከላከያ ሠራዊት እንዲቀጥሉ ሲደረግ፣ በተለያዩ ክፍሎች ተመድበው ይሠሩ የነበሩት ደግሞ በአብዛኛው በተለያዩ ሲቪል የመንግሥት ሥራዎች ተመደቡ። ጥቂቶቹ በፖሊስነትና በካድሬነት ተመድበው፣ በካድሬነት የተመደቡት የተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተቀጣሪ እንደሆኑ በማስመሰል ደመወዝ ይከፈላቸው ነበር።

አብዛኛዎቹ ታጋዮች ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አግባብ ቢሰማሩም በትምህርት ያልገፉትና በአካል ብቃታቸው ደከም ያሉቱ ከነዚህ የሥራ መደቦች ውጭ ሆነው ተንሳፍፈው ነበር። ተንሳፋፊዎቹ ምድብ ሥራ ያልተሰጣቸውና ዞሮ ዞሮ እንደሚሰናበቱ ተገምቶ ሲሆን ሴት ታጋዮች ብቻ እስከተወሰነ ጊዜ መከላከያ ሚኒስቴር እየከፈላቸው እንዲማሩ ተደርጎ፣ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ግና ሥልጠና ተሰጥቷቸው በተለያዩ ሥራዎች እንዲመደቡ ተደርጓል። በርካታ ሴት ታጋዮች ትእምት ባቋቋማቸው የጨርቃ ጨርቅና የስፌት መሰሰሉ ፋብሪካዎች በጉለበት ሠራተኝነት ሲመደቡ በትምህርት ደህና የገፉት ደግሞ እንደየዓቅማቸው በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተመድበው ነበር። ምንም ዐቅም የላችሁም የተባሉት የተወሰኑት ደግሞ ትንሽ ገንዘብ እየተሰጣቸው ተሸኝተዋል። ብዙ ሴት ታጋዮች የተመደቡበት ሥራ እጅግ አድካሚ ከመሆኑ ባሻገር የሚከፈላቸው ደመወዘ ዝቅተኛ ስለነበር ከፍተኛ ቅሬታ ነበራቸው። በሚከፈላቸው ደመወዛቸውም እንኳን ቤተሰብ ሊያስተዳድሩ የግል ኑሯቸውንም ለመምራት በጣም ተቸግረው ነበር። በምትከፈላቸው አነስተኛ ደመወዝ የኪራይ ቤት፣ የምግብ፣ የልብስና ሌላ ወጪያቸውን መሸፈን ያዳግታቸው ስለነበርም በየጊዜው ቅሬታና አለመግባባት ቢነሣም ለችግሮቹ መፍትሔ መግኘት አልተቻለም ነበር። ለጥያቄያቸው ይሰጣቸው የነበረውም መልስ እንደሌላው ሲቪል ሠራተኛ ሁሉ ደመወዛችሁን አብቃቅታችሁ ኑሯችሁን መግፋት አለባችሁ የሚል ነበር።

ከዚህ ሁሉ ወጣ ያሉና ከፍ ብለው በተጠቀሱት ምድብ ሥራዎች ያልተካተቱ በትጥቅ ትግሉ ጊዜ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ታጋዮችም ነበሩ። እነዚህም በጎ አድራጊ ድርጅቶች፣ የውጭ መንግሥታትና በተወሰነ ደረጃም መንግሥት በመደበው ገንዘብ በተለየ መንገድ የመልሶ ማቋቋም መርሐ ግብር ተነድፎላቸው ነበር። ሆኖም ለነዚህ አካል ጉዳተኞች የተመደበው በጀት በቂ ካለመሆኑም በተጨማሪ አካል ጉዳተኛ ታጋዮቹን በፍጥነት ማቋቋሙ አስቸጋሪ ነበር። ከጅምሩ እነዚህ አካል ጉዳተኛ ታጋዮች የጠባቂነት መንፈስ እንዳይሰማቸውና ራሳቸውን እንዲችሉ ሥልጠናና ድጋፍ ይሰጣቸው መባሉ በአስቸጋሪ ሂደት እንዲያልፉ አስተዋፅኦ አድርጓል። እነዚህ አካል ጉዳተኞች የትጥቅ ትግሉን ሲቀላቀሉ ገና ወጣቶች ስለነበሩ የግል ኑሮ የመምራት ልምዳቸው ዝቅተኛ ነበር። በዚህ ላይ እንደልብ ተንቀሳቅሰው መሥራት ያዳግታቸው ነበር። በዚህ ሁኔታ፣ በተለያዩ የዕደ ጥበብና አነስተኛ ሥራዎች ተሰማርተው የተወሰነ ክፍያ እየተሰጣቸው እንዲኖሩ ተደረገ። ይህ ሁሉ ሲደረግ የአካል ጉዳታቸው የሚያደርስባቸውን ሥነ-ልቦናዊ ችግር አልተጤነም ነበር። በትንሽ ወጪ ሕይወታቸውን ሊያሻሽሉላቸው የሚችሉ ተሽከርካሪ መንቀሳቀሻዎች *(wheelchairs)*፣ አውቶብሶች፣ መጠለያዎችና ቁሳቁሶች፣ ወደ ተለያዩ የሕዝብ ተቋማት በቀላሉ ለመግባት የሚያስችሏቸው ቅድመ ሁኔታዎች አልተዘጋጁላቸውም

ነበር። በአጠቃላይ የአካል ጉዳተኛ ታጋዮቹ ልክ እንደሌላው ታጋይ ዐቀበቱን በገዛ እጃችሁ ውጡት መባላቸው ከፍተኛ ቅሬታ አሳድሮባቸዋል።

የህወሓት ታጋዮች ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አግባብ ኑሯቸውን እንዲቀጥሉ ሲደረግ ሊያስከትሏቸው የሚችሉት ችግሮች በደንብ አልተጤኑም ነበር። በድርጅት መቁነን ሲሰፈርለት የነበረው ታጋይ ኅብረተሰቡን ሲቀላቀል በየትኛው የኑሮ ደረጃ መኖር እንዳለበት ከቶ አያውቀውም ነበር። የኅብረተሰቡን የኑሮ ውጣ ውረድም በሚገባ የተለማመደው አልነበረም። አንዳንዱ የላይኛውን የኅብረተሰብ ክፍል፣ ሌላው ደግሞ የመካከለኛውን ኅብረተሰብ ኑሮ ይመኝ ነበር። ጥቂት የማይባሉት ደግሞ ያለፈውን የታጋይነት ሕይወታቸውን እያስታወሱ ኑሯቸውን በየትኛው አቅጣጫ መምራት እንዳለባቸው ግራ ተጋብተው ነበር። በተለይ በመንግሥት ሥራ ላይ የተመደቡት ታጋዮች ደርግ ትቶት በሄደው የደመወዝ እርከን መከፈል ሲጀምሩ አንዳንዶቹ ከሚከፈሉት ደመወዝ በተጨማሪ ጥቅማ ጥቅም ሲያገኙ ሌሎቹ እጅግ ዝቅተኛ ደመወዝ የሚያገኙበትና አስከፊ ኑሮ የሚገፉበት ሁኔታ ተፈጠረ። የድርጅቱ አመራር አባላትና ከፍተኛ ካድሬዎች በሲቭል ሥራ እስከአገር ጥሬዚዳንትነት፣ ሚኒስትርነትና የክልል አስተዳዳሪነት፣ በወታደራዊ ሥራውም እስከጠቅላይ ኤታ ማዦርነት ሲመደቡ ብዙዎቹ የድርጅቱ አባላት ደግሞ በበታች ሠራተኝነትና በተራ ወታደርነት ሲመደብ የነበረው የኑሮ ደረጃ የሰማይና የምድር ያህል መራራቅ ጀመረ።

በከፍተኛ እርከን የተመደቡት ታጋዮች ዘመናዊ መኪና፣ የተንጣለለ ቪላ፣ ዳጎስ ያለ ደመወዝና የሥራ ማስኬጃ ጥቅማ ጥቅሞች ሲያገኙ፣ አብዛኛው ዝቅተኛው በተለይ ከገጠር ትግሉን የተቀላቀለው ታጋይ አነስተኛ ደመወዝ እየተሰጠው ኑሮውን መግፋትና ቤተሰቡን መምራት አቃተው። በተለይ የቤት ቁሳቁስ፣ ልብስና ሌላ መነሻ ንብረት ያልነበራቸው በርካታ ታጋዮች በሚያገኙት ደመወዝ ምን ማድረግ እንደሚችሉ ጨንቋቸው ነበር። በዚህ መንገድ የህወሓት ታጋይ በሀብታምና በደኻ ተከፋፈለ ። አንዳንድ ከፍተኛ ሥልጣን የተቆናጠጡትን ታጋዮችም ጥቅም ፈላጊዎች አሽትተው ደርሰውባቸው ከነአርሱ በሚያገኙት ተጨማሪ ጥቅም ታክሎበት የተንደላቀቀ ኑሮ መኖር ጀመሩ። ይህን ሁለት ዓለም ያስተዋሉ ብዙ ዝቅተኛ ታጋዮች ሁኔታዎች እጅግ ተለዋውጠውባቸው በመከፋታቸው «*ይህን ሁሉ መሥዋዕትነት ከፍለን ኑሯችን ለአንዱ አሥመራ ለሌላው ሑመራ ሆነ*» ይሉ ጀመር።

በታጋዮች መካከል የተፈጠረው የኑሮ ልዩነት ከጊዜ በኋላ የቅሬታ ምንጭ ሆኖ ድርጅቱ ውስጥ ከፍተኛ ችግር ፈጠረ። ተራውና የተከፋው ታጋይ የአመራር አባላት የሚያደርጉትን እያንዳንዱን እንቅስቃሴ እየተከታተለ እገሌ ቤተሰቡን እያደራጀ ነው፤ እገሌ ሀብት እያካበተ ነው፤ እገሌ በከፍተኛ ቅንጦት እየኖረ ነው፤ እገሌ ልጆቹን ጥቂት የከበርቴ ልጆች በሚማሩበትና ከፍተኛ ክፍያ በሚከፈልበት ትምህርት ቤት እያስተማረ ነው፤ እገሌ ደግሞ ሴቶችን እያማገጠ ነው፤ በማለት ሁኔታዎች ሁሉ እንደተመሳቀሉ የሚገልጽ ሰፊ ዘመቻ ያካሂድ ጀመር። ይህ ሁኔታ ያሳሰበው የድርጅቱ አመራር የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ጠርቶ ጉዳዩን ለመመልከት ቢሞክርም ነገሩን ከመሠረቱ ለመፍታት ግን አልተቻለም። በማዕከላዊ ኮሚቴው ስብሰባ በችግሩ ዙሪያ በተወያየንበት ጊዜ በመለስ ዜናዊ በቀረበው የመፍትሔ ሐሳብ እንደመነሻ ተወሰደ። ይህ ሐሳብ «*ማዕከላዊ ኮሚቴው ውስጥ የተወሰነ የግለኝነት አዝማሚያ ቢኖርም እንደ አካል ሲታይ ግን በመሠረቱ የተበላሸ አይደለም። አሁን በአመራሩ ላይ በዘመቻ መልክ እየቀረበ ያለውን የሙስናና የሥነ-ምግባር ብልሹነት ክስ እንዳለ ወስደን እርምጃዎችን ከወሰድን ድርጅቱ ማለቂያ ወደሌለው ችግር ይገባል። ስለዚህ ማትኮር ያለብን በከፋ ግለኝነት ዓይኑ ታውሮ /ሃንጎሪማ ከይኑ/ በድርጅቱ ላይ*

ሥመቻ በከፈተው ታጋይ ላይ መሆን አለበት፤::»[17] የሚል ነበር። ማዕከላዊ ኮሚቴውም በተመሳሳይ «*የግለኝነት ችግር በተወሰነ ደረጃ በአመራሩ የሚንጸባረቅ ቢሆንም ዋናውና የከፋው አደጋ ሆኖ ድርጅቱን ሊበትን የሚችለው ግን ከአመራሩ በታች ባለው ታጋይ የተከሰተው ነው*» በማለት ስምምነት ላይ ደረሰ። አመራሮቹ በዚህ ጉዳይ ላይ በቀላሉ ልንሰማማ የቻልነውና ችግሩን ከመሠረቱ ነቅሎ ለመጣል ቁርጠኝነት ያላሳየነው በአንድ በኩል በከፊልም ቢሆን ራሳችንም የችግሩ ሰለባ ሰለነበርን በሌላ በኩል ደግሞ ችግሩን ያየንበት አቅጣጫ የተሳሳተ ስለነበር ይመስለኛል።

ማዕከላዊ ኮሚቴው ይህን ውሳኔ ካስተላለፈ በኋላ እንደተለመደው ድርጅቱ ውስጥ ሰፊ ግምገማ፣ የሂስና የግለ ሂስ እንቅስቃሴ እንዲደረግ ተወሰነ። ለዚህም የመወያያ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ ተሰራጨ። ጽሑፉ ግለኝነት በድርጅቱ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ አመልክቶ እያንዳንዱ ታጋይ በአመለካከትና በተግባር ያለውን የግለኝነት ችግር በተመለከተ ግለ ሂስ እንዲያደርግ የሚገፋፋ ነበር። ይህን የማያደርግም ታጋይ ተጋልጦ የከፋ ችግር ፈጽሞ የተገኘው እንዲታሰር ተደረገ። በወቅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴው ራሱ ያኪያሂደው ሂስና ግለ ሂስ እንደ አካል ሳይሆን በተመደበባቸው የሥራ ዘርፎች ማለትም በአገር መከላከያ፣ በፌዴራል መንግሥት የሲቪል ሥራ ዘርፍ፣ በትግራይ መስተዳድር፣ በኢሕአዴግ የድርጅትና የፕሮፓጋንዳ ሥራ ዘርፍና በትእምት ነበር። በአገር መከላከያ የነበሩት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ስዬ አብርሃ፣ ጻድቃን ገብረ ተንሣይ፣ ታደሰ በርሄ /ጋውና/፣ አበበ ተከለ ሃይማኖት /ጀቤ/፣ ሓየሎም አርአያ፣ ሳሞራ የኑስ፣ ታደሰ ወረደና ጌታቸው አሰፋ ሲሆኑ፣ በፌዴራል መንግሥት የሲቪል ሥራዎች መለስ ዜናዊ፣ ሥዩም መስፍን፣ ዓባይ ፀሐዬ፣ አውዓሎም ወልዱ፣ ሙሉጌታ ገብረ ሕይወት /ጫልቱ/፣ ሙሉጌታ ዓለም ሰገድ፣ ቢተው በላይ፣ ክንፈ ገብረ መድኅን፣ ብርሃነ ገብረ ክርስቶስና አዲስ ዓለም ባሌማ ነበሩ። በትግራይ መስተዳድር ጋይ በርሄ፣ አረጋሽ አዳነ፣ ዓባይ ወልዱ፣ ሐሰን ሽፋና ገብሩ አሥራት፣ በኢሕአዴግ የድርጅትና ፕሮፓጋንዳ ሥራ ተወልደ ወልደ ማርያም፣ ዓለም ሰገድ ገብረ አምላክ፣ ሰለሞን ተስፋይ፣ አብርሃ ካሕሳይና ገብረ መስቀል ኃይሉ፣ በትእምት ስብሓት ነጋ፣ አባዲ ዘሙ፣ ቴዎድሮስ ሓጎስና አርከበ ዑቁባይ የማዕከላዊ ኮሚቴው አባላት ነበሩ።

ጋራ ባይሆንም የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ በየምድቡ ያኪያሄዳቸው ሂሶችና ግለ ሂሶች ጠነኛ ዐልፎ ዐልፎም ጠንከረ ያሉ ነበሩ። በተለይ በመከላከያ፣ በኢሕአዴግና በትግራይ ኮሚቴዎች ጠንከር ያሉ ሂሶችና ግለ ሂሶች ተኪያሂደው ነበር። ከሁሉም የከፋው ሂስና ግለ ሂስ የተኪያሄደው በመከላከያ ሲሆን ይህ ይበልጥ ያተኮረው በስዬና በጻድቃን ላይ ነበር። እርግጥ ቀደም ሲል በማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባችን መሠረታዊ የሆነ የሙስና ችግር የለም ብለን ብንስማማም ግምገማው ሌሎች መሠረታዊ ችግሮቻችንን እንዳናይ የሚከለክል አልነበረም። ይህ ሆኖም በአመራሩ በተደረጉት ግምገማዎችና ሂሶች የተነሡት ችግሮች መሠረታዊ ወይም ወሳኝ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮችና ተቋማዊ ግንባታዎች ላይ ያተኮሩ ሳይሆኑ ግለሰቦች ሥነ-ምግባርና ባሕርይ ላይ ብቻ ያነጣጠሩ ነበሩ። በኢሕአዴግ ጽሕፈት ቤትም ይሁን በትግራይ የተደረጉት ግምገማዎች፣ ሂሶችና ግለ ሂሶችም እንዲሁ በወሳኝ አገራዊ ጉዳዮች ላይ አላነጣጠሩም ነበር። እጅግ የሚገርመው ደግሞ የአገሪቱን አጠቃላይ ሕይወትና እድገት በሚመሩት የፌዴራል ተቋሞች በተሰማሩ እንደ መለስ ዜናዊ፣ ሥዩም መስፍንና ክንፈ ገብረ መድኅን ባሉት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ምንም ዓይነት ግምገማ፣ ሂስና ግለ ሂስ አለመኪያሄዱ ወይም የረባ ግምገማ አለመደረጉ ነው።

---

[17] በስብሰባው ተገኝቼ ካዳመጥኩት

በአጠቃላይ ድርጅቱ ከኤርትራ ጋራ የነበረውን ኢ-ፍትሐዊ ግንኙነት፣ የመንግሥት አወቃቀር ችግርን፣ መሠረታዊ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች ጥሰትን፣ ሥልጣን በግለሰቦች እጅ መከማቸቱን፣ የመሳሰሉ መሠረታዊ ችግሮች ሳያነሣ ሙስናንና የሥነ-ምግባር ጉድለት በተናጠል መመልከቱ የችግሩን ምንጭ ከሥሩ ለማድረቅ እንዳልፈለገ ያመለክት ነበር። በዚህ አጋጣሚ በቁንጽል ለተነሣው የሙስናና የሥነ- ምግባር ችግር ዋና ተጠያቂዎች የተባሉ ተራ ታጋዮችና መካከለኛ ካድሬዎች እየተጋለጡ ለተለያዩ ቅጣቶችና ለእስር ተዳርገዋል። በዚህ መሠረት በተለይ በአዲስ አበባ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ታጋዮች እንደታሰሩና እንደተጋለጡ ይታወቃል። ሂሱና ግለሂሱ እየጠነከረ ሲሄድም ችግሩ ከሙስናና ከሥነ-ምግባር አልፎ ድርጅትን ለማፍረስ የተደራጀ ሤራ ዐቅደዋል ወደሚል ወንጀል ተሸጋግሮ ነበር። ታጋዮች በጎቡእ ተደራጅተው ድርጅቱን ለማፍረስ እየተንቀሳቀሱ ነው፤ አመራሩን በማጥላላትና በማማት ከአባላቱ ጋ ለማጋጨት እየጣሩ ነው፤ በሚልም ታጋዮች እንዲጋለጡ ተደርጎ ብዙ ታጋዮች ድርጅት በማፍረስ ሤራ ተከሰው ዘብጥያ ወርደዋል። ይህ የማጋለጥ ሂደት ሁለት መሠረታዊ ችግሮች እንደነበሩት ማየቱ ይበጃል። አንደኛው ችግር ድርጅቱ ውስጥ በተደረገው ግምገማ ታጋዩን ዘብጥያ ማውረድ የሕግ ጥያቄ ማንሣቱ ነው። በድርጅቱ ሕገ ደንብ መሠረት ማንኛውም ግምገማ፣ ሂስና ግለ ሂስ ከድርጅት ለመባረር የሚያበቃ እንጂ ወህኒ የሚያስገባ አልነበረም። ይህ የፍርድ ቤትና የፖሊስ ጉዳይ መሆን ሲገባው ድርጅቱ ራሱ ፖሊስና ፍርድ ቤት ሆኖ አጥፍተዋል ባላቸው ታጋዮች ላይ የእስር ብይን ሰጥቷል። ምንም እንኳን ነጻ ፍርድ ቤትና ገለልተኛ ፖሊስ በሌሉበት ጉዳዩ በሚፈለገው አግባብ ሊፈጸም ባይችልም ትክክለኛውና ተገቢው አኪያሄድ ይኸው ሕግን የተከተለ መሆን ነበረበት።

ሁለተኛው ችግር ደግሞ በሙስናና በሥነ-ምግባር ጉድለት የተጀመረው እንቅስቃሴ ወደ ድርጅት ማፍረስ ሤራ መሸጋገሩ ነው። ይህ ህወሓቶች በጥያቄዎች ስንወጠር የምንከተለው ስልት እንደሆነ ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ድርጅታዊ ቀውስን በተመለከተ ገልጨዋለሁ። በአንድ ወቅት የሚከሰቱ ችግሮችን በማጠዝ ድርጅት ሊፈርስ ነው፤ ልንበታተን ነው፤ በማለት ተቃዋሚዎችን ማውገዝና መድፈቅ ህወሓት/ኢሕአዴግ የተካነበት ስልት ነው። በዚህ እንቅስቃሴ በአመራሩ ላይ አጠንጥኖ የነበረው ጉዳይ በመጨረሻ ዋናው ትኩረቱ በተራው ታጋይ ላይ መሆኑ ከፍተኛ ስሕተት ነበር። የታችኛው ታጋይ «*የህወሓት ዴሞክራሲ ሞዳ እንግሊዝ ሱሪ ዓይነት ነው*» ያለውም ለዚሁ ነበር። እንዳባባሉ የህወሓት ዴሞክራሲ ከላይ ሰፊ፣ ከታች ጠባብ በመሆኑ ታችኛውን ታጋይ ዐፍኖ ይዞ አመራሩን ዘና ያደርገዋል ለማለት ነበር።

9. የሽግግሩን መንግሥት ያቋቋሙት ድርጅቶች መበታተን

በኢትዮጵያ ከደርግ ውድቀት በኋላ በተቋቋመው የሽግግር መንግሥት የትኞቹ ድርጅቶች ታቅፈው እንደነበር ቀደም ሲል ገልጨዋለሁ። ከነዚህ ድርጅቶች መካከል ከኢሕአዴግ ቀጥሎ በሰው ኃይልና በአደረጃጀት ጠንካራ ሊባል የሚችለው አነግ ነበር። አነግ በትጥቅ ትግል ረጅም ጊዜ ያሳለፈ ከመሆኑም በተጨማሪ በአሮሞ ምሁራን የሚመራ ስለነበር በኢሕአዴግ ጥላ ሥር ከተሰባሰበው አሕዴድ ይበልጥ በአሮሞ ሕዝብ ተቀባይነት ነበረው። በሽግግሩ ወቅት የህወሓት አመራር አነግ ካሳደረበት ሥጋት የተነሣ ጠባብ ብሔረተኛ ብሎ ፈርጆት አሮሚያ ውስጥ ተቀበቃይነት እንዲያጣና በተናጠልም ይሁን ከሻዕብያ ጋራ በመተባበርም የትጥቅ ትግሉን እንዲያቋርጥ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አድረጓል።

ከፍተኛ ተቀባይነት ይኑሮው እንጂ አነግ ያራምደው የነበረው የፖለቲካ አቅጣጫ የተሳሳተ ነበር። የኦሮሞ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው በማለት ኦሮሞዎች የአሁኗን ኢትዮጵያ በመመሥረት ረገድ የነበራቸውን ቁልፍ ሚናና ከፍተኛ አስተዋፅኦ ለመሠረዝ ሞክሯል። ምዕራፍ አንድ እንደገለጽኩት ኦሮሞዎች በተለይ ከአሰራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የኢትዮጵያ ታሪክ ከፍተኛ ቦታ እንደነበራቸው ኦሮሞዎች ራሳቸውም ይሁኑ ሌሎች ኢትዮጵያውያን የጻፉት ታሪክ ይመሰክራል። ኦሮሞዎች በምዕራብ ኢትዮጵያ ዳሞትንና ኢናርያን ሲቆጠጣጠሩ በመሻልና በሰሜን ኢትዮጵያ ደግሞ እስከ ትግራይ የሚዘልቅ ሰፊ አካባቢ ተቆጣጥረው ነበር። ይህን ታሪክ ከዘገቡት አንዱ ዶክተር ላጵሶ ጌ· ድሌቦ፣ «*የሶዶ.....ወዘተ ኦሮሞ ጎሳዎች በሰሜኑ ደጋ ከትግራይ፣ ከላስታና ከበጌምድር በመለስ፣ በምዕራብ ደግሞ ከዓባይ-ጎጃም በመለስ፣ በምሰራቅ በደቡብ፣ በመሀልና በመሀል-ምዕራብ በቅድሞ የሀድያ-ሲዳማ .... የጋፋትና የእናርያ አገሮችና ሕዝቦች ላይ እንዴት በነዋሪነት እየሰፈሩ አዲስ የእርሻ ሥራና ባህል እንደጀመሩ ብሎም ጥንታዊ የገዳ ሥርዓታቸው በአዲስ አካባቢና የኦሮ ሁኔታ ማለትም በሥርዓታዊ ዕድገትና ለውጥ መፍረስ እንደጀመረ*»[18] ብለው ይዘግባሉ። ይህ እንቅስቃሴ በተከሰተበት ሁሉ ኦሮሞው በአካባቢው ከነበረው ሕዝብ ጋር እየተዋሐደ ዐልፎ ዐልፎም ሳይደባለቅ ራሱን ችሎ የኦሮሞ ቋንቋና ባህል እንዲስፋፋ አድርጓል። ይህ የኦሮሞዎች የአጭር ጊዜ ታሪክ በኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ ያሳደሩ ባሻገር የኦሮሞ ሕዝብን አሰፋፈር ለውጦታል።

ይህ ሆኖ ሳለ የኦሮሞዎችንና የሌላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ግንኙነት ወደ አንድ መቶ ዓመት ዝቅ አድርጎ ከአጼ ምኒልክ መስፋፋትና «ቅኝ ገዥነት» ጋራ ማያያዙ ትክክል አይደለም። በእርግጥ ኦሮሞዎች የነበራቸው ኃይል ተዳክሞ በአገሪቱ ላይ የነበራቸው ተጽዕኖ ቀነሰበት ወቅት የኃይል ሚዛኑ ተለውጦ መንግሥት ተቆጣጥረው የነበሩት የኢትዮጵያ ነገሥታትና ገዥዎች በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ምዝበራና ጭቆና ማድረሳቸው በታሪክ ተዘግቧል። የኦሮሞን መሬት በቀላድና በጉልት ተቀራምተው እንደዘረፉ፣ ኦሮሞውን በገዛ አገሩ መሬት አልባ አድርገው ወሳኙን ሀብት ነጥቀውት ለድኽነትና ለችግር እንደዳረጉት፣ ሀብቱን ለመቆጣጠር ባደረጉት እንቅስቃሴም ከፍተኛ ግድያ፣ ድብደባና እስር እንዳወረዱበት ጥርጣሬ የለውም። እንዲህ ዓይነቱ ምዝበራና የፖለቲካ ጭቆና በከፍተኛ ደረጃ የተፈጸመው በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ቢሆንም ከዚያ በኋላም በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ በደል ደርሷል። የኦሮሞ ልጆች ትጥቅ አንግበው ለመታገል የተነሡትም ይህ ጭቆናና ምዝበራ አንገሽግሿቸው ነው። ሆኖም ግን፣ በኦሮሞዎች የደረሰው ጭቆናና ምዝበራ ከሞላ ጎደል በሌሎችም የኢትዮጵያ ሕዝቦችም ላይም ደርሷል። በደቡብ ኢትዮጵያ የሚኖሩ ወርካታ ብሔር ብሔረሰቦችና በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦች ከኦሮሞው የማያንስ በደል ደርሶባቸዋል። በብሔር ጭቆና መልክ ባይከሰትም የነገሥታቱ ገዥዎች የትውልድ ስፍራ ነው የሚባለው የሰሜን ሸዋ አካባቢ እንኳን ከከፋ ጭቆናና ምዝበራ አላመለጠም። ይህ በገዥዎች የደረሰውና አሁንም በመድረስ ላይ ያለው ጭቆናና ምዝበራ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የጋራ ችግር እንጂ የኦሮሞዎች የብቻ አይደለም። ካለፈው ታሪክ የምንወስደው ትምህርት መጥፎ ገጽታው እንዳይደገም መልካሙ ደግሞ እንዲቀጥል እንጂ ቂም ይዘን እርስ በእርስ የምንጠፋፋበት ሁኔታ እንዲፈጠር መሆን የለበትም።

አነግ በኦሮሞ ሕዝብ የደረሰውን ጭቆና ለማስወገድ ዓመታት የፈጀ የትጥቅ ትግል ካካሂደ በኋላ በሽግግሩ ቻርተር በሰፈረው ሐሳብ ተስማምቶ የሽግግሩ መንግሥት መሥራች መሆኑ ይታወሳል። በወቅቱ በሽግግሩ ቻርተር የሰፈረው የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከ

---

[18] ላጲሶ ዴሌቦ/ዶክተር/፣ 1982 ዓ.ም.፣ *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ*፣ አንደኛ መጽሐፍ፣ አዲስ አበባ፣ 1982፣ ገጽ 160

መግንጠልን የሚደነግገው አንቀጽ ለኦሮሞ ሕዝብ ችግር መፍትሔ ይሆናል የሚል እምነት ነበረው። የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ነው ቢልም በሕዝበ ውሳኔ በአንድነት ወይም በመገንጠል ማዕቀፍ ይፈታል ብሎም በሽግግር መንግሥት ተሳትፎ ነበር። የሽግግር መንግሥንቱ አጭር ዕድሜ እንደሚኖረው የተገነዘበው አነግ ዋናው ጨዋታ ከሽግግሩ በኋላ በሚመሠረተው መንግሥት የሚኖረው ቦታ እንደሆነ ያውቅ ነበር። በመሆኑም አነግ በሽግግሩ ጊዜ ከፍተኛ ድርጅታዊ ሥራ በማኪያሄድ ከተቻለ በአገሪቱ በአጠቃላይ ካልሆነም በኦሮሚያ የበላይነቱን ለማረጋገጥ ተንቀሳቅሶ ነበር። ከፍተኛ ትኩረቱ የነበረውም ሠራዊቱን በመገንባትና የአባላቱን ቁጥር በማጠናከር ላይ ነበር። አነግ እነዚህ ሁለት የድርጅቱ ክንፎች ላይ ማትኮር ኋላ ላይ ለሚኖረው የሥልጣን ክፍፍል ጠቃሚ እንደሚሆን ተገንዝቦ ነበር። በተለይ ሠራዊቱን በማጠናከር ረገድ በርካታ የቀድሞ የደርግ ወታደሮችን መልምሎ ከአስኳል ጦሩ ጋር እንዲቀላቀሉ አድርጎ ግዙፍ ሠራዊት ለመፍጠር ሞክሮ ነበር። አነግ በትጥቅ ትግሉ ወቅት የነበረው የሠራዊት ብዛት በምሥራቁ ግንባር 1,500፣ በምዕራቡ ግንባር ደግሞ 3,000 ሲሆን፣ በጠቅላላ 4,500 የሚገመት ነበር። በሽግግሩ ጊዜ ግን የአነግ ሠራዊት በምሥራቁ ግንባር ከ7,500 እስከ 8,000 በምዕራቡ ግንባር ደግሞ ከ10,000 እስከ 12,000 ደርሶ በጠቅላላ ከ20,000 በላይ ሆኖ ነበር[19]።

ከላይ የተጠቀሰውን የአነግ እንቅስቃሴ ኢሕአዴጎች በዓይነ ቁራኛ እንመለከተው ነበር። አነግ ሠራዊቱን ባሰፈረባቸው ቦታዎች ሁሉ ይዞታውን ለማጠናከርና የኢሕአዴግ አባል ከሆነው አሕዴድ በልጦ ለመገኘት አበክሮ በመሥራት በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሮ ነበር። በአንዳንድ አካባቢዎችም ድጋፍ ለማግኘት ከነበረው ጉጉት የተነሣ ግፍም ፈጽሟል። በተለይ በምሥራቅ ኦሮሚያ ሐረር አካባቢ በወተር፣ በበደኖና በሌሎች አካባቢዎች የተፈጸመው ግፍ አሰቃቂ ነበር። ግፉም ኢሕአዴግ በአነግ ላይ ሊወስደው ለፈለገው እርምጃ ምክንያት ሆኖለታል። በወቅቱ በአነግ ስለተፈጸመው ግፍ የኦሕዴድና የኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚ አባል የነበረው ዶክተር ነጋሶ ጊዳዴ የሚከተለውን ይላል፤ «*ሁኔታው እስከ መስመሩ የሳተ ነበር። የኦሀዴድ ሴት ታጋዮች ጡት ይቆረጥ ነበር። ወንዶች ደግሞ የጭናቸው ስጋ እየተቆረጠ ብሉት ይባል ነበር። በተለይ በበደኖ ጉዳይ ላይ የአነግ አመራር የዚህ ዓይነት ድርጊት እንዲፈጸም ትዕዛዝ ባይሰጥም ድርጊቱ የተፈጸመው በአነግ ወታደሮች መሆኑን አቶ አባ ቢያ አባ ጆቢር በፓርላማ አምኖ ነበር። በጣም መጥፎ አመለካከት የሚያራምዱ የአነግ ታጋዮችም ነበሩ።*»[20] ይህን ግፍ በተደጋጋሚ በቴሌቪዥን በማሳየት ኢሕአዴግ አነግን ከሕዝቡ ለመነጠል ሞክሯል። ኢሕአዴግ ዋነኛውን ሥልጣን ስለተቆጣጠረ አነግን በከፍተኛ ደረጃ ለማጥላላትና ለመነጠል ቻለ እንጂ ራሱም ቢሆን ከስሕተት ነጻ እንዳልሆነ ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ በመጽሐፉ ሲገልጽ፣ «*በኦሕዴድ ታጋዮች በኩልም መጥፎ ድርጊቶች የሚፈጽሙ ሰውም የሚገድሉ እንደነበሩ ሪፖርቶች ይቀርቡ ነበር።*»[21] በመቀጠልም «*ኢሕአዴግ ልክ አሁን በተቃዋሚዎች ላይ የሚጠቀመውን ዓይነት ዘመቻ ነበር በአነግ ላይ የተጠቀመው «አነግ የነዳነት አጀንዳውን ተግባራዊ ያደርጋል፤ ኢትዮጵያን ይገነጣጥላል፤ በማለት የምዕራባውያን ሃገሮችን ልብ መማረክ ችሏል።*»[22] በመሆኑም አነግ ዓላማውን ለማሳካት ያከማቸውን ኃይል ተጠቅሞ የበላይነቱን ሳያሳካ በኢሕአዴግ ስልት ተጨናገፈ።

---

19 የኦሮሞ ነጻ አውጪ ግንባር /አነግ/ አጠቃላይ ሁኔታ ከትላንት እስከ ዛሬ፣ ግንቦት 1985 ዓ.ም. የቀረበ የጥናት ሪፖርት፣ ገጽ 40 እና ገጽ 93፣ በዚህ ሪፖርት መሠረት ምሥራቅ ግንባር የሚባለው ሐረርጌን ማዕከል ያደረገው ምሥራቁ የኦሮም ክፍል ሲሆን፣ ምዕራብ ግንባር የሚባለው ደግሞ ወለጋን ማዕከል ያደረገው ምዕራቡ ይኦሮሞ ክፍል ነው። ከዚህ ሌላ ባሌ፣ አሩሲንና ቦረናን ያካተተው ደቡብ ግንባር ያን ያህል በሠራዊት የተጠናከረ አልነበረም፤ ዋናው ኃይሉም ሚሊሺያው ነበር።

20 ዳንኤል ተፈራ፣ 2003 ዓ.ም.፣ *ዳንዲ፣ የነጋሶ መንገድ*፣ የመጀመሪያው ኅትም ሰኔ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ ገጽ 150

21 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 150

22 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 152

አነግ በአንድ በኩል ወታደራዊና ፖለቲካዊ ይዞታውን በማጠናከር ኃያልነቱን ለማረጋገጥ እየሞከረ በሌላ በኩል ደግሞ በሽግግር መንግሥቱ ያለውን ቦታ በማጠናከር በማዕከላዊው መንግሥት ያለውን ሥልጣን ከኢሕአዴግ እኩል ለማድረግ ሞክሯል። አነግ በሽግግሩ መንግሥት የግብርና፣ የትምህርትና የማስታወቅያ ሚኒስቴር ፖርትፎልዮዎችን ቢይዝም ከነበረው ኃይል ሚዛን አንጻር ይህ በቂ እንዳልሆነ ተገንዝቦ ወሳኝ በተባሉ የመንግሥት ተቋማት ተጨማሪ ቦታ እንዲሰጠው ጠይቆ ነበር። ያኔ ወሳኝ የሚባሉት የሚኒስቴር ቦታዎች ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትርነት፣ የማስፈጸም ሥልጣን የነበረው ፕሬዚዳንትነት፣ የአገር ውስጥ ሚኒስትርነት፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነትና የመከላከያ ሚኒስትርነት ነበሩ። አነግ ከተጠቀሱት የሚኒስቴር ተቋማት መካከል የተወሰኑት እንዲሰጡት መጠየቁ ከፍትሐዊ የሥልጣን ክፍፍል አንጻር ተገቢ ቢሆንም ጥያቄው ገና የሥልጣን መሠረቱን ባላደላደለውና ከአነግ ጋ ስልታዊ ግንኙነት ብቻ ነበረን በሚለው በኢሕአዴግ ተቀባይነት አልነበረውም። ኢሕአዴግ በነበረው ስትራቴጂ አነግን በሽግግሩ መንግሥት ያሳተፈው ወአገሪቱ መረጋጋት ለመፍጠርና የሚመሠረተው መንግሥት ሁሉም የኦሮሞ ድርጅቶች እንደሚሳተፉበት ለማመልከት እንጂ ከአነግ ጋራ አብሮ በዘላቂነት ለመሥራት አልነበረም። ሲከተለው የነበረው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮተ ዓለም የአንድ ፓርቲን የበላይነት እውን የሚያደርግ እንጂ የብዙኃንን ውድድር የሚቀበል ስላልነበር ከአነግ ጋራ መፋታቱ አይቀርም ነበር።

አነግ በሽግግሩ መንግሥት የነበረው ዝቅተኛ የሥልጣን ድርሻ በርካታ አባላቱንና ደጋፊዎቹን አስቆጥቶ ነበር። ሥልጣንን በመከፋፈል ረገድ መሠረታዊ ጥያቄዎችን ያነሣውም ከዚህ የተነሣ ሊሆን ይችላል። አነግ ከሥልጣን ክፍፍሉ ባሻገር በሕዝቡ ስለሚኖረው ገጽታም ያስብ የነበር ይመስላል። ነገሩን በቀጥታ ባልሰማውም ካሉት ሁለት ዜተ መንግሥቶች ማለትም ከአጼ ምኒልክና ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ቤተ መንግሥቶች አንዱ እንዲሰጠው ጠይቆ ነበር ይባላል። ጥያቄው ላይ ላዩን ሲያዩት ትርጉም አልባ ቢመስልም ወገጽታ ግንባታ ረገድ ግን ትልቅ ትርጉም ነበረው። የአገራችን ሰው ቤተ መንግሥትን እንደ ትልቅ የሥልጣን መገለጫ ስለሚያየው ይህን መቆጣጠር ከካድሬ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ የበለጠ ፋይዳ እንዳለው ተገንዝበው ያቀረቡት ጥያቄ ይመስላል። የሆነው ሆኖ በዚህም ላይ ከኢሕአዴግ ጋር ስምምነት ላይ ሊደርሱ አልቻሉም። ኢሕአዴግ የአነግን አዝማምያ ካስተዋለ በኋላ ድርጅቱን ከሥሩ የሚነቅልበትን ሁኔታ ያመቻች ነበር። በሽግግሩ ወቅት የደኅንነት ኃላፊ የነበረው ክንፉ ገብረ መድኅን የአነግን ወታደራዊ ይዞታ፣ የሠራዊቱን ደካማና ጠንካራ ጎኖች፣ የአባላቱን ሁኔታና ፖለቲካዊ አቋሞች እንዲሁም ውስጣዊ ቅራኔዎቹን በተመለከተ አንድ ሰፊ ጥናት ለኢሕአዴግ አመራር እንዲያቀርብ የተደረገውም ለዚሁ ነበር[23]።

አነግ በሽግግሩ መንግሥትም ይሁን ከዚያ ባሻገር ስለሚኖረው የሥልጣን ክፍፍል ተስፋ የሚሰጥ ነገር ስላላየ የኢሕአዴግ አጃቢ ሆኖ ለመቀጠል አልፈለገም ነበር። በመሆኑም የነበሩትን የመንግሥት ኃላፊነቶች በሙሉ ትቶ ከሽግግሩ መንግሥቱ ወጣ። ከአነግ ሌላም ወአቶ ወልደ አማኑኤል ዱባለ ይመራ የነበረው ሲአን፣ በአቶ አሰፋ ጫቦ ይመራ የነበረው ኦሕነኮ፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት /ኢዴኃቅ/፣ መላው አማራ ሕዝብ ድርጅት /መአሕድ/፣ የመሳሰሉት የሽግግር መንግሥቱን ጥለው ወጡ። አነግና እነዚህ ድርጅቶች ከሽግግር መንግሥቱ ቢወጡም ሌሎች አጋሮች ማለትም የደቡብ፣ የሶማልያ፣ የኦሮሞ፣ የአፋር፣ የቤንሻንጉልና የጋምቤላ ድርጅቶች በመንግሥቱ ውስጥ ተካተው ስለነበር

---

[23] ዝኒ ከማሁ፣ የኦሮሞ ነጻ አውጪ ግንባር /አነግ/ አጠቃላይ ሁኔታ ከትላንት እስከ ዛሬ፣ 206 ገጾች ያሉት አነግን የተመለከተ ጥናታዊ ሪፖርት

ስለአገራዊው ገጽታችን እምብዛም አልተጨነቅንም ነበር። እንዲያውም ከአነግ ጋራ የተፈጠረው አለመግባባት የአነግን ሠራዊት ለመምታት ምቹ ሁኔታ ፈጥሮልን ነበር። አነግም በዚህ ድርጊት ተበሳጭቶ አገር ጥሎ እስከመሄድ ደርሶ፣ አብዛኛዎቹ ከፍተኛ አመራሮቹ ኑሯቸውን ዳግም በውጭ አገር በስደት ለማድረግ ተገደዱ። የአነግ ከሽግግሩ መንግሥት መውጣትና ኢሕአዴግ ብቻውን የፖለቲካ ሜዳውን መቆጣጠሩ ለኢሕአዴግ አገዛዝ የተመቸ ነበር። ያኔ በኢትዮጵያ የነበረው የፖለቲካ ምኅዳር እጅግ ጠባብ እንደነበር የሚያጠያይቅ አይደለም። የሽግግሩን መንግሥት ለቆ መውጣቱ ለአነግ የነበረውን ፋይዳ ራሱ አነግ ሊገመግመው ቢገባም በኢትዮጵያ ፈጥሮት የነበረው የፖለቲካ ተጽዕኖ እንደተጓደለበት ግን ግልጽ ነው።

10. የሻዕብያ ዝርፊያና ግድያ

ሻዕብያ በደርግ ውድቀት ማግስት የጠራው ኮንፈረንስና በዚያ ኮንፈረንስ የተቀየሰውን ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያኪያሂድ ነበር። ከነዚህ እንቅስቃሴዎቹ አንዱ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የተለያዩ ስምምነቶችን ማድረግ ነበር። ለዚህ ሲባልም በ1985 ዓ.ም. ስምምነቶችን የሚነድፉና ተግባራዊ የሚያደርጉ ከሁለቱ መንግሥታት የተውጣጡ የጋራ ኮሚቴዎች ተመሠረቱ። ከነዚህ ኮሚቴዎች አንዱ ከፍተኛው የጋራ ሚኒስትሮች ኮሚቴ የሚባለው ሲሆን ኮሚቴው በኢትዮጵያ በኩል በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር በነበረው ታምራት ላይኔና በኤርትራ በኩል ደግሞ የሻዕብያ ሁለተኛ ሰው በነበረው መሐመድ ሸሪፎ የሚመራ ነበር። በዚህ ከፍተኛ የጋራ ኮሚቴ ሥርም የመገናኛና ትራንስፖርት፣ የፋይናንስ፣ የንግድ፣ የመከላከያና የጸጥታ ንኡሳን ኮሚቴዎች ተቋቁመው ነበር። እነዚህ ኮሚቴዎች በሁለቱ አገሮች መካከል የሚደረጉትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነቶች ለማዋሐድና *(to harmonize)* ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመፍታት የተቋቋሙ ነበሩ።

የተቋቋሙት ኮሚቴዎች የተለያዩ ስምምነቶችን ነድፈው ተግባራዊ ለማድረግ ቢሞክሩም ሂደቱ ጭራሽ ፈቅ ሊል አልቻለም ነበር። የሻዕብያዎች ዕቅድ ከተቻላቸው በሚነደፉት ስምምነቶችና በሚቋቋሙት ኮሚቴዎች አማካይነት ዝርፊያ ለማኪያሄድ ይህ ካልተሳካ ደግሞ ሌላ ዘዴ በማበጀት ጥቅማቸውን ለማራመድ ነበር። ሆኖም በነዚህ ኮሚቴዎች አማካይነት ሻዕብያዎች በሚፈልጉት ደረጃ ዝርፊያ የሚያኪያሂዱበት ሁኔታ ሊመቻችላቸው አልቻለም ነበር። እንዲያውም በኢትዮጵያ መንግሥት የተወከሉት የኮሚቴ አባላት የሻዕብያን የዝርፊያ ሜሪ በሚገባ ስለተገነዘቡ ሙከራዎቻቸውን ሁሉ ለማክሸፍ የተቻላቸውን ማድረግ ጀምረው ነበር። ሻዕብያዎች እነዚህ ኮሚቴዎች በኢሳያስ አፈወርቂና በመለስ ዜናዊ የቅርብ አመራር ሰጭነት ስለሚንቀሳቀሱ የተባሉትን ሁሉ ያስፈጽማሉ ብለው አስበው ነበር። ሆኖም በኢትዮጵያ በኩል የተወከሉት የኮሚቴ አባላት በአገሪቱ ፖሊሲና ሕግ መሠረት እንጂ በበላይ ትእዛዝ ስላልተንቀሳቀሱ ሻዕብያዎች ደስተኞች አልነበሩም። በተለይ ከኮሚቴ አባላቱ መካከል የትራንስፖርትና መገናኛ ምክትል ሚኒስትር የነበረውን ሚቹን አቶ አየነው ቢተውልኝን ክፉኛ ጠምደውት ነበር። ታምራት ላይኔንም አልወደዱትም ነበር። በሻዕብያዎች የፖለቲካ አሠራር ጥቅማችንን ያንድላል፤ የኛ መሣሪያ ሊሆን አይችልም፤ የሚሉትን ሰው ስም ማጥፋትና ማጥላላት የተለመደ ነበር። ስለዚህ ሻዕብያዎች የአንድን ሰው ስም ማጥፋት ሲጀምሩ ያ ሰው ጥቅማቸውን እንደሚጻረር መገንዘብ ይቻል ነበር። ያም ሆነ ይህ ሻዕብያዎች በአብዛኛዎቹ የኮሚቴ አባላት በተለይ ደግሞ በአቶ አየነው ቢተውልኝ ላይ ከፍተኛ የስም የማጥፋት ዘመቻ ጀምረው ነበር።

ሻዕብያዎች በሕግ በተቋቋመው የሚኒስትሮች ኮሚቴ አማካይነት ከፍተኛ ዝርፊያ ሊያከናውኑ ስላልቻሉ ከዚህ ጎን ለጎን ሌላ እንቅስቃሴ ጀመሩ። በአንድ በኩል ከመለስ ጋር በቀጥታ በመገናኘት ፍላጎታቸውን ሲያሰፈጽሙ በሌላ በኩል ደግሞ በትግራይና በአፋር ቆንስላዎችን አቋቁመው የዝርፊያ ስትራቴጂያቸውን ማስፈጸም ነበር። በሻዕብያዎች በኩል ከመለስ ጋራ የሞቀ ግንኙነት መፍጠር ለስትራቴጂያቸው እጅግ ወሳኝ ነበር። ይህን ግንኙነታቸውንም ተጠቅመውም ከፍተኛ የኢትዮጵያ ሀብት ሊዘርፉ ችለዋል። እስከአሁን የማናውቃቸውን የሻዕብያ ዝርፊያዎች ትተን ከህወሓት ክፍፍል በኋላ ይፋ የሆነውን በመለስ ትእዛዝ በብሔራዊ ባንክ አስፈጻሚነት ከኢትዮጵያ ግምጃ ቤት ወጥቶ ለሻዕብያ የተሰጠውን 1.2 ቢለዮን ብር መጥቀስ ይቻላል[24]። ይህ ገንዘብ ሻዕብያዎች ከመለስ ጋራ በነበራቸው ግንኙነት እንጂ በመንግሥትም ይሁን በፓርቲ በተቋቋሙት መዋቅሮች ውሳኔ እንዳልተሰጣቸው ግልጽ ነው። ጉዳዩ በኢሕአዴግ ምክር ቤትም ይሁን በአገሪቱ መንግሥት ምክር ቤት፣ በፖሊትቢሮውም ይሁን በሚኒስትሮች ምክር ቤትም የሚታወቅ አልነበረም። ሻዕብያዎች እንዲቀጥል የፈለጉትም የዚህ ዓይነቱን የማፊያና የውንብድና አኪያሄድ ነበር።

የሻዕብያዎች ሌላው የዝርፊያ ዘዴም በአዲስ አበባ ባቋቋሙት ኤምባሲ ሥር በትግራይ ክልል በመቀሌ ከተማና በአፋር ክልል በአሳይታ ከተማ በሚንቀሳቀሱት ሁለት ቆንስላዎቻቸው አማካይነት ማኪያሄድ ነበር። የኤምባሲውና የነዚህ ቆንስላዎች ዋና ዓላማ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የኤርትራን ጥቅም ማስጠበቅ ነበር። በመሆኑም የአዲስ አበባ ኤምባሲያቸው የውጭ ምንዛሪ በመመንዘር በኢትዮጵያ የኤርትራ ብሔራዊ ባንክን ሚና ሲጫወት፣ ከኬንያ እስከ ኤርትራ የሚኪያሄደውን የሻዕብያዎችን የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴም ይመራ ነበር። ከዚህ ኢኮኖሚያዊ ውንብድና በተጨማሪ ሻዕብያን ይቃወማሉ የተባሉትን ግለሰቦችና ቡድኖችን እያደነና እያፈነ ይገድላል። በዚህ መልክ ሻዕብያ በስመ ዲፕሎማሲ ብዛት ያላቸውን የማፊያ መሰል ቡድኖች በማሰማራት በኢትዮጵያ ከፍተኛ ደባ ይፈጽም ነበር።

ወኅልሎቹ የተቋቋሙት ቆንስላዎችም ተልዕኳቸው ተመሳሳይ ነበር። ኤርትራን በቡና ላኪነት እንድትታወቅ ያደረጋትን የኮንትሮባንድ ሥራ የመሩትና ያከናወኑት እነዚህ ቆንስላዎች ነበሩ። ሌሎች ኤርትራውያንም ከኢትዮጵያ እየተዘረፉ ወደ ውጭ የሚላኩ ውድ ሽቀጦችን በማስተላለፍና ከውጭ በርካሽ የሚያስገቧቸው ሽቀጦች ሳይቀረጡ ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት አስፈጻሚዎች ነበሩ። ከዚህ ሌላም በሻዕብያ የሚፈለጉትንና የተፈረደባቸውን ኤርትራውያን በማፈን፣ በመግደልና በመሰወር ተስማርተው ነበር። በአዲስ አበባ ኃይለ መርቆርዮስ በአምባሳደርነት ሲመደብ ከሥሩ በኮማንዶና በማፊያ ሥራቸው የሚታወቁት እነ ወዲ በርሀ ተመድበው ነበር። በመቀሌው ቆንስላ ጽሕፈት ቤትም ዱሮ የጀብሃ ኮማንዶ የነበረውና ኋላ ላይ ሻዕብያን የተቀላቀሰው ጄኔራል አብርሃለይ ክፍለ ቆንስሉን ሲመራ በእርሱ ሥር ደግሞ እንደነ ንዋቱና ኢያሱ /ወዲ ሃለቃ/ የመሳሰሉ ተመድበው ነበር።

ይህ ከኤምባሲ እስከ ቆንስላ የተዋቀረው የዝርፊያ፣ የዐፈናና የግድያ ቡድን በአገራችን ያልፈጸመው ወንጀል የለም። ለአብነት እኔ የማውቃቸውን የተወሰኑ ወንጀሎች ብጠቅስ ጠቋሚ ይሆናል ብዬ ከዚህ በታች እዘረዝራለኹ፤

1ኛ/ *በኮንትሮባንድ ሊወጣ ሲል የተያዘው ሰሊጥ*፣ ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ ሻዕብያዎች በሑመራ በኩል የሰሊጥ ንግድ ያኪያሂዱ ነበር። ይህን የሰሊጥ ንግድ ሲያኪያሂዱ ግዢው የአካባቢውን ነጋዴዎች አሰማርተው ሲያከናውኑ ሰሊጡን ከአገር ለማስወጣት

[24] *ሪፖርተርና* ሌሎች በወቅቱ የታተሙ የግል ጋዜጦች እንደዘገቡት

ደግሞ ከፌዴራልና ከክልል ባለሥልጣናት ጋራ ይመሳጠሩ ነበር። በከፍተኛ የሰሊጥ ምርት የምትታወቀውን የሑመራን ከተማ ከኤርትራ የሚያዋስናት ተከዜ ወንዝ ብቻ በመሆኑ ኤርትራውያኑ የገዙትን ሰሊጥ ከባለሥልጣናቱጋ በመመሳጠር ከሑመራ ጥቂት ሜትር ተጉዘው ተከዜን ተሻግረው ወደ ኤርትራ መሬት ያስገቡት ነበር። ሻዕብያዎች ይህን መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ ተጠቅመው የኢትዮጵያን ሀብት ያላግባብ ወደ አገራቸው ለሁለት ዓመታት ያህል ካሻገሩ በኋላ በሦስተኛው ዓመት ሑመራ ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ደባ እየፈጸሙ እንደሆነ ከአገር ወዳዶች ለክልሉ መንግሥት መረጃ ደረሰ። ይህን መረጃ ያገኘነው የክልሉ አመራር አባላት ተግባራቸውን መቅጨት እንዳለብን ተስማምተን ለአንድ ዓመት የሰሊጥ ምርት ግዢው ሲያኪያሂዱ በቅርበት ተከታተልናቸው። በዚህ ክትትላችንም ሻዕብያዎች የሰሊጡን ምርት ሕጋዊ ሽፋን ሰጥተው የሚያስወጡት ባሕር ዳር የነበሩትን የፌዴራል ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች በጉቦ በመደለልና እዚያ ይሠሩ የነበሩትን ኤርትራውያን በመጠቀም እንደሆነ ደረስንበት።

ሻዕብያዎች እንደልማዳቸው በባሕር ዳርና በአዲስ አበባ በነበሩ ከአራት ከማያንሱ የፌዴራል መሥሪያ ቤቶች ጋር ተመሳጥረው ሰሊጡን የሚያስወጡበትን ዘዴ ሲወጥኑ የብሔራዊ ባንክ፣ የጥራትና የደረጃ መዳቢና ጉምሩክን የመሳሰሉት የፌዴራል ውጭ ንግድ ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤቶች ትግራይ ውስጥ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንዳሏቸው አጥተውት ሳይሆን ከክልሉ ዕይታ ለመራቅ ነበር። በመሆኑም ሑመራ የነበረው የሻዕብያዎች ወኪል ከጥራትና ደረጃዎች መዳቢ ባለሥልጣን ድርጅት ሰሊጡ ጥራቱ የተመሰከረ ለመሆኑ ፈቃድ ሲያገኝ ከብሔራዊ ባንክም በትክክለኛ ዋጋ መግኘቱን የሚያረጋግጥ ፈቃድ ሲሰጠው ከጉምሩክም የይለፍ ወረቀት አገኘ። ይህ ሁሉ ሲሆን እያንዳንዱን የሻዕብያዎች እርምጃ እንከታተል ነበር። በመጨረሻ ሻዕብያዎች ሠላሳ ስምንት መኪኖች ከነተሳቢዎቻቸው ሰሊጥ አስጭነው ከሑመራ ወደ ኤርትራ ማንቀሳቀስ ጀመሩ። በዚህ ጊዜ የትግራይ ጉምሩክና የጸጥታ ኃይሎች በቁጥጥር ሥር አዋሏቸው። ሻዕብያዎችም ሕጋዊ ፈቃድ ስላለን መያዘ የለብንም ብለው ሲያንገራግሩ ፈቃዳቸውን እንዲያሳዩ ሲጠየቁም ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ከባሕር ዳርና ከኢዲስ አበባ ያገኙትን ሰነድ አቀረቡ። ሑመራ ላይ ምንም ዓይነት የሰሊጥ ማጣሪያ መሣሪያ ሳይኖር የጥራትና ደረጃ መዳቢዎች ባለሥልጣን እንዴት ፈቃድ ሰጣቹሁ ሲባሉም መልስ አልነበራቸውም። በነገራችን ላይ ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች የሰሊጥ ምርት ወደ ውጭ ለመላክ የግዴታ ሰሊጡን ከአንድ ሺሕ ኪሎ ሜትር በላይ አጓጉዘው ናዝሬት ላይ በነበረው ብቸኛ ማጣሪያ ማለፍ ነበረባቸው። የሻዕብያዎች ተግባር ሕጋዊ አለመሆኑን አረጋግጠን ሊያሸሹት የነበሩትን ሠላሳ ስምንት ሚልዮን ብር የሚያወጣ ሰሊጥ እንዲወረስ አደረግን።

ይህን ዜና የሰማው ኢሳያስ አፈወርቂ ኢትዮጵያ ውስጥ በነበሩ ወዳጆቹ አማላጅነት ሰሊጡ እንዲለቀቅለት ተማጸነ። ትግራይ ውስጥ ወደ ነበርነው የአስተዳደር አባላትም ወዲ በርሀ ተልኮ የተወሰነ ስሕተት ቢደረግም ወዳጅነታችንን ዐይታችሁ ሰሊጡን እንድትለቁልን ኢሳያስ ልኮናል አለን። ማንም ቢልካቸው ጉዳያችን ስላልነበር ሕጉን በጣሱ ኢትዮጵያውያን ላይ የምንወስደውን እርምጃ በኤርትራውያን ላይ ባንወስድ ትክክል አይሆንም ብለን ለአማላጆቹ ነግረናቸው ሸኝናቸው።

2ኛ/ *ያልተቀረጠው የሻዕብያ ውስኪ ስለመወረሱ*፣ ሻዕብያዎች ሳያስቀርጡ ወደ ኢትዮጵያ ከሚያገቧቸው ሸቀጦች አንዱ ዊስኪ ሲሆን ዊስኪውን አመቺ መስሎ በሚታያቸው ኬላ በኩል ያስገቡት ነበር። አንዳንዴ ከኬላ ጠባቂዎችና ከጉምሩክ ኃላፊዎች ጋራ

በመመሳጠር ውስኪውን ሲያስገቡ አንዳንዴ ግን አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ደባቸውን ያከሽፉባቸው ነበር። ሻዕብያዎች አንድ መኪና ጭነት ዊስኪ ከኬላው ኃላፊዎችና ከጉምሩክ ሠራተኞችጋ ተመሳጥረው በራማ በኩል ወደ መቀሌ እንዳስገቡ የትግራይ መስተዳድር መረጃ ሲደርሰው መቀሌ ላይ አሰሳ አድርጎ ከአንድ ሚልዮን ብር በላይ የሚያወጣ ዊስኪ በአቶ ኃይለ ጓንጉል የከብት ርቢ ማዕከል ውስጥ ተገኘ[25]። ዊስኪውም ልክ ሑመራ ላይ እንደተወረሰው ሰሊጥ ቢወረስም ሻዕብያዎች የተጭበረበረ የይለፍ ፈቃድ ስላልነበራቸው ብዙም ሳያንገራግሩ ጉዳዩን ውጠውት ዝም አሉ።

3ኛ/ *ቡናን ከመኻል አገር የማስወጣት እንቅስቃሴ*፣ አሁንም በተጭበረበሩ ሰነዶችና ከኬላ ጠባቂዎች ጋራ በመመሳጠር ሻዕብያ በከፍተኛ ደረጃ ቡና በመዝረፍ እንቅስቃሴ ተሰማርቶ ነበር። በዚህ ረገድ ሻዕብያዎች ይከተሉት የነበረው ስልት ለየት ያለ ነበር። ትግራይ ውስጥ የነበሩ ነጋዴዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ በሚል ሽፋን ቡናውን በሕጋዊ መንገድ ካስመጡ በኋላ ሌሎች አነስተኛ ነጋዴዎች በአህያ፣ በበቅሎና በግመል እየጫኑ ለኤርትራ ነጋዴዎች ያስተላለፉላቸው ነበር። የዚህ ዓይነቱን ሕገ ወጥ እንቅስቃሴ ከተገነዘብን በኋላ በድንበር አካባቢ ኬላዎች አዘጋጅተን መቆጣጠር ጀመርን። ከዚህ በተጨማሪም ወደ ኤርትራ የሚተላለፍ የኮንትሮባንድ ሽቀጥ ያስያዘ ዜጋ ያስያዘውን ዕቃ ዋጋ አርባ ከመቶው እንደሚሰጠው አወጅን። ክልሉ የዚህ ዓይነት ሥልጣን ባይኖረውም ከጉምሩክ ባለሥልጣን ጋራ በመማከር ይህ ተግባራዊ እንዲሆን አደረገ። ይህን ሁሉ መከላከል ብናደርግም በትግራይ በኩል ወደ ኤርትራ የገባ የኮንትሮባንድ ዕቃ አልነበረም ለማለት ያስቸግራል። እኔ እስከማውቀው ድረስ በትግራይ በኩል ወደ ኤርትራ ለማለፍ የሞከሩ አራት ቡና የጫኑ መኪኖች በተለያዩ ወቅቶች በቁጥጥር ሥር ውለው ተወርሰዋል። ኤርትራን በቡና ላኪነት ሊያሳውቃት የቻለው ከፍተኛ መጠን ቡና ግን ሰፊ በረሐና ላላ ያለ የጥበቃ ኬላ በነበረው በፋር በኩል እንዳለፈ መገመት ይቻላል።

4ኛ/ *በዓሣ ሽፋን የጦር መሣሪያና ሌላ ሸቀጥ*፣ ሻዕብያዎች ኮንትሮባንድ በስፋት እንዲነግዱ ያስቻላቸው አንዱ ዘዴ ተላላፊ *(transit)* ሸቀጥን በተመለከተ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ያደረጉት ስምምነት ነበር። በስምምነቱ መሠረት ኤርትራ ከአገርዋ ወደ ኬንያና ወደ ሌሎች የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች የምትልካቸው ሸቀጦችና ከነዚህ አገሮች ወደ ኤርትራ የሚገቡ ሸቀጦች በኢትዮጵያ በኩል በነጻ እንዲተላለፉ ተፈቅዶ ነበር። በዚህ መንገድ ወደ ኤርትራና ከኤርትራ ወደ ምሥራቅ አፍሪካ የሚተላለፉ እየተባሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለምንም ቀረጥ ገብተው በከፍተኛ ትርፍ የሚቸበቸቡ የኤሌክትሮኒክስና ሌሎች ሸቀጦች ነበሩ። ሻዕብያዎች ከዚህ መሰሉ ሕገ ወጥ ንግድ በርካታ ገንዘብ አካብተዋል። በተለይ ከኤርትራ /ምጽዋ/ ወደ ኬንያ የሚላክ ዓሣ ታሽጎ መሄድ አለበት፤ ከተከፈተ ሊበላሽ ይችላል፤ በሚል የማታለያ ዘዴ የተለያዩ ሸቀጦችን ያስገቡ እንደነበር የትግራይ መስተዳደር ደርሶበት ነበር። ሻዕብያዎችጋ በተደረሰው ስምምነት የተከፋው መስተዳደር በአንድ ወቅት አንዱን በዛላምበሳ በኩል የገባውን የታሸገ መኪና በግዴታ ሲፈትሽ በርካታ መትረየሶችና ካላሺንኮቭ ጠመንጃዎች አገኘ። ሻዕብያዎች መሣሪያው በስሕተት እንደተጫነ በማስረዳት ድርጊቱን አቅልለው ለማቅረብ ቢሞክሩም ጉዳዩ በኢትዮጵያ የጸጥታ ሁኔታ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል

---

[25] አቶ ኃይለ ጓንጉል መቀሌ ውስጥ በንግድ ሥራ የሚተዳደሩ ሀብታም ኤርትራዊ ነጋዴ ነበሩ። ሻዕብያ ኤርትራን ከተቆጣጠረ በኋላ መቀሌ ላይ ቆንስላ ሲከፍት እሳቸውም የኤርትራ ኮምዩኒቲ አባል እንደመሆናቸው በንቃት ይንቀሳቀሱ ጀመር። ሻዕብያዎች በሚያደርጉት ሕገ ወጥ እንቅስቃሴ ነጋዴዎችን ያሳትፉ ስለነበርም እሳቸውም በዚህ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በሚጎዳ ተግባር አሳትፈዋቸው ለከብት ርቢ ብለው ባሠሩት በረት ውስጥ ውስኪው ተደብቆ ተገኘ።

ተገልጸ በስመ ዓሣ መኪናዎችን ከፍቶ ያለመፈተሽ የተደረሰው ስምምነት ዳግም እንዲታይ ለፌዴራሉ መንግሥት ጥያቄ ቀርቦ ጥያቄው ተቀባይነት አገኘ።

5ኛ/ *ግድያና ዐፈና፣* ሻዕብያዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ባሰማሯቸው ነፍሰ ገዳዮች አማካይነት በርካታ ሰዎችን ገድለዋል፤ ዐፍነዋል። ከነዚህ መካከል ከትግራይ መስተዳደር ጋራ ቀጥተኛ ግንኙነት የነበራቸው የዴምሓኤ አባላት ተጠቃሾች ናቸው። ይህ ድርጅት የሻዕብያን መንግሥት በጽናት ከመታገሉ ባሻገር ከጀብሃ አፈንግጠ ወጥቶ ጠንካራ ድርጅት ያቋቋመ ነበር። ድርጅቱ ከምሥረታው ጀምሮ የሻዕብያ ሰላዮች ሠርገው ቢገቡበትም ጠንካራ የአመራር አባላት ስለነበሩት ሳይበገር ቀርቶ ነበር። በመሆኑም ሻዕብያ ኢትዮጵያ ውስጥ በስመ ቆንስላና ኤምባሲ ባደራጃቸው ነፍሰ ገዳዮች አማካይነት በነዚህ ጠንካራ የአመራር አባላት ላይ ግድያና ዐፈናን ያኪያሂድ ነበር። በሻዕብያ ቅጥረኞች አማካይነት ከተገደሉት አንዱም ዘካርያስ የተባለው የዴምሓኤ መሥራችና የፕሮፓጋንዳ ኃላፊ ነበር። ዘካርያስ ቀጭን፣ ረጅምና ቀላ ያለ ሲሆን እጅግ የተሟላ ስብእና ያለው ታጋይም ነበር። ሻዕብያ ፀረ-ዴሞክራሲ ድርጅት በመሆኑ በማንኛውም መንገድ ከሻዕብያጋ መሥራትና መደራደር አይቻልም ብሎ የሚያምን ጽኑ ታጋይ ከመሆኑም በተጨማሪ ሻዕብያን ለመታገል ሕይወታቸውን ለመሠዋት ከቆረጡት አንዱ ነበር። ይህን የተገነዘበው ሻዕብያ መቀሌ ላይ በከፈተው ቆንስላ አስተባባሪነት እንዲገደል ወሰነበት። በወቅቱ ዘካርያስ ለድርጅት ሥራ ከመቀሌ ወደ ደሴ ሄዶ እዚያ በከፈቱት ጽሕፈት ቤት ረዘም ላለ ጊዜ ቆይቶ ነበር። እንቅስቃሴውን ያጠኑት ሻዕብያዎች ድርጅቱ ውስጥ ካሠረጓቸው አባላት ጋር በመተባበር አንዱን አባላቸውን ዓዲግራት ላይ ሆኖ እንዲከታተል አስቀምጠው ሌላውን ግድያ የሚፈጽመውን ወደ ደሴ ላኩት። ዓዲግራት ያለው የሻዕብያ ሰላይ በስልክ ወደ ደሴ የተላከውን ነፍሰ ገዳይ እየመራ አመሻሽ ላይ ዘካርያስን ከቤቱ ለሥራ ጉዳይ እንደሚፈልጉት አድርገው አስጠርተውት ወጣ እንዳለ ተኩሰው ዘረሩት። ኋላ ላይ ይህን ድርጊታቸውን ለማወቅ የቻልነውም የስልክ ግንኙነቱን ሲከታተሉ ከነበሩት የአገራችን የደኅንነት አባላት ነበር። ሻዕብያዎች መንግሥት አለ በተባለበት አገር ይህን ግድያ ፈጽመው ሊያመልጡ ችለዋል።

ሌላው የዐፈና ደባ የተፈጸመው ደግሞ ገብረ ብርሃን በተባለው የዴምሓኤ ሊቀመንበር ላይ ነበር። ገብረ ብርሃን ጠይም፣ አጠር ያለ መልከ መልካም የጀብሃ ታጋይ የነበረ ሲሆን እንደ ዘካርያስ ሁሉ የዴምሓኤ መሥራች ሆኖ ሻዕብያን ለመታገል የቆረጠ ነበር። የሥራ አስፈጻሚና የዴምሓኤ ሁለተኛው ሰው የነበረው ዘካርያስ በሰላ አመለካከቱ ሲታወቅ፣ ገብረ ብርሃን ደግሞ በተግባቢነቱና በአስተባባሪነቱ ይታወቅ ነበር። ገብረ ብርሃን በሻዕብያ የታፈነው ለሥራ ጉዳይ ከአዲስ አበባ ወደ ሑመራ በተንቀሳቀሰበት ጊዜ ነበር። ይህን እንቅስቃሴውን ያወቁ የሻዕብያ ሰላዮች መምጣቱን ሑመራ ለነበረው ወኪላቸው አስታውቀው የአዲስ አበባው የኤርትራ ኤምባሲና የትግራይ ቆንስላቸው ባደረጉት ትብብር ገብረ ብርሃንን ከሑመራ ዐፍነው ወደ ኤርትራ ወሰዱት። ወስደው ምን እንዳደረጉት ባይታወቅም ይህ ድርጊትም ኢትዮጵያ ውስጥ ካከናወኗቸው እኩይ ሥራቸው አንዱ ነው። በዚህ በግድያና በዐፈና መንገድ ሻዕብያዎች መልክም ዴምሓኤ የተባለውን ተቀናቃኛቸውን በእጅጉ አዳክሙት።

ሻዕብያ የኢትዮጵያን ሀብት ለመመዝበርና ተቃዋሚዎቹን ጸጥ ለማሰኘት ሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎችን ሲያኪያሂድ ኢሕአዴግ ዐጸፋውን በተገቢ ደረጃ አልመለሰም። እንዲያውም ኢሕአዴግ የተከተለው ፖሊሲ መለሳለስና መለማመጥን ስለነበር ሻዕብያዎች የልብ ልብ ተሰምቷቸው ያሻቸውን እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸው ነበር። ሻዕብያዎች በዚህ

ስውርና ከፊል ስውር በሆነ እንቅስቃሴያቸው ወሳኝ በሚባሉት የአገራችን የመንግሥት ተቋማት ሠርገው ለመግባትና ያሻቸውን ለመሥራት ችለዋል። ይህ የሻዕብያ ጋጠወጥነት የተሞላበት እንቅስቃሴና የኢሕአዴግ አመራር ግድ የለሽነት በሁለቱ መንግሥታት መካከል የነበረውን ግንኙነት እንዴት እንዳሻከረውና እንዳበላሸው ኋላ ላይ እመለከተዋለሁ።

11. የተሠው ታጋዮች ቤተሰቦች ቅሬታ

ህወሓት ባኪያሄደው የአስራ ሰባት ዓመታት የትጥቅ ትግል የተከፈለው መሥዋዕትነት ከፍተኛ ነበር። በትጥቅ ትግሉ በትግራይ የተሠዋውን የሰው ኃይል ብዛት ምን ይህል እንደሆነ ለማወቅ በተደረገው ረጅም መረጃ የማሰባሰብ ጥናት ኃምሳ አራት ሺሕ ያህል ሰው እንደተሠዋ ተረጋግጧል። ይህ አኃዝ ሕይወታቸውን ያጡትን ብቻ የሚመለከት ሲሆን ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ የአካል ጉዳተኞችና የደረሱበት የማይታወቅና የጠፉም አሉ። ይህን ሁሉ መሥዋዕትነት የከፈለው ኅብረተሰብ በተለያዩ ወቅቶች መርዶ እንዲነገረው፣ ከተቻለም ካሳ እንዲከፈለውና የተያያዙ ማኅበራዊና ሕጋዊ ችግሮቹ መፍትሔ እንዲያገኙ ጥያቄ ያቀርብ ነበር። ከተሠውት በርካታ ወጣቶች መካከል ትዳራቸውን፣ ልጆቻቸውንና ወላጆቻቸውን ትተው ያለፉ ስለነበሩ የውርስ፣ የጋብቻና ሌሎች ማኅበራዊ ጥያቄዎችም ይነሡ ነበር። እነዚህ ጉዳዮች ለረጅም ጊዜ በእንጥልጥል በመቆየታቸው በተለይ የመሬትና የንብረት ጥያቄ መፍትሔ ሳያገኙ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሞተሠውት ወጣቶች ወላጆችና ቤተሰቦች ቅሬታቸው እየጠነከረ ሄደ።

በተለይ ኤርትራ ውስጥ ከሻዕብያ ተሰልፈው ሕይወታቸውን ያጡት ማንነት ለኅብረተሰቡ ተነግሮ የተወሰነ ካሳ በሻዕብያ ተከፍሎ ስለነበር ወሬው ትግራይ ውስጥ ሲሰማ ህወሓትስ ለምን መርዶ አይነግረንም የሚለው ጥያቄ እየተጠናከረ መጣ። ህወሓት ይህን ጥያቄ ቶሎ መመለስ እንዳለበት በማዕከላዊ ኮሚቴው ተወስኖ ጥናት ከተኪያሄደ በኋላ መርዶ ለመንገር ዝግጅት ተደረገ። የዝግጅቱ አንድ ክፍልም የታጋይ ቤተሰቦችን ያካተተ ኮንፈረንስ ጠርቶ መግባባት ላይ መድረስ ነበር። በዚህ መሠረትም የነባርና የታዋቂ ታጋይ ቤተሰቦችን ያካተተ ኮንፈረንስ በ1985 ዓ.ም. መቀሌ ላይ ተኪያሂዶ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ ውይይት ተደረገ።

በኮንፈረንሱ ከተደረጉት ውይይቶች አንዱ ድርጅቱ ለተሠውት ቤተሰቦች ሊያደርግ ያሰበውን ድጋፍ የተመለከተ ነበር። በውይይቱ የታጋይ ቤተሰቦች እንደየ ምርጫቸው በአንድ ጊዜ ሦስት ሺህ ብር የመውሰድ ወይም ደግሞ እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ ድረስ አንድ መቶ ብር በወር እንዲወስዱ የሚለው አማራጭ ተሰጠ። ከዚህ ውጭ ደህና ገቢና ኑሮ ላላቸው ቤተሰቦች በገንዘብ ምትክ አንድ ካላሺንኮቭ ጠመንጃ እንደ ማስታወሻ እንዲሰጣቸው የሚል ሐሳብም ቀርቦ ነበር። ነገር ግን አብዛኛዎቹ የተሠውት ቤተሰቦች ችግረኞች ስለነበሩ ምርጫቸው ገንዘብ እንደሚሆን በመገመት ትእምት ይህን ገንዘብ እንዲያዘጋጅ ተወስኖ ለሁሉም ለተሠዉት ቤተሰቦች ገንዘብ ቢሰጥ መቶ ስድሳ ሁለት ሚልዮን ብር እንደሚያስፈልግ ተሰልቶ ይህን ገንዘብ በአንድ ጊዜ ለማቅረብ ስለሚያዳግት በሦስት ዓመታት እንዲከፈል ተወሰነ።

በኮንፈረንሱ ቀደም ሲል የተጠቀሱትን የእርዳታ አማራጮች ቀርበው ሰፊ ውይይት ከተደረገ በኋላ ስምምነት ላይ ተደረሰ። ስምምነት ላይ የተደረሰበት አግባብ ግን እንደተለመደው ድርጅቱ ወስኖ ለማሳመን በሚያደርገው ቅስቀሳና ውትወታ ነበር። ድርጅቱ ድኻ እንደሆነ፣ ያሰባሰበው ሀብት እንደሌለው፣ ከመንግሥት ካዝና ለመክፈል ሕጋዊው

ድኻ እንደሆነ፣ ያሰባሰበው ሀብት እንደሌለው፣ ከመንግሥት ካዝና ለመክፈል ሕጋዊው ማዕቀፍ እንደማይፈቅድለትና ሕይወትን የሚያክል ነገር በገንዘብ መካስ አስቸጋሪ እንደሆነ ተገንዝበው ድርጅቱ ያቀረበውን የመፍትሔ ሐሳብ እንዲቀበሉ ከተማጸነ በኋላ ኮንፈረንሱ በቀረበው ሐሳብ ተስማምቶ የቀረበው የካሳ አማራጭ ተግባራዊ እንዲሆን ተደረገ።

የገንዘብ ካሳና ማስታወሻ ለተሠውት ቤተሰቦች ይሰጥ በተባለበት ወቅት የተነሡ በርካታ ጥያቄዎች ነበሩ። ከነዚህ ጥያቄዎች አንዱም ታጋዮች የተሠውት የደርግን ፋሽስታዊ ሥርዓት ለማስወገድ ስለነበር ለምን በአዲሱ መንግሥት ቋሚ ጡረታ አይቆረጥላቸውም? ከደርግ ጎን በሠራዊትነት ተቀጥረው ይዋጉ ለነበሩ የጡረታ መብት ሲከበር ለምን ለታጋዩ የጡረታ መብት አይፈቀድለትም? ለታጋዩ የጡረታ መብት ካልተፈቀደለት አኪያሂዱ ፍትሐዊ ሊሆን አይችልም፤ የሚል ክርክር ተነሥቶ ነበር። በጊዜው ለጥያቄው የተሰጠው መልስ የደርግ ሠራዊት እንደ ህወሓት የአንድ ድርጅት ሳይሆን የመንግሥት ሠራዊት እንደመሆኑ የሠራዊት አባላት የጡረታ መብትም ይከበር የነበረው እንደ አገልግሎት ዘመናቸው ከደመወዛቸው እየተቆረጠ በሚጠራቀመው መዋጮ ነው የሚል ነበር። ኢሕአዴግ የታጋዮች የጡረታ መብት ይጠብቅ ከተባለም ደርግን የተፋለሙት እንደ ኢሕአፓ፣ ኢዴኅ፣ አነግ፣ አነግ፣ ምሶነግ፣ ወዘተ... ያሉት ድርጅቶች ሁሉ የይገባኛል ጥያቄ ሊያነሡ እንደሚችሉም ተገለጸ። በትጥቅ ትግል የወደቁት ብቻ ሳይሆኑ ከተማ ውስጥ ደርግን እየታገሉ የተሠውቱም የይገባኛል ጥያቄ ቢያነሡም ጉዳዩ እጅግ ውስብስብ ይሆናል ተባለ። ስለዚህ ድርጅቱ ሊያደርገው የሚችለውን ብቻ ያደርጋል ተባለ።

ትግራይ ውስጥ የተሠውት ቤተሰቦች ያነሡት ሌላው ጥያቄ «*ኤርትራ ውስጥ ልጆቻቸው ለተሠዉባቸው ቤተሰቦች ካሳ የሚሰጠው መንግሥት ራሱ ሲሆን የሚሰጠው የካሳ መጠንም ከፍተኛ ነው፤ እኛ አካባቢ ግን መንግሥት ካሳ ካለመክፈሉም በተጨማሪ የሚከፈለውም እጅግ ዝቅተኛ መጠን ነው፤*» የሚል ነበር። ለዚህ የተሰጠው መልስም «*ቀደም ሲል የኤርትራ መንግሥት የሚባል ኧንዳልነበረና፣ ሻዕብያ አዲስ መንግሥት ሲያቋቁም ግን ድርጅትም መንግሥትም ሊሆን ሲችል እኛ ጋራ ግን ይህ አልሆነም። በመሆኑም ሻዕብያ ያደረገውን ሁሉ ማድረግ አንችልም*» የሚል ነበር። ከዚህ ሌላም «*ሻዕብያዎች ለእያንዳንዱ የተሠዋ ታጋይ ቤተሰብ አስር ሺሕ ብር መክፈላቸውም እንደመንግሥት ዓቅም ስለነበራቸው ነው፣ እኛ ግን ይህን ስናደርግ እንደ ድርጅት ስለሆነ የነእርሱን ያህል ለመክፈል አንችልም*» የሚል መልስ ተሰጥቷል። መልሶቹ አጥጋቢ ባይሆኑም በመጨረሻ በድርጅቱ የተደረገው ውሳኔ ለነዚህ ለተሠዉት ቤተሰቦች የተመደበው ገንዘብና ጠመንጃ ብቻ እንዲከፈል የሚል ነበር።

ለተሠውት ታጋዮች ቤተሰቦች እርዳታ በተሰጠበት ወቅት ካሳውን የሚያገኘው ማን ነው? የሚል የውርስ ጥያቄም ተነሥቶ ነበር። ይህ ጥያቄ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት እንዲስተናገድ ተደረገ፣ ቀጥተኛ ወራሾች ሚስትና ልጆች፣ ሚስትና ልጆች በሌሉበት ወላጆች፣ ወላጆች በሌሉበት ደግሞ ወንድምና እኅት ወራሾች እንዲሆኑ ተደረገ። አባትና እናት ተለያይተው ከሆነም ውርሱ ለሁለቱ እንዲከፈል ተደረገ። ይህ የተከፈለው የውርስ ገንዘብ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ አብዛኛዎቹን ሴቶች፣ አዛውንትና ሕፃናት ከድኽነት ማጥ ሊያላቅቃቸው አልቻለም። አብዛኛዎቹ የተሠዉት ወጣቶች በምርት ሥራ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ ስለነበሩ እነዚህን ያጡ ቤተሰቦች ለጉስቁልናና ለከፋ ድኽነት መዳረጋቸው አልቀረም። አንዳንዶቹም ሁለትና ከሁለት በላይ ልጆች ያጡ ስለነበሩ ሐዘኑና የኑሮ ጫናው ተደራርቦባቸው ከፍተኛ ብሶት ነበራቸው። በመሆኑም እንኳን ድርጅቱ የሰጣቸው አነስተኛ ገንዘብና የተሻለ ድጎማም ቢደረግላቸው ሁኔታቸውን መለወጥ አስቸጋሪ ነበር። በኮንፈረንሱ

ወቅትም የነዚህ ቤተሰቦች የከፋ የሕይወት ሁኔታ ከተጎዳና ከገረጣ ሰውነታቸው ይታይ ነበር።

የተሠውት ቤተሰቦች መርዶ ከተነገራቸው በኋላ አንዳንዶቹ ቀድሞውንም የቅርበቻቸውን ሞት ገምተውት ስለነበር ለቅሶ ሳይቀመጡ ሐዘናቸውን ሲወጡ ሌሎቹ ደግሞ ልቅሶ ተቀምጠው ከድርጅቱ በድጎማ ያገኙትን ገንዘብ ለተዝካር አውለውታል። አንዳንዶቹ ደግሞ በተገኘው ገንዘብ ለልጆቻቸው ማስታወሻ ቤት ሠርተው፣ ላም፣ ፍየልና በግ ገዝተው ግርባት ጀምረው ነበር። የተደረገላቸው መጠነኛ ድጎማ ሕይወታቸውን ሳይለውጠው አስከፊ ሕይወታቸው የቀጠሉት ግን እጅግ በርካታ ነበሩ።

12. የሻዕብያ በሠራዊት ግንባታ መጠመድ

ሻዕብያዎች በደርግ ውድቀት ማግስት ጊዜያዊ መንግሥት ከመሠረቱ ከሁለት ዓመት በኋላ ቋሚ መንግሥት አቋቋሙ። ሻዕብያዎች በረጅሙ ጦርነት ያዳበሩት ወታደራዊ ልምድ *"Might makes Right"* በአማርኛ «እውነቶች በጉልበት ይረጋገጣሉ» ወደሚለው የፈረንጆች አባባል የመራቸው ይመስላል። ጠንካራ ወታደራዊ ኃይል ካለ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥንካሬ ሊረጋገጥ ይችላል የሚለውን ሐሳብ ከዱሮ ወራሪዎቻቸው የቀሰሙት ትምህርትም ይመስላል። በመሆኑም በወቅቱ ከስድሳ ዐምስት ሚልዮን በላይ ሕዝብ የመምራት ኃላፊነት የወሰድነው ኢሕአዴጎች የቆየውን ሠራዊታችንን ስናሰናብት፣ ሁለት ሚልዮን ስድስት መቶ ሺሕ ያህል ሕዝብ[26] ይመራ የነበረው ሻዕብያ ተጨማሪ ወጣቶች ለወታደርነት በመመልመል ኃይሉን ለማዳበር ወሰነ። ይህን ኃይሉን ለማሠልጠንም በምዕራባዊ ቆላ ኤርትራ ክፍል የሚገኝ ሳዋ የተባለ ስፍራ መርጠ ወጣቶችን በገፍ መመልመል ጀመረ። ኢሕአዴጎች ይህን የሻዕብያ ውሳኔ ለኢትዮጵያ ከሚፈጥረው ሥጋት አንጻር በጥሞና አልተመለከትነውም ነበር።

ሻዕብያዎች ሳዋን ማዕከል አድርገው ወጣቶች ማሠልጠን ሲጀምሩ ኢትዮጵያ ሥጋት እንዳያድርባት ለማረጋጋት ማዕከሉ ወጣቶችን በሥራ፣ በሥነ-ምግባር፣ በዕውቀትና በክህሎት የሚገነባ እንደሆነ አሳውቀውን ነበር። እኛም ይኸን እንዳለ ተቀብለን ከሻዕብያ ጋር የነበረንን ግንኙነት ቀጠልን። ሻዕብያ ይህን ማዕከል ከፍቶ የመጀመሪያ ዙር ሥልጠና በጀመረበት ማግስት ከማዕከሉ መቋቋም ልምድ እናገኝበት ይሆናል በማለት የትግራይ መስተዳድር ማዕከሉን ለመጎብኘት ሻዕብያዎችን ጠይቆ ተፈቀደለት። በዚህ መሠረት በክልሉ ፕሬዝዳንት/ገብሩ/ የሚመራ ቡድን ወደ ሳዋ ተጓዘ። በወቅቱ የሥልጠና ማዕከሉ ገና በመቋቋም ላይ ስለነበር በርካታ መሠረተ ልማቶች ባይሟሉም በቂ የውሀና የመብራት አገልግሎት ነበረው። ለመሪዎች ማረፍያ የሚሆኑ ማቀዝቀዣና ገና በከተማ ያልተስፋፋው የሳተላይት ዲሽ የተገጠመላቸው ኮንቴይነሮች ነበሩ። ወደ ሳዋ ያቀናነው ልኡካንም በእነዚህ ኮንቴይነሮች ዐርፈን እዚያው አደርን።

የልኡካን ቡድኑ አባላት በማዕከሉ የሚደረጉትን እንቅስቃሴዎች የጎበኘነው በነገታው ነበር። የተመለከትነው ግን የሙያና የክህሎት ሥልጠና ሳይሆን የመጀመሪያውን ዙር የሰዋ ወታደራዊ ሥልጠና ነበር። ከተለያዩ የኤርትራ ክፍሎች የተመለመሉ ወጣቶች በመጀመሪያው የሰልፍና የቡድን ወታደራዊ እንቅስቃሴ ሲሠለጥኑ አይተንም ፕሮጄክቱ የሙያና የክህሎት ሥልጠና ሽታ እንደሌለው አረጋገጥን። ይህን ግዙፍ ተቋም የሚመራው ደግሞ የኢሳያስ አፈወርቂ ቀኝ እጅ የነበረውና በትጥቅ ትግሉ ዘመን ባዕከርን ስናጠቃ[27]

[26] ጦርነቱ ከተጠናቀቀ ከአንድ ዓመት በኋላ ትግራይን ለመጎብኘት የመጣው የዱሮው የሻዕብያ ሊቀመንበር ሮመዳን መሐመድ ኑር የወቅቱን የኤርትራ ሕዝብ ብዛት እንደገለጸልን

[27] ምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተጠቀሰው

የሻዕብያን ኃይል ሲመራ የነበረው በምርኮ ክፍፍል ከኛ ጋራ ሳይስማማ የቀረው ተኽላይ ሀብተ ሥላሴ ነበር። ተኽላይ ለወታደራዊና ለፖለቲካዊ ሥልጠና እንጂ ለክህሎትና ለሙያ ሥልጠና እንዳልተመረጠም ግልጽ ነበር።

የልኡካኑ ቡድን አባላት ሳዋ በቆየንበት ጊዜ በማዕከሉ ለሚሰጠው ሥልጠና የተዘጋጀውን ከሪኩለም እንዲሰጡን ለካምፑ መሪዎች ጠየቅን። ሆኖም ለጊዜው አምንታዊ ምላሽ ሰጥተውን ትንሽ ቆይተው ግን ከሂዳችሁ በኋላ እንልክላችኋለን ብለው ከሪኩለሙን ሳይሰጡን ቀሩ። በዚህ አጋጣሚም ሻዕብያዎች ከሪኩለሙ ቢኖርም ሊሰጡን እንዳልፈለጉ፣ ሙያንና ክህሎትን በተመለከተም ሥልጠና እንዳልነበር ተገንዝብን። የተባለው ሥልጠና በሌለበት ለምን ማዕከሉን እንድንጎበኝ እንደፈቀዱልን እስከአሁን ድረስ አይገባኝም። ያም ሆነ ይህ ማዕከሉ የወታደራዊ ማሠልጠኛ እንጂ የሙያና የክህሎት እንዳልሆነ በተጨባጭ ተገንዝበን ወደ አገራችን ተመለስን።

በኢሕአዴግ አመራር ደረጃ ሳዋን በተመለከተ ውይይት ባይደረግም፣ አንዳንዶቻችን በግል ስንነጋገር ሻዕብያ ሳዋን እንደወታደራዊ ማዕከል ለማሳደግ የመረጠው በሱዳን በኩል የተደቀነበትን ሥጋት ለማስወገድ ነው የሚል መላምት ነበረን። የሱዳኑ ፕሬዝዳንት ኮሎኔል አልበሽር በአክራሪ እስላሞች ማለትም በእስላማዊው ብሔራዊ ግንባር (*National Islamic Front*) ድጋፍ በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን የጨበጠ ነበር። እስላማዊው ግንባር እጅግ አክራሪ ከመሆኑም የተነሣ ሱዳንን በሙሉ፣ የደቡብ ሱዳን ክርስትያኖችና ጣያት አምላኪዎችን ጨምሮ፣ በሸሪዓ ወይም በእስላማዊ ሕግ ለማስተዳደር ቆርጦ ተነሥቶ ነበር። ይህን ፍላጎቱንም በሱዳን ብቻ ሳይሆን በጎረቤት አገሮችም በተለይም በኤርትራና በኢትዮጵያ ላይ ለመጫን ዕቅድ ነድፎ ነበር። በእስላማዊው ግንባር አስተሳሰብ ኤርትራ አብዛኛው ሕዝቧ የእስልምና እምነት ተከታይ በመሆኑ በእስላማዊ ሕግ መገዛት ነበረበት። ኢትዮጵያም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የእስልምና ተከታዮች ስላሏት የእስላማዊው ሕግ ተጽዕኖ በኢትዮጵያም እንዲኖር ፍላጎት ነበራቸው። ከዚህ የተነሣም በኤርትራ ምዕራባዊ ቆላ እንቅስቃሴያቸውን ያጧጥፉ የነበሩትን እስላማዊ ጅሃድ ቡድን (*Islamic Jihad*) እየደገፉ ዓላማቸውን ለማሳካት የተቻላቸውን ያህል ይንቀሳቀሱ ነበር። ኤርትራም ይህን እንቅስቃሴ በቅርቡ ትከታተለው ስለነበር ጦርነት ቢነሣ ዐጸፋውን ለመመለስና ለማጥቃት ሰፊ ወታደራዊ ምልመላ በማካሂድ ምልምሎችን በሳዋ ማሠልጠን እንደጀመረች የምንገምትም ነበርን።

ሱዳኖች በእስላማዊ ጅሃድ አማካይነት በኤርትራና በኢትዮጵያ ይንቀሳቀሱ የነበሩትን ተቃዋሚዎች ይደግፉ ስለነበር ኤርትራና ኢትዮጵያ የጋራ እንቅስቃሴ ማካሄዳቸው አልቀረም። በተለይ በሱዳኑ እስላማዊ ጅሃድ የሚደገፉ ግብጻውያን አዲስ አበባ ድረስ ዘልቀው የቀድሞውን የግብጽ ፕሬዝዳንት ሑስኒ ሙባረክን ለመግደል ያልተሳካ ሙከራ ካደረጉ በኋላ ኤርትራና ኢትዮጵያ ተጨባጭ የጋራ ሥጋትና አደጋ ስለተደቀነባቸው የጋራ የመከላከል ዐጸፋ በማካሂዳቸው ኤርትራ ለኢትዮጵያ ወቅታዊ ሥጋት ትሆናለች የሚል ግምት በኢሕአዴግ አመራር በኩል ፍጹም አልነበረም። እንዲያውም ሱዳን ውስጥ ፀረ-በሽርና ፀረ-ብሔራዊ እስላማዊ ግንባር እንቅስቃሴዎችን በጋራ እናካሂድ ነበር። እነዚህን በጋራ ስናካሂዳቸው የነበሩትን እንቅስቃሴዎች መግለጽ ከአገር ደኅንነት አንጻር ተገቢና ጠቃሚ ስላልሆነ በአጠቃላይ የጋራ እንቅስቃሴ እንደነበር ብቻ ጠቁሜ ማለፉን መርጫለሁ።

ሱዳን በ1980ዎቹ ኤርትራንና ኢትዮጵያን የሚያጠቁ ሽምቅ ተዋጊዎችንና ሠርጎ ገቦችን ከማሠልጠኗ በተጨማሪ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ስሙ የገነነውንና ጽንፈኛ እስላማዊ ርዕዮተ ዓለም በማራመድ የእስልምናን ትንሣኤ እውን አደርጋለሁ ይል የነበረውን አልቃይዳ መሪ

ቢን ላደንን በማስጠጋቷ በአሸባሪ አገሮች ተርታ ልትሰለፍ ችላለች። ምዕራባውያንም የሱዳንን እስላማዊ ጽንፈኝነት አጥብቀው ይቃወሙ ስለነበር ሱዳን ከዓለም የምትገለልበትንና የምትዳከምበትን ስልት ቀይሰው ይህን ግባቸውን እንዲፈጽሙላቸው ኢትዮጵያንና ኤርትራን በአጋርነት ለማሰለፍ ሞክረዋል። በደቡብ ሱዳን የተቀጣጠለው የነጻነት እንቅስቃሴም ከዚሁ የምዕራቡ ዓለም ስትራቴጂ ጋራ የተያያዘ ነበር። መጀመሪያ ላይ ኤርትራ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በምዕራባውያኑም እንድሥጋት ምንጭ ያልታየችበት አንዱ ምክንያትም የሁሉም ትኩረት ሱዳን በደቀነችው የጸጥታ ሥጋት ላይ ስለነበር ነው። በአጠቃላይ ሱዳን የጽንፈኛ እስልምና ንቅናቄ ማዕከል ለመሆን ያደረገችው ሙከራ ኤርትራ ኃይሏን እንድታጠናክርና ጥርጣሬ ውስጥ እንዳትገባ ምክንያት ሆኗል።

እንዲህም ኤርትራ መጀመሪያ በልማት ሽፋን ሳዋ ላይ የፈጠረችው የሥልጠና ማዕከል ቀስ በቀስ ማንኛውም ለውትድርና ብቁ የሆነ ወጣት ኤርትራዊ ዜጋ በተለያየ ዙር የሚሠለጥንበትና ግዙፍ ሠራዊት የሚገነባበት ስፍራ ሆነ። ለዐቅመ አዳም የደረሱ ጎልማሳ ሴቶችና ወንዶችም በዚህ የሥልጠና ሂደት እንዲያልፉ ተገደውም ኤርትራ ሁሉም ዜጋ የሚሳተፍበት የእስራኤል መሰል የመከላከያ ኃይል ልትገነባ ሞከረች። ይህ የሳዋ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ማዕከል መሆን ይበልጥ ጎልቶ የታየው ሠልጣኞቹ በወታደራዊ አሐዶች ተደራጅተው መንቀሳቀስ ሲጀምሩ ነበር።

13. የኢሕአዴግ ሠራዊት መዳከም

ሻዕብያዎች በትጥቅ ትግሉ ጊዜ ካደራጁት ሠራዊት በተጨማሪ የአገሪቱን ወጣቶች በሙሉ በወታደርነት መልምለው ሲያሠለጥኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ምንም ዓይነት ወታደራዊ ግምባታ አልተደረገም ነበር። እንዲያውም የነበረውን ሠራዊት በከፊል የማሰናበትና የመበተን እርምጃ ተወስዶ ነበር። የኢሕአዴግ አመራር ይህን ያደረገው በሁለት ምክንያቶች ነበር። አንደኛው ሠራዊቱን ከብሔር ተዋፅኦ አንጻር የማመጣጠን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለመልሶ ማቋቋምና ለኢኮኖሚያዊ ልማት ዋና ትኩረት ለመስጠት ነበር። በእርግጥ የሠራዊቱን ተዋፅኦ ማመጣጠን ትክክለኛ አቅጣጫ ቢሆንም ያአገሪቱን የደኅንነት ሥጋት በሚገባ ሳያገናዝብና ተተኪዎችን በሚገባ ሳያዘጋጅ በሺዎች የሚቆጠሩ ተራ ተዋጊዎችንና የበታች ኃላፊዎችን በገፍ ማሰናበቱ በመከላከያ ተቋሙ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ አልቀረም።

በወቅቱ የሠራዊቱን የብሔር ተዋፅኦ ለማመጣጠን ከህወሓት በርካታ ታጋዮች ተሰናብተው አመራሩ ግን ሳይነካ መቅረቱ ሠራዊቱን ሥጋ ያልለበሰ አጥንት አድርጎታል። ምክንያቱም ከሌሎች ብሔሮች የተመለመሉ ተራ ወታደሮችን ቁጥር በሚፈለገው ደረጃ ጨምሮ ክፍተቱን መሙላት አልቻለም ነበርና። ከዚህ ሌላ ፋይዳ ያለው ማመጣጠን ሊደረግ ይችል የነበረው በመኮንኖች አስኳል *(core)* ስለነበር ይህን ለማድረግ ከሁሉም ክልሎች የተውጣጡ ሠራዊቱን ለመምራት የሚችሉ የሠለጠኑ መኮንኖች ማዘጋጀት የግድ ይል ነበር። ይህ ሁሉ ሳይደረግ በስመ ማመጣጠን የተደረገው ቅነሳም የተቀመጠለትን ግብ ካለመምታቱ በተጨማሪ ልምድ ያለውን ተራ ተዋጊ በማሰናበት አገራችን ደካማ የመከላከል ቁመና እንዲኖራት አድርጓል።

ሠራዊቱን ለመቀነስ ያስገደደው ሌላ ምክንያት የበጀት ችግር ነበር። በአገር ደረጃ የመልሶ ማቋቋምና የመልሶ ግንባታ ዕቅድ ተይዞ ጠንካራ ሠራዊት ለመገንባት የሚያስፈልገውን ከባድ ወጪ መሸፈን አይቻልም የሚል ምክንያት ይቀርብ ነበር። ኢኮኖሚውን ይቆጣጠሩ የነበሩ ዓለም ዓቀፍ ለጋሾችም ለመከላከያ በሚወጣው በጀት ላይ ጣሪያ መደረግ አለበት እያሉ ይወተውቱና ተጽዕኖም ያሳድሩ ስለነበር የኢሕአዴግ አመራር ለሠራዊት ግንባታ በቂ

በጀት ሊመድብ አልቻለም። በእርግጥ በዋነኛነት ከደርግ የተወረሱ የጦር መሣሪያዎችና መሠረተ ልማቶች በመጠቀም የተወሰኑ ማስተካከያዎች ተደርገዋል። ውሱን እግረኛ ጦር ሠራዊትና አየር ኃይሉን ዳግም አደራጅቶ ለማንቀሳቀስም ተሞክሯል፤ መጠነኛ ሥልጠናዎችም ተኪያሂደዋል። ሆኖም እነዚህ እንቅስቃሴዎች የአካባቢ ሥጋትን በሚያስወግድ ደረጃ አልተከናወኑም። አየር ኃይላችን የታጠቀው ደርግ ሲጠቀምበት በነበረው ሚግ 21ና 23 ተዋጊ አውሮፕላኖችን ሲሆን ለማጓጓዣ የሚገለገልባቸውም እጅግ ጎላ ቀርና ያገለገሉ አውሮፕላኖችን ነበር። በተመሳሳይ ሁኔታ ለውግያና ለማጓጓዣ የሚያገለግሉ የተወሰኑ ሄሊኮፕተሮችም ነበሩ። ችግሩ ግን የመሣሪያዎች ማርጀትና መለዋወጫ መጥፋት ብቻ አልነበረም፤ በቂ ዘመናዊ መሣሪያዎችን ሊያንቀሳቅስ የሚችል የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረትም ነበር። ከደርግ ውድቀት በጎላ በአየር ኃይሉ የተወሰኑ በደርግ ዘመን ያገለግሉ ጥቂት አዲስ አብራሪዎች ብቻ በኢሕአዴግ ተመልምለው ሠልጥነው ነበር። በርካታ ታዋቂ አብራሪዎች ግን በተፈጠረው የፖለቲካ ቀውስ ምክንያት ተሰደውም፤ ተባረውም፤ ጠፍተውም ነበር። አዲሱ ኃይል ደግሞ በአግባቡ ተደራጅቶና ተቋቁሞ በሁለት እግሩ ባለመቆሙ ኢትዮጵያ በአካባቢው የነበራትን የአየር ኃይል የበላይነት አጥታ ነበር።

እግረኛው ሠራዊትም በተሻላ ሁኔታ እንዲደራጅና እንዲቋቋም አልተደረገም ነበር። በዚህ ረገድም አንዱ የችግር ምንጭ ቅድሚያ ለመልሶ መቋቋሙና ግንባታ መሰጠቱ ነበር። የእግረኛው ሠራዊት ትጥቅም በታጋዮች እጅ የነበሩና ከደርግ የተማረኩ መሣሪያዎች ነበሩ። ታንኮች፣ መድፎች፣ ሞርታሮች፣ ወዘተ... ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ አንጻር ያረጁና ጊዜ ያለፈባቸው ነበሩ ሊባል ይቻላል። ቲ 55 እና ቲ 62 ታንኮች ቢኖሩም ከሚያስፈልገው ዘመናዊ የጦር መሣሪያ አንጻር አጥጋቢ አልነበሩም። ከዚህ ሌላ አሳሳቢ የነበረው በቂ ሠራዊት ያለመኖሩ ነበር። በአገሪቱ ምሥራቅና ደቡብ ምዕራብ ቀጠናዎች የነበረውን የጸጥታ ችግር ለማስታገስ በርካታ ሠራዊት ያስፈልግ ነበር። ከወደ ሱዳን የተፈጠረው ሥጋትም ቀላል አልነበረም። እነዚህ አካባቢዎች የሥጋት ቀጠናዎች ስለነበሩ ብዙ ኃይል ሊሰማራባቸው በተገባ ነበር። ሆኖም በኢሕአዴግ በኩል ከጸጥታ ሥጋት ያለፈ ትርጉም አልተሰጣቸውም ነበር። አመራሩ እጅግ ግዙፉን የደርግ ሠራዊት አቸንፈያለሁ በማለት የከፋ ወታደራዊ ተግዳሮት ሊያጋጥመው እንደሚችል ሳያጤን ዘና ብሎ ነበር። ይህ ሁሉ አመራሩ ይከሱቱ ለነበሩ ችግሮች በቂ ክብደት እንዳይሰጥና አስፈላጊውን ቅደመ ዝግጅት እንዳያደርግ ተጽዕኖ ማሳደሩ አልቀረም።

ሻዕብያ ወረራ ከመፈጸሙ በፊት በኢሕአዴግም ይሁን በህወሓት ሲደረጉ በነበሩ የአመራር ስብሰባዎች የሠራዊት ግንባታን በተመለከተ በቂ ትኩረት አይሰጥም ነበር። የሠራዊት ጉዳይ ሲነሣ ብዙ ጊዜ ይወሳ የነበረው የማመጣጠኑና የተሰናበቱትን የማቋቋሙ ጉዳይ ነበር። ዐልፎ ዐልፎም የጸጥታ ችግሮችና ሠራዊቱ እነዚህን ችግሮች እንዴት እየተወጣ እንደሆነ የሚያሳዩ ዘገባዎች ይቀርቡ ነበር። ከዚህ ያለፈ ጥልቀት ያለው ውይይትና ክርክር ካለመኪያሄዱ በላይ በተለይ የህወሓት አመራር ወቅቱ የመልሶ ማቋቋምና የመልሶ ግንባታ ነው በማለት በሠራዊቱ የነበሩትን የአመራር አባላትም በዚሁ በመልሶ ማቋቋሙ ሥራ እንዲሰማሩ አድርጓል። በትጥቅ ትግሉ ጊዜ የህወሓትና የኢሕአዴግ ወታደራዊ አዛዥ የነበረውና በሽግግሩ ጊዜም የመከላከያ ሚኒስትር የነበረው ሰዬ አብርሃ ከሠራዊቱ አመራር ተነሥቶ በልማቱ ሥራ እንዲሰማራ ሲደረግ የኢሕአዴግም ሆነ የህወሓት አመራር ለሠራዊቱ ግንባታና ለጸጥታ ጉዳዮች እጅግ ዝቅተኛ ትኩረት እንደሰጠ መገንዘብ ይቻላል።

የሰዬ ከሠራዊቱ መውጣትና በትእምት መመደብ በወቅቱ ትኩረት ሳይሰጠው ቆይቶ፣ ሻዕብያ ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት ግን በጣም አነጋጋሪ ሆኖ ነበር። አብዛኞዎቻችን ትእምት እጅግ ተዳክሟል፤ የተቋሙ ህልውና ሥጋት ላይ ወድቋል፤ እንል ስለነበር ሰዬ

ሠራ አስኪያጅነት ሲመደብ ውሳኔውን ደግፈነው ነበር። ስብሓት ግዙፉን የትእምት ተቋም በሚመራበት ወቅት ኩባንያዎቹ ተዳክመው ለኪሳራ ተዳርገው ስለነበር ስጼ ሲመጣ ሁኔታው ይሻሻላል ብለን ገምተን ነበር። ስብሓትን በስጼ የመተካቱ ሐሳብ የተወጠነውና ለአመራሩ የቀረበው ግን በድርጅቱ ሊቀመንበር በመለስ ዜናዊና በምክትል ሊቀመንበሩ ተወልደ ወልደ ማሪያም ነበር። ሁለቱም የትእምት ቦርድ አመራር አባላት ስለነበሩም ድርጅቱ እያጋጠሙ የነበሩትን ችግሮች ያውቁ ነበር። ስብሓት ትእምትን ለመምራት ብቁመቻሉ በስጼ መተካቱ የአብዛኛውን የአመራር አባል አምንታ ቢያገኝም በተወሰኑ የአመራር አባላት ስጼ ከሠራዊቱ ሲነሣ የመከላከያ ዐቅማችን አይዳከምም ወይ? የሚል ጥያቄ ቀርቦ ነበር። ለዚህ የተሰጠው መልስም ሠራዊቱን በሚገባ የሚያውቁትና ሊመሩት የሚችሉ እነ ጻድቃን፣ ሓየሎምና ሌሎችም ስላሉ ችግር የለም የሚል ነበር። በተለይ ወታደራዊ ንድፈ ሐሳቦችንና ዶክትሪኖችን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ በመምራት በኩል ጻድቃን ጉልሕ ሚና ሊጫወት ይችላል ተብሎም ነበር።

የአንድ አገር ሠራዊት ሲገነባ ዕውቀትና ክህሎት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በደርግ ሠራዊት የነበረው ክህሎትና ዕውቀት ቀላል ባይሆንም ከጥቂት ሙያተኞች በስተቀር አብዛኛው የደርግ ሠራዊት አባላት በአዲሱ ሠራዊት አልተካተቱም ነበር። ለዚህም ይሰጥ የነበረው ምክንያት የደርግ ሠራዊት ፀረ-ሕዝብ በመሆኑ መፍረስ አለበት እንጂ በአገሪቱ የመከላከያ ወቅም ግንባታ ሚና አይኖረውም የሚል ነበር። ይህ ያኢሕአዴግ አመራር አንዱ ስሕተት ነበር። በእርግጥ ደርግም ኢሠፓም እንደ መንግሥታዊና እንደ ፖለቲካዊ ተቋም በአገራችን ላይ ከፍተኛ ጥፋት አድርሰዋል። የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያው መብቶች ከመርገጥ አልፈው የዘር ማጥፋትና የጦር ወንጀሎች ፈጽመዋል። ከዚህ አኳያ ተቋሙና የተቋሙ ቀንደኛ መሪዎች በወንጀሉ መጠየቅ ስለነበረባቸው ተቋሙ ሲፈርስና ሕጋዊነት ሲጠፋ ጥናዎቹ ወታደራዊ መሪዎቹም ለእስር ተዳርገዋል። ከዚህ ዐልፎ ግን በኢሠፓ ይታዘዝ የነበረው ሠራዊት በጠቅላላ ብትንትኑን ማውጣት ጉዳዩን ፖለቲካዊና አገራዊ ሳይሆን ድርጅታዊና ተቋማዊ ፉክክር ላይ የተመሠረተ ያስመስለዋል።

የደርግ ሠራዊት አመራር አባላትን ጉዳይ ወደ ጎን ትተን ተራ ወታደሮችና በሙያቸው የሠለጠኑ መካንኖች ግን የአገራችን ሠራዊት አባላት ሆነው ቢያገለግሉ ችግር አልነበረውም። ለነገሩ በመጨረሻ ሰዓት በተማረኩትና ቀደም ብለው ተማርከው የኢሕአዴግ አባላት በሆኑት የደርግ ሠራዊት አባላት መካከል ከፍተኛ ልዩነት አልነበረም:: አሕዴድንና በከፊል ብአዴንን ያጥለቀለቁት ታጋዮችና የአመራር አባላት የደርግ ሠራዊት አባላት የነበሩና ከተማረኩ በኋላ ተለውጠናል ያሉ ነበሩ። ከአሕዴድ አባዱላ ገመዳ፣ ኩማ ደመቅሳ፣ ባጫ ደበሌ፣ ዓለምሸት ደግፌ፣ የደርግ ሠራዊት አባላት ሆነው ኖረው አሕዴድን ከተቀላቀሉ በኋላ ከከፍተኛ ጀኔራልነት ማዕርግ ጀምሮ እስከ ክልል ፕሬዚዳንትነት ደረጃ ደርሰዋል። እነዚህን በከፍተኛ የድርጅትና የሠራዊት አመራር ላይ አስቀምጠ ሌላውን የደርግ ሠራዊት አባል አዲስ በተቋቋመው ሠራዊት እንዳይሳተፍ መከልከል ትክክል አልነበረም:: በኢሕአዴግ የመጠመቅ ጉዳይ ከሆነ በተከዜ፣ በማይ ጋባና በሌሎች የትግራይ አካባቢዎች እንደተደረገው ሁሉ ከደርግ የተረከብናቸውንም ማጥመቅ ከባድ አልነበረም። እንዲያውም ኢሕአዴግ በሕገ መንግሥቱ እንዳሰፈረው፣ ሠራዊቱ ከፖለቲካ ነጻ መሆን ስላለበት በኢሕአዴግ ሳይጠመቅም በዜግነቱ ብቻ የሠራዊቱ አባል የመሆን መብቱን አስጠብቆ ቢቀጥል አገሪቱን የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ ባልነበር።

የደርግ ሠራዊት አባላት በግለሰብ ደረጃ ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን በጥቅም ላይ የሚያውሉበትና አዲስ በተደራጀው ሠራዊት ውስጥ በአባልነት የሚቀጥሉበት ሁኔታ ቢመቻች ኖሮ ከፖለቲካው አንጻር ይፈለግ የነበረውን የብሔር ብሔረሰብ ስብጥር ከማሟላትም ሌላ የረጅም ጊዜ ልምዳቸውንና ዕውቀታቸውን አገራዊ ሠራዊት ለመገንባት

ባዋሉት ነበር። እንደሚታወቀው የኢሕአዴግ ሠራዊት በአብዛኛው በህወሓት አባለት የተመሠረተ ሲሆን የደርግ ሠራዊት ደግሞ በአብዛኛው ከደቡብና ከመኻል አገር በተገኙ ዜጎች የተገነባ ነበር። ከነዚህ ሁለት ሠራዊቶች የተውጣጡ አባላት አብረው እንዲሠሩ ቢደረግ ኖሮ ከፖለቲካውም ከወታደራዊውም ብቃት አንጻር የተሻላ ሠራዊት መፍጠር በተቻለ ነበር። ይህ ቢደረግ ኖሮ በዋናነት ይከፋ የነበረው የደርግን ሠራዊት በጥላቻና በቂም በቀል ይመለከት የነበረው ሻዕብያና የተሸነፈውን የደርግ ሠራዊት እንደሥጋት ያዩ የነበሩ አንዳንድ የኢሕአዴግ አመራር አባላት ብቻ ናቸው።

በእርግጥ ከ1987 ዓ.ም. ጀምሮ ሠራዊቱ ከፖለቲካ ፓርቲ አባልነት እንዲወጣ በአዋጅ ተደንግጎ፣ የኢሕአዴግ ሠራዊት ለሕገ መንግሥቱ ተገዥ ሆኖ የኢትዮጵያ ሠራዊት ተብሎ ተሰየመ። ሆኖም በተግባር ሲታይ ሠራዊቱ በኢሕአዴግ ቁጥጥር ሥር ሆኖ ቀጥሏል። የፓርቲ አባላት የሚወያዩባቸው አጀንዳዎች ሁሉ ትንሽ ለውጥ ተደርጎባቸው ሠራዊቱም እንዲወያይባቸው ተደርጓል። ዜጎችን ጠላትና ወዳጅ ብሎ የሚከፋፍለውና ፍጹም ሕገ መንግሥቱን የሚጻረረውን የኢሕአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ዕንሰ ሐሳብ ሠራዊቱ እንዲቀበለው ተደርጓል። የኢሕአዴግ የፖለቲካ ውሳኔዎች ሁሉ በበላይ አዛዦችና በፖለቲካ መኮንኖች አማካይነት ሠራዊቱ እንዲወይባቸው ተደርጓል። ሠራዊቱን የፖለቲካ ወገንተኝነት እንዳይኖረው የሚከለክለው ሕገ መንግሥት ከጸደቀ በኋላም በደርግ አመራር ሥር የነበሩትን ተራ ወታደሮችና መኮንኖች ሙያዊ ብቃታቸውን ይዘው ከአዲሱ ሠራዊት ጋራ እንዳይቀላቀሉና እንዳያጠናክሩ የተደረገውም ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ የፖለቲካ አቅጣጫ የተነሣ እንጂ ሕገ መንግሥቱ ስለማይፈቅድላቸው አልነበረም።

14. የሻዕብያና የእነ መለስ በትግራይ መስተዳደር ላይ ሤራ

ሻዕብያዎች የህወሓት አመራር አባላትን በአፍቃሪ ሻዕብያና በሻዕብያ ጠላት ይከፋፍሏቸው ነበር። አፍቃሪ ሻዕብያ ተደርገው ቸሚወሰዱት የህወሓት አመራር አባላት ስብሓት ነጋና መለስ ዜናዊ ግንባር ቀደሞች ነበሩ። በትጥቅ ትግሉ መጀመሪያ ላይ ሻዕብያዎች መለስን በጥርጣሬ እያዩት በሻዕብያና በህወሓት መካከል ይፈጠሩ ለነበሩ አለመግባባቶች ከዓባይ ፀሐዬ ጋራ እያዳበሉት ተጠያቂ ያደርጉት ነበር። ሆኖም ከ1977 ዓ.ም. እስከ 1980 ዓ.ም. ድርጅቱ ከሻዕብያ ጋራ ግንኙነት ባቋረጠበት ጊዜ ሳይቀር፣ መለስ የማሌሊት የፕሮፓጋንዳ ኃላፊ እያለ ከሻዕብያዎች በላይ ለኤርትራ ተቆርቋሪ ሆኖ ይጽፋቸው የነበሩትን ጽሑፎች በምዕራፍ ሁለት አውስቻለሁ። የማሌሊትንና የህወሓትን ሊቀመንበርነት ከተቆጣጠረበት ከ1981 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ ከሻዕብያዎች ጋራ የሚደረጉ ድርድሮችንና ግንኙነቶችን ሲመራ ሻዕብያዎች ጽሑፉን ብቻ ሳይሆን ልቡንም አንብበውት ታማኝ ወዳጅ አድርገውት ነበር። ያም ሆኖም ግን መለስን የስብሓትን ያህል አይወዱትም ነበር። ሻዕብያዎች ስብሓትን በቀይ ኮከብ ዘመቻ ወቅት የህወሓት ሊቀመንበር ሳለ ትልቅ ኃይል እንዲላክላቸው በማድረጉ ከሽንፈትና ከመበታተን እንዳዳናቸው ታላቅ አባትና ባለውለታ ይቆጥሩት ነበር። በአጠቃላይ የሻዕብያ መሪዎችና የስለላ አባሎቻቸው ስብሓት የቁርጥ ቀን ወዳጃቸው እንደሆነ እኛም ፊት በይፋ ይናገሩ ነበር።

ሻዕብያዎች ከሁለቱ ወዳጆቻቸው ለስብሓት ያደሉ እንደነበር በወቅቱ በኤርትራ የኢትዮጵያ አምባሳድር የነበረው አውዓሎም ወልዱ ይመሰክራል። በ1987 ዓ.ም. ሻዕብያዎች፣ አውዓሎምና ስብሓት በተገኙበት አንድ ግብዣ አድርገው ነበር። እንደተለመደው ምርጥና ውድ የአልኮል መጠጥ ዓይነቶች እንደ ውሃ እያፈሰሱ ጨዋታው ደርቶ፤ ሳቀና ጫጫታው በርክቶ፤ «*ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል*» እንዲሉ ኢሳያስ አፈወርቂ በልቡ ያመቀውን በይፋ እየተናገረ ስብሓት እጅግ ሞኝና ስነፍ መሪ እንደሆነ በተደጋጋሚ ይገልጻል።

ሥልጣኑን እንደመለስ ዓይነቶች ወጣቶች አሳልፎ እንደሰጠም ይገልጻል። ሥልጣኑን አስጠብቆ ቢሄድ ኖሮ በሻዕብያና በህወሓት መካከል አለመግባባት ላይከሰት ይችል እንደነበርም ይናገራል። እንዲህም ከመለስ የበለጠ ስብሓትን እንደሚወድ የገለጸበት ሁኔታ ነበር። ይህ የኢሳያስ አመለካከት ከሻዕብያ በላይ አመራር ጀምሮ እስከ ተራው አባል ድረስ ተሰራጭቶ አቦይ ስብሓት አባታችን መለስ ዜናዊ ወንድማችን ይባል ነበር።

ሻዕብያዎች በአንጻሩ ከህወሓት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መካከል ዓባይ ፀሐዬን፣ ተወልደ ወልደ ማሪያምን፣ ስዬ አብርሃንና ገብሩ አሥራትን፣ እንደባላንጣ ያዩን ነበር። ዓባይን፣ ሻዕብያዎች ዴሞክራቶች አይደሉም፤ ለሶቭዬት ኢምፔሪያሊዝም የተንበረከኩና ለኤርትራ ነጻነት ጸንተው የማይቆሙ ናቸው የሚለው አቋም ህወሓት ውስጥ ተቀባይነት እንዲያገኝ አድርጓል በሚል ይጠሉታል። ተወልደን እጅግ ቁጥብ፣ የሚያስበው ነገር በቀላሉ የማይታወቅ፣ ከአፉ የሚያወጣቸውን ቃላት ጠንቅቆ ማዳመጥ እንደሚያስፈልገውና በአጠቃላይ እንደ መለስና እንደ ስብሓት ሻዕብያዎች የሚሉትን ሁሉ አሜን ብሎ እንደማይቀበል ሰው ያዩታል። በመሆኑም ድርጅቱ በአመራር ስላስቀመጠውና ከእነርሱ ጋራ እንዲነጋገር ስለሚላክ ብቻ የሚቀበሉት መሪ ነበር። ስዬ መጀመሪያውንም ከሻዕብያ ጋራ ያን ያህል ቀጥተኛ ግንኙነት አልነበረውም። ሆኖም በምዕራፍ ሁለት እንደጠቀስኩት ባዕከር ላይ በተደረገው የጋራ ወታደራዊ ሥራ ከሻዕብያዎች ጋራ እንደተቃቃረና ካርቱም ላይ በተደረገው የሁለቱ ድርጅቶች ግንኙነት የተቋረጠበት ስብሰባ እንደተገኘም ሻዕብያዎች ያውቁ ነበር። ስዬ ከሻዕብያዎች ጋራ ዳግም መነጋገርና መወያተት የጀመረው የህወሓት ሠራዊት አዛዥ ከሆነና በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ የጋራ ወታደራዊ ሥራዎችን ማኪያሄድ ሲጀመር ነበር። በነዚህ አጋጣሚዎች ሻዕብያዎች ስዬ በውስጡ የነበረውን ስሜት ያነበቡት የነበር ይመስላል፤ ቢያንስ የቁርጥ ቀን ወዳጃቸው ሊሆን እንደማይችል ተገንዝበው ነበር።

እኔም ከሻዕብያዎች ጋራ ብዙ ግንኙነት ባይኖረኝም በ1976 ዓ.ም. ባዕከር ላይ የጋራ ወታደራዊ ሥራ ሲከናወን በንብረት ክፍፍል በተነሣው ውዝግብ ተካፋይ ነበርኩ። በ1977 ዓ.ም. ካርቱም ላይ ከሻዕብያጋ ግንኙነት ሲቋረጥም የድርድሩ ተካፋይ ነበርኩ። የህወሓትን ሠራዊቱ ከሳሕል ምሽግ ለማስመለስ የተላከው የልኡካን ቡድን አባል ነበርኩ። ከ1975 ዓ.ም. እስከ 1977 ዓ.ም. ከኤርትራ ጋር የሚያዋስነንን፣ ባድመና ሌሎች አጨቃጫቂ አካባቢዎች የሚገኙበትን፣ ምዕራባዊ ሪጅን /ሪጅን አንድ/ አስተዳዳሪ ነበርኩ፣ በየጊዜው ከሻዕብያ ካድሬዎች ጋር አስተዳደራዊ ውዝግቦች ሲነሡ ነበርኩ። ከዚህ ሌላም በ1977 ዓ.ም. ድርቅ በተከሰተበት ወቅት ሻዕብያዎች ህወሓት በሪጅን አንድ በኩል ወደ ሱዳን የሚያደርገውን የመኪና ጉዞ ሲያሰናክሉ ሌላ ተለዋጭ መንገድ ተሠርቶ የሻዕብያዎች ሜራ እንዲከሽፍ ሲደረግ የሪጅን አንድ አስተዳዳሪ ነበርኩ። በነዚህ ሁሉ ሸካራ ግንኙነቶች ምክንያት ሻዕብያዎች እንደ ሰይጣንና እንደ ጥቅማቸው ተቀናቃኝ ያዩኝ ነበር። በአጭሩ በቀላሉ ፍላጎታቸውን ለማስፈጸም የምችል ሰው እንዳልሆንኩኝ አረጋግጠው ነበር።

የትጥቅ ትግሉ ካበቃ በኋላ የትግራይ ክልል አስተዳዳሪ በነበርኩበት ጊዜ ከኤርትራ ጋራ የነበረን ሰፊና አወዛጋቢ ወሰን ለከፋ ግንኙነት ዳርጎናል። ሻዕብያዎች የኢትዮጵያን ጥቅም እየገዘገዙ የራሳቸውን ጥቅም ለማዳበር መረማመጃ ይሆነናል ብለው ያሰቡት አንዱ አካባቢ የትግራይ ነበር። ሆኖም መስተዳደሩ ደባቸውን በሚገባ ያውቀው ስለነበር ያሰቡትን ለግሳካት ባለመቻላቸው በመስተዳደሩ፣ በተለይ ደግሞ በእኔ ላይ «ገብሩ ፀረ-ኤርትራዊና ፀረ ዴሞክራሲ ነው፤ ገብሩ ትግራይን ማስተዳደር አልቻለም፤ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት እንዲሻክር እያደረገ ነው፤» የሚል የማጥላላት ዘመቻ በተቀናበረ መልኩ ትግራይ ውስጥ በነበረው ቆንስላቸው አማካይነት ያካሂዱ ነበር።

ሻዕብያዎች ይህን ሲያደርጉ ትግራይ ውስጥ የነበሩ ብዙ ኤርትራውያንና የተወሰኑ በሕገ ወጥ መንገድ መከበር የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎችም ተባባሪዎቻቸው ነበሩ። የመለስ አባት አቶ ዜናዊ አስረስም ከነዚህ ተባባሪዎች አንዱ ነበር። በወቅቱ አቶ ዜናዊ መቀሌ ሲመጡ ዐልፎ ዐልፎ የሚያርፉት በኤርትራ ቆንስል ግቢ የሚዝናኑት ከቆንስላው ኃላፊዎች ጋራ ነበር። እኒህ ሰው ከኤርትራ ቆንስላ ጋር ጥብቅ ግንኙነት የመሠረቱት ያለ ምክንያት አልነበረም፤ ከምንም ተነሥተው ሀብታም ነጋዴ ሲሆኑ የቻሉትም ከሻዕብያዎች ጋራ በነበራቸው የጠበቀ የጥቅም ግንኙነት ምክንያት ነበር። አቶ ዜናዊ በትግራይ ኤርትራ የሚመረተው የፋርኖ ዱቄት አከፋፋይ እንዲሆኑ በሻዕብያ ውክልና ተሰጥቷቸው ነበር። ሌሎችም ሸቀጦች ከኤርትራ ወደ ትግራይ እንዲያስገቡ ፈቅደውላቸው ነበር። እንዲህም በትጥቅ ትግሉ ጊዜ ኑሯቸው ተሳሳቁሎ ሁለት አህዮች እየነዱ ሲነግዱ የነበሩት አቶ ዜናዊ ከደርግ ውድቀት በኋላ በሻዕብያዎች ድጋፍ ባለጸጋ ሆኑ። ሻዕብያዎች ለአቶ ዜናዊ ይህን ሲያደርጉላቸው የነበረው ካለምክንያት ሳይሆን ከልጃቸው ከመለስ ጋ የበለጠ ለመቀራረብ መሸጋገሪያ እንዲሆኗቸው ነበር።

አቶ ዜናዊ ከትጥቅ ትግሉ በኋላ ደህና ሀብት እንዳካበቱ በራሳቸው አንደበት አንድ ቃለ ምልልስ ላይ የመለሰን ልጅ ለማስተማር ትንሽ ገንዘብ ባንክ ውስጥ ማጠራቀማቸውን ለመገናኛ ብዙኃን ገልጸዋል።[28] የኢትዮጵያን ጠቅላይ ሚኒስቴር ልጅ በሳንፈርድ የግል ትምህርት ቤት ለማስተማር ከቻሉ ምን ያህል ሀብታም እንደነበሩ መገመት አያቅትም። በኢትዮጵያ በተፈጠረው ፀረ-ሻዕብያ ፖለቲካ ምክንያት ከበለጸጉበት እንቅስቃሴ ተገቱ እንጂ ሰውየው የበለጠ ሀብት ለማካበት ሐሳብ እንደነበራቸው ዓድዋንና አሥመራን በማቆራኘት ጀምረውት የነበረው እንቅስቃሴ ያመለክታል። እኔና የሥራ ባልደረቦቼ አቶ ዜናዊ የጉምርክ ኬላዎችን ጥሰው ለማለፍ ያደርጉ የነበሩትን ሕገ ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ እንዲገታ አድርገናል። በአንድ ወቅት ብቻ አንድ መኪና ሙሉ ሸቀጥ በራማ የጉምሩክ ኬላ በኩል በሕገ ወጥ መንገድ ለማሳለፍ ሲሞክሩ ተይዘባቸው ጉዳዩ እኛ ጋራ ደርሶ ሕጉ በሚፈቅደው እንዲቀጡ ተደርጓል። አቶ ዜናዊ ከሻዕብያ ቆንስላ ጋራ የኛን ስም በማጥፋቱ ዘመቻ የተሰማሩትም በዚሁ ምክንያት ይመስለኛል።

ሻዕብያዎች፣ በተለይ ኢሳያስ ከትግራይ እንድነሣ በጣም ተጣጥሯል፤ *«ገብሩን ከትግራይ አንሡት፤ ትግራይን ማስተዳደር አልቻለም።»* እያለም ለህወሓት አመራር አባላት ሐሳብ ያቀርብ ነበር። የህወሓት አመራር አባልና በኤርትራ የኢትዮጵያ አምባሳደር ለነበረው አውዓሎም ወልዱም ይህን ሐሳብ ሲቀርብለት፤ *«ትግራይን ለማስተዳደር ከእርሱ የተሻለ ሰው የለንም፤ የፖሊትቢሮ አባል እንዲሆን የመረጥነውም በችሎታው ነው፤ በእርሱ ላይ ባንተማመን ኖሮ የትግራይ አስተዳዳሪ አናደርገውም ነበር፤ ስለዚህ የምታቀርበው አስተያየት ትክክል አይደለም።»* ብሎ እንደመለሰለት አጫውቶኛል። አቶ ዜናዊም ከኢሳያስ የሚመሳሰል ጥያቄ ለአውዓሎም ሲያቀርቡለት፤ አውዓሎም ጥያቄውን እያነሡ ያሉት ከሻዕብያ የሚያገኙት ጥቅም እንዳይቀርባቸው እንደሆነ በግልጽ ነግሯቸዋል። አኪያሂዳቸው እንደማይጠቅማቸው፣ ሻዕብያዎችም ጥቅም እየሰጧቸው ያሉት በመለስ ምክንያት እንደሆነና የሚያደርጉትን ካላቆሙ የልጃቸው ስም እንደሚጠፋ ገልጸላቸው ነበር።

ጉዳዩ መለስም የነበረበት እንደሆነ ከክፍፍሉ በኋላ ተወልደ ወልደ ማሪያም ሲያወጋኝ፤ መለስ *«ገብሩን ከትግራይ መስተዳድር አንሥተን በዓለም ሰገድ ገብረ አምላክ ብንተካው ይሻላል።»* ብሎት እንደነበርና ይህን ሐሳቡን እንዳልተቀበለው ነግሮኛል። ሌላም በታጠቅ የካድሬ ማሠልጠኛ ማዕከል፣ የኢሕአዴግ ጽሕፈት ቤት ሰዎች የተሳተፉበት እኔን ከትግራይ

[28] በጋዜጠኛ ብርሃነ ንጉሤና ባልደረቦቹ አዘጋጅነት ሲታተም የነበረው «ኢንፎንተይመንት» የሚባል መጽሔት ጋራ ካደረጉት ቃል ምልልስ የተወሰደ

ለማንሣት የተሠራ ድራማ ነበር። ታጠቅ ጦር ሰፈር የካድሬ ማሠልጠኛ ማዕከል ሆኖ ያገለግል በነበረበት ወቅት፣ የትግራይ ካድሬዎች በማዕከሉ በዙር እየተላኩ ይሠለጥኑ ነበር። በሥልጠናው የተለያዩ ጉዳዮች እተየነሡ ውይይት ይደረግባቸው ነበር። በአንዱ የሥልጠና ዙር «ትግራይ ውስጥ ዴሞክራሲ የለም» የሚል ርእስ ለውይይት ቀርቦ፣ ይህን መነሻ ለማስረገጥና ወደ ጭብጥ ለመለወጥ ሠልጣኞቹ ካድሬዎች ጉዳዩን በጥልቀት እንዲወያዩበት ተወተወቱ። ካድሬዎቹም ሕዝቡን በሚገባ እንደማያስተናግዱ፣ ፍትሐዊ አስተዳደር እንደማይሰጡ፣ አቤቱታ አቅራቢዎችን እንደሚያጉላሉ፣ በሂስና በግምገማ ሕዝቡን እንደሚያስጨንቁ፣ ዐልፎ ዐልፎም ገበሬውን እንደሚያመናጭቁ፣ እንደሚደበድቡና እንደሚያስሩ ተናዘዙ። እንዲያውም በየቀበሌውና በየቀዬው ቁጥር ስፍር የሌላቸው ገበሬዎችን እንዳሻቸው እንደሚያስሯቸውና እንደሚቀጧቸው አመኑ። በዚህ ጊዜ ጥቂት ካድሬዎች ብቻ እየተባለ ያለው ትክክል አይደለም፤ ዐልፎ ዐልፎ በማስገደድ የማሠራት ክስተት ቢታይም በሚገለጸው ደረጃ ፀረ-ዴሞክራሲ አሠራር የለም፤ ብለው ተቃውመው ተከራከሩ። ሆኖም የነዚህ ሐሳብ ተሰሚነት ሳያገኝ ቀርቶ ውይይቱ፣ «ትግራይ ውስጥ ዴሞክራሲ የለም» በሚለው ተደመደመ። ይህን ውይይት በቀጥታ ይመራው የነበረው የኢሕአዴግ የፕሮፓጋንዳ ኃላፊ ዓለም ሰገድ ገብረ አምላክ ነበር።

ከላይ የተጠቀሰው ትግራይ ውስጥ አለ የተባለው ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ክስተት ለመለስ ተላልፎ እንደተለመደው ለኢሕአዴግ ጽሕፈት ቤትም ሪፓርት ተደረገ። የኢሕአዴግ ጽሕፈት ቤት፣ በተለይ ተወልደ ወልደ ማሪያም፣ በካድሬው ትምህርት ቤት የተደረገውን ግምገማ መሠረት በማድረግ የትግራይ መስተዳድር ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ለመድረስ ስለተቸገረ ይህን ጉዳይ ከትግራይ መስተዳድር ጋራ ለማየት ወሰኖ የጋራ ስብሰባ እንድናኪያሂድ ጠየቀን። በጥያቄው መሠረትም ትግራይ የነበርነው የመስተዳድሩ ኮሚቴ አባላት አዲስ አበባ መጥተን የኢሕአዴግ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች፣ በተለይ ተወልደ ወልደ ማሪያምና ዓለም ሰገድ ገብረ አምላክ በተገኙበት ኢሕአዴግ ጽሕፈት ውስጥ ስብሰባ አኪያሄድን። የስብሰባው አጀንዳ በካድሬ ትምህርት ቤት የተነሡት ጥያቄዎች ላይ የሚያተኩር ነበር። ቀደም ብለን ጉዳዩን ሰምተን የነበርነው የትግራይ መስተዳደር አባላት፤ ዓለም ሰገድ ገብረ አምላክ በዝርዝር ያቀረበውን ሪፓርት አዳመጥን። ከዚያም የመስተዳድሩ አባላት፣ በተለይ እኔ በንዴትና በቁጣ መልስ መስጠት ጀመርኩ። ይህ ሪፓርት በአዲስ አበባ የሚገኙ አንዳንድ ጽንፈኛ ጋዜጦች በትግራይ መስተዳድርና ሕዝብ ላይ ከሚያሰራጩት የተለየ ስላልሆነ፣ ገለጻውን ከነዚህ ጋዜጦች ብንሰማው በተሻለ ነበር፤ ብዬም ጉዳዩ ከኢሕአዴግ ከፍተኛ አመራር መምጣቱ እጅግ እንዳስገረመኝ ተናገርኩ። ዓለም ሰገድም በረጋ መንፈስ ከጽንፈኛ ጋዜጦች ጋራ መመሳሰሉ ትክክል እንዳልሆነ ገለጸ። እኔም ውይይቱ ከቅን አስተሳሰብ የተነሣ ሳይሆን፤ በትግራይ ዴሞክራሲ የለም ከሚለው ድምዳሜ ተነሥቶ ጭብጥ ለማሰባሰብ የተቀናበረ እንደሆነ ተናገርኩ። በተጨማሪም ካድሬውን ያተፈለገው አቅጣጫ ለመንዳትና የተፈለገውን ድምዳሜ እንዲደግፍ ለማድረግ እንደሚቻልና፤ ከተፈለገም ካድሬው ይህን የደረሰበትን ድምዳሜ እንዲለውጥ ለማድረግ እንደሚቻል ገለጽኩ።

ይህን ከፍተኛ ንትርክ የተሞላበትን ስብሰባ ሲመራ የነበረው ተወልደ ወልደ ማሪያም አንዱ ወይም ሌላው በሚያቀርበው አስተያየት ላይ ተንተርሶ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ባለመቻሉ ጉዳዩን በካድሬ ትምህርት ቤት በተደረገው ውይይት ላይ ብቻ ከመመሥረት ይልቅ መሬት ላይ ያለውንም ሁኔታ ማየት አለብን የሚል ሐሳብ አቀረበ። አንድ አጥኚ ቡድን ተቋቁሞ እውን ትግራይ ውስጥ በሚባለው ደረጃ የዴሞክራሲ ረገጣ አለ ወይስ የለም የሚለውን ማጣራት አለብን ተባለ። የትግራይ መስተዳደርም በዚህ ተስማማ። ወዲያውኑ ከኢሕአዴግ ጽሕፈት ቤት ተወልደ ወልደ ማሪያም፣ ከትግራይ መስተዳደር ገብሩና አለቃ

ጸጋይ በርሀ የምንገኝበት ቡድን ተቋቁሞ ጉዳዩን እንዲያጠናና ግኝቱን ለውሳኔ እንዲያቀርብ ስምምነት ላይ ተደረሰ። ቡዱኑ ሌሎች አባላትንም አካቶ ወደ ትግራይ ተጉዞ በተለያዩ የትግራይ የገጠር ማዕከላትና በከተማ ጥናት እንዲኪያሂድ፣ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችንና የድርጅት አባላትንም እንዲያነጋግር ተወሰነ።

በስምምነቱ መሠረት ቡድኑ ትግራይ ውስጥ በሽሬ እንዳ ሥላሴ፣ በወርቃምባና በአካባቢው፣ በአፅቢ፣ በራያ አካባቢ፣ ለቀናት የዘለቀ ሰፊ እንቅስቃሴ አደረገ። ሚሊሺያዎች፣ የቀበሌ አስተዳዳሪዎች፣ የድርጅት አባላት፣ የማኅበራት መሪዎች፣ የሕዝብ ተወካዮች፣ ወዘተ... ያለ ምንም ተጽዕኖ በመስተዳደሩ አሠራር፣ አደረጃጀት፣ ውሳኔ አሰጣጥና የአስተዳደር ቅልጥፍና፣ ወዘተ... ያላቸውን ቅሬታ እንዲያቀርቡ ተጠየቁ። ጥናቱ የሚኪያሄደው የአመራርና የአሠራር ማስተካከል ለማድረግ እንደሆነም ተነግሯቸው የሚያውቁትንና የሚሰማቸውን ሁሉ በግልጽ እንዲናገሩ ተደረገ።

በዚህ በርካታ ቀናትን በወሰደ ጥናት መሠረታዊ የዴሞክራሲ ጥሰት እንደሌለ፣ መጠነኛ ግድፈቶችና ስሕተቶች ግን እንዳሉ ተረጋገጠ። ካድሬው በታጠቅ ጦር ሰፈር የተናገረውና መሬት ላይ ያለው ሁኔታ የማይጣጣሙ መሆናቸውም ይፋ ሆነ። ከዚህ በኋላ ከጥናቱ ቡድን ተወልደና ገብሩ፣ አዲስ አበባ ከነበሩት ዓለም ሰገድና መለስ ጋራ ስለጉዳዩ ለመነጋገር በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ስብሰባ ተቀመጥን። ትግራይ ውስጥ የተደረገው ጥናትና ግኝቱ በዝርዝር ቀረበ። መለስ ረዘም ያለውን ዘገባ ካዳመጠ በኋላ፣ «*እንግዲህ በትግራይ የተደረገው ጥናት መሠረታዊ የዴሞክራሲ ጥሰት እንደሌለ ያመለክታል፤ ከካድሬ ትምህርት ቤቱ የተገኘው መረጃ ደግሞ መሠረታዊ የዴሞክራሲ ችግር እንዳለ ያመለክታል፤ ሁለት ጭብጦች አግኝተናል፤ ጭብጦቹ ሁለት ስለሆኑም በአንዱ ወይም በሌላው መተማመን አይቻልም፤ ስለዚህ ሁለቱን ጭብጦች ይዘን መቀጠል ይኖርብናል*» አለ። በበኩሌ በዚህ ማጠቃለያ በፍጹም እንደማልስማማ ገልጬ፣ «*ሁለቱ ጭብጦች አብረው የሚሄዱ ስላልሆኑ ጉዳዩ በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ ማሰሪያ ማግኘት አለበት፤ የተሰጠውም አስተያየት ትክክል አይደለም*፤» ብዬ ተናገርኩ። ሆኖም ተወልደና ዓለም ሰገድ የመለስን ድምዳሜ ስለተቀበሉ በጉዳዩ ስምምነት ላይ ሳንደርስ ተለያየን። አሁን መለስ ብዬ ሳየው፣ በተለይ ደግሞ አውዓሎምና ተወልደ መለስና ኢሳያስ አሉት ብለው የነገሩኝን ሳገናዝበው፣ መለስ እኔን ከትግራይ መስተዳድር ለማንሣት የሸረበው ሤራ እንደነበር ምንም ጥርጣሬ የለኝም።

እግረ መንገዴን ማንሣት ያለብኝ መሠረታዊ ነገር ግን አለ። ይኸውም፣ በወቅቱ በትግራይ ዴሞክራሲ አለ ወይስ የለም የሚለው ጥያቄ የተነሣበት አቅጣጫ ፍጹም የተሳሳተ ቢሆንም፣ ጥያቄውን አሁን ካለኝ የዴሞክራሲ ግንዛቤ አንጻር ብመለከተው ኖሮ በትግራይ ሆነ ባጠቃላይ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ እንዳልነበር ለመገንዘብ ባልተቸገርኩ ነበር። የያኔው የመለስና የኛ አመራር ጥልቅ ስለሆነው የዴሞክራሲ ፅንሰ ሐሳብና ንድፈ ሐሳብ የነበረን ግንዛቤ ፍጹም የተሳሳተ ነበር። በወቅቱ ስንከተለው የነበረው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እምነታችን የአንድ ፓርቲን የበላይነት፣ የፓርቲውን ግንባር ቀደም መሪነት፣ የዴሞክራሲን ከመደብ ጋራ መያያዘ፣ ዴሞክራሲ ለወዳጅና ለጭቁን መደቦች እንጂ ለጨቋኝ መደቦች የማይሰጥ መሆኑን፣ ያስተምር ነበር። ከዚህ ሌላ፣ በተቋም ደረጃ፣ መሪው ፓርቲ ሁሉንም የመንግሥት ተቋማት፣ ማለትም ፓርላማንና የክልል ምክር ቤቶችን፣ ሥራ አስፈጻሚውን፣ የፍትሕና የጸጥታን አካላት መቆጣጠር እንዳለበት እናምን ነበር። መሪ ፓርቲያችን የሲቪል ማኅበረሰቡንና ኅብረተሰቡን በአጠቃላይ በቁጥጥሩና በተጽዕኖው ሥር ማስገባት እንዳለበትም እናምን ነበር። ነጻ ጋዜጣና ሚዲያ መኖሩ ከዓላማችን ጋራ የሚጋጭ ነበር። በአጠቃላይ ከመሪ ፓርቲው ዕይታ ውጭ ያሉ እንቅስቃሴዎች በሙሉ መገደብ እንዳለባቸውና በቁጥጥር መዋል እንዳለባቸው እናምን ነበር። ይህን እምነት እየተከተልን የመንግሥት አካላት አንዱ

ሌላውን የሚቆጣጠርበት፣ የብዙኃን ፓርቲ ሥርዓት የሚሰፍንበት፣ ሥልጣን ፍትሐዊና ነጻ በሆነ ምርጫ የሚጨበጥበት፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሠርተናል ሊባል አይቻልም። ከዚህ አኳያ ሲታይ ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች ይከበሩ ነበር ለማለት አይቻልም። የፓርቲው አኪያሄድ እንዲህ ከነበረ ደግሞ በፀረ-ዴሞክራትነት ሊጠየቅ የሚገባው የትግራይ መስተዳደር ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ አገሪቱን ይመራ የነበረው ኢሕአዴግና የዚህ ፓርቲ የበላይ አመራር የነበረው ሥራ አስፈጻሚውና ማዕከላዊ ኮሚቴው በአጠቃላይ ነበሩ። በግለሰብ ደረጃ ከታየም ለዚህ የዴሞክራሲ ችግር በይበልጥ ኃላፊነት መውሰድ የነበረበትም ፓርቲውን፣ መንግሥቱንና ሠራዊቱን የሚመራው መለስ መሆን ነበረበት።

የዴሞክራሲ ጥያቄ በሻዕብያ በነመለስና በተባባሪ ነጋዴዎች የተነሣበትን ምክንያት ከላይ ለመጠቆም ሞክሪያለሁ። የተጠቀሱት ወገኖች የዴሞክራሲ ጥያቄ ያነሡ የነበሩት የሻዕብያን የዝርፊያና የውንብድና እንቅስቃሴ እያደናቀፈ የነበረውን የትግራይ መስተዳድር በተለይ ገብሩን ለማንሣት እንደነበር መገንዘብ አይያስቸግርም። ሻዕብያዎችና መለስ በካድሬው ትምህርት ቤትና በአንዳንድ ነጋዴዎች አማካይነት ያደረጉት እንቅስቃሴ ሳይሰምር ቢቀርም እንቅስቃሴያቸው ግን አላቋረጠም ነበር። ያሰቡትን ዓላማ ግብ ላይ ለማድረስም በተጠናከረ መንገድ ተደራጅተው ቀጥለውበት እንዲያውም ጉዳዩን ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር በአስገራሚ ሁኔታ ማዕከላዊ ኮሚቴው ውሳኔ እንዲሰጥበት ለማድርግ ሞክረው እንደነበር ከዚህ በታች ከቀረበው ዝርዝር መገንዘብ ይቻላል።

በ1988 ዓ.ም· እና በ1989 ዓ.ም· ከሻዕብያ ጋራ የነበረው ግንኙነት እጅግ ሻክሮ ነበር። ለግንኙነቱ መሻከር ምክንያት አንዱም ሻዕብያዎች የኢትዮጵያን ኬላዎችና ድንበሮች እየጣሱ ሰፊ የኮንትሮባንድ ዘመቻ ማጧጧፋቸው ነበር። ሻዕብያዎች ቀደም ሲል ከተገለጸው የሰሊጥና የቡና ዝርፊያ በተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ ያስገኛሉ የተባሉን ሸቀጦች ሕጋዊና ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ መዝረራቸውን ተያይዘውት ነበር። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከባህላዊ ወርቅ አምራቾች ወርቅ አልገዛም የሚል ፖሊሲ ይከተል ስለነበርና ገዢዎችን ብቻ ሳይሆን አምርተው የሚሸጡትንም በሕገ ወጥነት ይመለከታቸው ስለነበር ለሻዕብያ እጅግ አመቺ ሁኔታ ተፈጥሮለት ነበር። በትግራይ ምዕራባዊ ዞን በባህላዊ መንገድ ወርቅ እየተመረተ በዓመት ቢያንስ ከሦስት እስከ አራት ኩንታል ይሰበሰብ ነበር። ይህን ወርቅ ብሔራዊ ባንክ ስለማይገዛው፣ የተወሰነውን ትግራይ ውስጥ ወርቅ ሠሪዎች ይገዙት ነበር። ሻዕብያ ደግሞ የኢትዮጵያን ብር ወደ ወርቅ ለመለወጥ እየተሯሯጠ፣ ግዥውን በድብቅ አሟጥፎት ነበር። ከዚህ ሌላ የውጭ ምንዛሬ ያስገኙልኛል የሚላቸውን የቁም ከብቶችንና ቆዳና ሌጦ ይዘው ኬላዎችን ሰብረው ድንበር ተሻግረው ኤርትራ ውስጥ ጥሩ ዋጋ ያገኙባቸው ነበር። በዚህ አግባብም ሻዕብያ ብዙ የኢትዮጵያን ሀብት ዘርፏል። እንዲሁም በኬላዎች በሚደረገው እንቅስቃሴ ዐልፎ ዐልፎ ከጉምሩክ ሠራተኞችጋ በመመሳጠር፣ ዐልፎ ዐልፎም ሕጋዊ በማስመሰል ቡናና ሌሎች የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ ሸቀጦች ዘርፏል።

ይህን የሻዕብያ የዘረፋ ዘመቻ የተገነዘብነው የትግራይ መስተዳደርም ሁኔታውን ለመግታት የተለያዩ መመሪያዎችን እናወጣ ነበር። በመመሪያው መሠረት ብዙ ሚሊሺያዎች ወደ ኤርትራ ሊገቡ የተንቀሳቀሱትን የኢትዮጵያ ጥሬ ዕቃዎችን በመቆጣጠር ከፍተኛ ውጤት አስገኝተዋል። የጉምሩክና የድንበር ጸጥታ ሠራተኞችም ጠበቅ ያለ ፍተሻና ቁጥጥር ያደርጉ ነበር። ይህ አሠራር በሰዎች ላይ መጉላላትንና ጫና ቢፈጥርም ተግባራዊ የሆነው የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ እንጂ ሆን ተብሎ ኤርትራውያንን ለማጉላላት አልነበረም።

ይህ የትግራይ መስተዳድር ያወጣው መመሪያና ያደረገው እንቅስቃሴ በሻዕብያ ዘንድ በበጎ አልታየም ነበር። ለነገሩ ሻዕብያዎች በኢትዮጵያውያን ላይ የሚያደርሱት መጉላላትና ወከባ

እጅግ የከፋና ትግራይ ውስጥ ይፈጸማል ከሚባለው ጋር ፍጹም የማይመጣጠን ነበር። ሁኔታው ይህ ሆኖ እያለ ሻዕብያዎች የትግራይ መስተዳደር በተለይ ገብሩ ጉሮሮአችንን አንቆ፤ የሕዝብ ለሕዝቡን ግንኙነቱን እያሻከረ ነው፤ የኤርትራውያንንም ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን እየጣሰ ነው በማለት በሰፊው ማስወራት ጀመሩ። ቀደም ሲል የተጠቀሱት በኮንትሮባንድ የተሰማሩት የትግራይ ሰዎችም ይህን የሻዕብያ ወሬ ማስተጋባት ጀመሩ። ነገሩ በዚህ ሳያቆም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስም ይህን የኢሳያስን ሐሜታ ተቀብሎ በ1989 ዓ.ም. በተደረገው የህወሓት የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ነገሩን አንጸባረቀው።

በተለያዩ ጉዳዩች ላይ ለመነጋገር በአራት ኪሎ ቤተ መንግሥት በሚገኘው መሰብሰቢያ አዳራሽ የተሰየመው የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ልዩ ረዳትና የቅርብ ቤተሰብ የሆነው ሙሉጌታ ዓለም ሰገድና በሙሉጌታ ገብረ ሕይወት /ጫልቱ/ ተመሳሳይ አስተያየቶች ሰነዘሩ። ይኸውም ኤርትራውያን በኢትዮጵያ ኬላ ላይ ከፍተኛ መጉላላት እየደረሰባቸው ነው፤ ዴሞክራሲያዊ መብታቸው እየተጣሰ ነው፤ የያዙትን አንድ ኪሎ ቡና ሳይቀር እየተነጠቁ ነው፤ ጋቢና ሌላ ጨርቃ ጨርቅም እንዳይወስዱ ይከለከላሉ፤ የሚሉ አስተያየቶች አቀረቡ። ክንፈ ገብረ መድኅንም ለተሰጠው አስተያየት ድጋፍ በመስጠት ተጨማሪ አስተያየት ሰነዘረ። እነዚህን አስተያየቶች ካዳመጥኩ በኋላ በቁጣ መንፈስ መልስ መስጠት ጀመርኩ፤ «*እውነት በዚህ በምታነሡት ጉዳይ ለመነጋገር ትፈልጋላችሁን? ከሆነማ እኔም እያነሣችሁት ካላችሁት የኤርትራውያን መብት ረገጣና የዴሞክራሲ ጥሰት የበለጠውን የአገራችን ሉዓላዊነት በሻዕብያ መጣስ ጉዳይ በአጀንዳ እንዲያዝልኝ እፈልጋለሁ*» አልኩኝ። እንደ ዛሬ አያድርገውና አለቃ ጸጋይ በርሄም ከእኔው ተመሳሳይ አቋም *ይዞ* እጅግ ተናዶ ነበር። ሌሎች የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትም እንዲሁ ተባሳጭተው ነበር። ነገሩ ወደ ጭቅጭቅና ንትርክ ስላመራ ስዬ ጣልቃ ገብቶ ይህ ጉዳይ እንዲሁ በግብታዊነት የምንነጋገርበት ስላልሆነ ሌላ ጊዜ እንየው የሚል ሐሳብ አቅርቦ ሐሳቡ በሁለቱም በኩል ተቀባይነት አግኝቶ ጉዳዩ ሳይቋጭ ተለያየን። ይህ ሁሉ ሲሆን መለስ ምንም አልተናገረም ነበር። ያልተናገረውም የሚናገሩለትን አበጅቶ ስለነበር እንደሆነ እገምታለሁ። እንዲህም በዚህ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ለማስረገጥ የተፈለገው የትግራይ መስተዳድር ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ነው የሚለው ውሳኔ ሳይተላለፍ ቀረ፤ እነ መለስ መስተዳድሩን በፈለጉት የሰው ኃይል ለማደራጀት የተለሙት ዕቅድም ከሸፈ።

15. የቻይና ጉዟችንና የኤርትራን ተቃዋሚዎች ለማባረር መሞከሩ

የቻይና ኮምዩኒስት ፓርቲ ለኢሕአዴግ ባደረገው የጉብኝት ጥሪ መሠረት በ1987 ዓ.ም. አንድ የኢሕአዴግ ከፍተኛ ቡድን ወደ ቻይና ተልኮ ነበር። ቡድኑ በተወልደ ወልደ ማሪያም ይመራ የነበረ ሲሆን፣ ዓለም ሰገድ ገብረ አምላክን፣ አዲሱ ለገሰን፣ ኩማ ደመቅሳን፣ በረኸት ስምኦንን፣ ኃይለ ኪሮስ ገሰሰንና ገብሩ አሥራትን ያካተተ ነበር። የጉብኝቱ ዓላማም ከቻይና ኮምዩኒስት ፓርቲ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ልምድ ለመቅሰም ነበር። ይህን ዓላማ ለማሳካት ቡድኑ የተለያዩ የቻይና ግዛቶችን ማለትም ቤጅንግን፣ ሴችዋንን፣ ጓንግሺንና ታንጂንን ጎብኝቶ በነዚህ ግዛቶች የኢንዱስትሪ፣ የግብርናና የትምህርት ተቋማት፣ የመሠረተ ልማት፣ የሕዝቡን ባህላዊ እንቅስቃሴዎች፣ ወዘተ... ተመልክቷል።

ቻይና ይወራ እንደነበረው በኢኮኖሚ ኋላ ቀር ሳትሆን በከፍተኛ የእድገት ጉዞ ላይ የነበረችና የኢኮኖሚ እድገቷም እጅግ ፈጣንና ዘርፈ ብዙ የነበረ መሆኑን ቡድኑ ለማየት ችሏል። በቻይና ዝቅተኛ የሚባለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በቤተሰብ ደረጃ የሚካሄደው ሲሆን በመንግሥትና በጎብረት ሥራ ማኅበራት የሚካሄደው ግን እጅግ ግዙፍና ስፋት

ያለው ነበር። በቻይና በአገራችን እንደሚደረገው ትንሹንም ትልቁንም እንቅስቃሴ በቴሌቪዥን መስኮት እያሳዩ እድገት እያስመዘገብን ነው ማለት ሳይሆን ሁሉም የፓርቲው አመራርና ዜጋ ግቡን ለማሳካት በተጨባጭ የሚፍጨረጨርና የተሻላ ኑሮ ለማስመዝገብ የሚጥርበት ሁኔታ ነበር። የተገኘውም ለውጥ በተጨባጭ በዓይን የሚታይና በእጅ የሚዳሰስ ነበር። አውራ ጎዳናዎቹ ሁሉ የግንባታ መሣሪያዎችንና ዕቃዎችን በሚያመላልሱ ተሽከርካሪዎች የተሞሉ ነበሩ። ቢስክሌቶችና መኪኖችም ይጎርፉ ነበር። የልማቱ እንቅስቃሴ የማይታይበት አካባቢ ከቶ አልነበረም። ያም ሆኖ የፓርቲው መሪዎችም የቻይና የነፍስ ወከፍ ገቢ ከአንድ ሺሕ የአሜሪካ ዶላር እንደማይበልጥ ይናገሩ ነበር።

በወቅቱ ቻይናዎች እድገታቸውን አፋጥነውና ዘላቂነት እንዲኖረው አድርገው አገራቸው በሻያ ዓመታት ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንደምትሰለፍ ይገልጹን ነበር። መካከለኛ ገቢ ማለት ምንድን ነው? ስንላቸውም የዚያን ወቅት የስፔይን የነፍስ ወከፍ ገቢን ያህል ነው ይሉን ነበር። ቻይና መካከለኛ ገቢ ያላት አገር ከሆነች በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ቦታ እንደሚኖራትና ይህን ለማሳካት የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወኑ እንደሆነ ይነግሩን ነበር። ትኩረት ካደረጉባቸው ሥራዎች መኻልም የቴሌቪዥን ግምረቻቸውን አሳይተውን ነበር። ቻይናን በጎበኘንበት ጊዜ ቴሌቪዥን ሙሉ በሙሉ በራሳቸው ቴክኖሎጂ ባያመርቱም ከጥቂት ዓመታት በኋላ ራሳቸውን እንደሚችሉ ነበር። ይህን ለማድረግ የመረጡት ዘዴም ከጃፓን የቴሌቪዥን አምራች ኩባንያ ጋ ስምምነት አድርገው በጋራ ቴሌቪዥን አምርተው በቻይና መሸጥ ነበር። ጃፓኖች የቻይናን ገበያ ሲያገኙ፣ ቻይናዎች ደግሞ ቴክኖሎጂውን በማግኘታቸው ስምምነቱ ለሁለቱም ጠቃሚ ነበር። በዚህ መሠረት፣ ሥራው ሲጀመር ጃፓን ሰማንያ በመቶ የቴክኖሎጂው ባለቤት፣ ቻይና ደግሞ ኻያ በመቶ የቴክኖሎጂው ባለቤት ነበሩ። እኛ ፋብሪካውን በጎበኘንበት ጊዜ፣ ቻይና ስድሳ በመቶ፣ ጃፓን አርባ በመቶ የቴክኖሎጂው ባለቤቶች ነበሩ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ቻይና ሰማንያ በመቶውን፣ ጃፓን ደግሞ ኻያ በመቶውን እንደሚይዙ ገልጸውልን ነበር:: በመጨረሻም ቻይና መቶ በመቶ ቴክኖሎጂውን እንድትቆጣጠርና ጃፓን ሥራውን በሙሉ እንድታስረክብ ተስማምተው፣ በመቶ ሚልዮኖች የሚቆጠሩ የቻይና ቤተሰቦችን የቴሌቪዥን ተጠቃሚ ለማድረግ ዐቅደው ነበር።

ቻይናውያን በሌሎች መስኮችም በምርምር እየተደገፉ የቴክኖሎጂ ባለቤት ለመሆን ይሯሯጡ ነበር። ለምርምር የሚመድቡት ገንዘብና የሚሰጡት ትኩረት ከፍተኛ እንደሆነና የምርምራቸው ውጤት ላይ እንደሚያተኩሩም ለመገንዘብ ችለን ነበር። ለእድገት ቆርጠው በመነሣታቸውም ሊሠሩት ያቀዱትን ሁሉ ተግባራዊ ያደርጉ እንደነበር ተመልክተናል። ቻይናውያን በኢኮኖሚው ዘርፍ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረጉ የነበሩ ቢሆኑም በፖለቲካው ረገድ ግን ይከተሉት የነበረው የአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነትን ወይም አምባገነንነትን የሚያጎላ አቅጣጫ ነበር። የአገራቸው ሥርዓት ሶሻሊስት እንደሆነ እየገለጹልን በገበያ የሚመራ ምርትና ንግድ እንደሚያካሂድ ይነግሩን ነበር። በአጠራርም ዐልፎ ዐልፎ በገበያ ላይ የተመሠረተ ሶሻሊዝም *(market based socialism)* እንደሚከተሉ ይገልጹልን ነበር። ሥርዓታቸው ሶሻሊስት ካሉት የአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝም አብሮ የሚሄድ ነበር። በአገሪቱ መረጋጋትና እንዲኖርም የአንድ ፓርቲ ሥርዓት መቀጠል እንዳለበት፣ ኢኮኖሚያቸውም ዘጠና በመቶ በመንግሥትና በጎብረት ሥራ ማኅበራት /በእነርሱ አነጋገር በሕዝቡ/ እጅ እንደሆነ ይናገሩ ነበር።

ቻይናዎች የሚከተሉት ሥርዓት ለጎብረ ፓርቲያዊ ሥርዓት አደረጃጀት ፍጹም ቦታ እይሰጥም ነበር:: እንዲያውም እ.አ.አ. በ1989 ዓ.ም· የተኪያሄደው የቲያንአንሜን አደባባይ ዕልቂት ሥርዓቱ እንዳይናጋ የተፈጸመ እንደሆነ ይገልጹልን ነበር። የቲያናንአንሜን ዕልቂት

በ1989 ዓ.ም· የቻይና ተማሪዎችና ሲቪል ኅብረተሰቡ አገራቸው ውስጥ የፖለቲካ ነጻነት እንዲኖር በመጠየቅ ሰልፍ ወጥተው በታንክና በሌሎች የጦር መሣሪያዎች የታጨዱበትና በግፍ ያለቁበት ነበር። በዚህ ድርጊታቸው ዓለም በሙሉ ቢያወግዛቸውም ለጋራ ደኅንነታችን ስንል የወሰድነው ተገቢ እርምጃ ነው ይሉን ነበር። የቻይና ኮምዩኒስት ፓርቲ ከፍተኛ የአመራር አባላት በግል ስለሰልፉ ሲያወሩን ስሕተት እንደተፈጸመ ቢያምኑም የስሕተቱ ምንጭ የሥርዓቱ ኢ-ዴሞክራሲያዊነት ሳይሆን ሰላማዊ ሰልፍ የመበተንና የመቆጣጠር ልምድ አለመኖር ነው ይሉ ነበር። ሆኖም ስለቲያንአንሜኑ ሰልፍ በግልጽ እንዲወራ አይፈልጉም ነበር፤ ከዚያም በኋላ ሰላማዊ ሰልፍና የግል ተቃውሞንም አልፈቀዱም። ቻይናዎች በዚህ የእድገት ደረጃችን ሊበታትነን የሚችል ነጻነትና መብት መፍቀድ አንችልም፤ ይህን ማድረግ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ይከተናል፤ ይላሉ። ይህን ይበሉ እንጂ በፖለቲካው ረገድ አገራቱ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የማይከበሩባትና የአንድ ፓርቲው አገዛዝ፣ ሙስናና ብልሹ አስተዳደር እንዲንሰራፋ የሚጋብዝበት ሁኔታ እንዳለባት ተገንዝበን ነበር። ለምሳሌ በአንድ ትንሽ ግዛት ውስጥ አንድ ግለሰብ ከተራ ሠራተኛነት ተነሥቶ የሲሚንቶ ፋብሪካ እንዳቋቋመ እየገለጹልን እንደ አርአያ ይጠቅሱት ነበር። ይህ ሰው ከጥቂት ዓመታት በፊት የአንድ የኮምዩኒስት ፓርቲ መለስተኛ ባለሥልጣን ሹፌር ነበር። በአጭር ጊዜ ባደረገው እንቅስቃሴ ግን ሚልዮኔር ለመሆን እንደበቃ ነገሩን። ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ አንዱ አስጎብኚአችንን ስንጠይቀው ከባለሥልጣናቱ ጋራ ተሻርኮ ያገኘው ሀብት ሊሆን ይችላል ብሎ መለሰልን። ከዚህ አንጻር ምን ያህሉ የኮምዩኒስት ፓርቲው ባለሥልጣናት ሀብት እያካበቱና በሙስና እየተዘፈቁ እንደሆነ መገመት አያስቸግርም ነበር። መንግሥት በሙስና የተዘፈቁን የፓርቲ አባላት በሞት ሳይቀር እቀጣለሁ ቢልም በሥርዓቱ ከፍተኛ ሙስና እንደሰፈነም ግልጽ ነበር።

ወደ ቻይና የተጓዝነው ልኡካን ወደ አገራችን ከተመለስን በኋላ በኢንዱስትሪ ልማት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና በምርምር ረገድ ከቻይና የቀሰምነውን ልምድ በመቀመር መወሰድ ያለበትን ተሞክሮ ብናስቀምጥም ሻምገማችን በኢሕአዴግ አመራር በኩል እምብዛም ትኩረት አልተሰጠውም። ፓርቲውን የሚመራው የድርጅቱ የመንግሥት ቡድን በኢኮኖሚው ረገድ የዓለም ገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ ፖሊሲዎችን መሠረት አድርጎ ይንቀሳቀስ ስለነበር በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሚኪያሄደውን ከቻይናውያን የተገኘውን የልማት ተሞክሮ ያን ያህል ጠቃሚ ይሆናል ብሎ አልገመገተም ነበር።

ለሁለት ሳምንታት ቻይና በቆየሁበት ወቅት ትግራይ ውስጥ አንድ አስገራሚ ነገር ተከሰቶ ነበር። ይኸውም በትግራይ ጠለላ አግኝተው የነበሩ የሻዕብያ መንግሥት ተቃዋሚ ድርጅቶች አባላት ታስረው ለሻዕብያ እንዲሰጡ ከአዲስ አበባ ትእዛዝ መተላለፉ ነው። ቀደም ሲል ሻዕብያዎች ኢትዮጵያን መናኸሪያቸው አድርገው የሻዕብያን መንግሥት ተቃዋሚዎች ሁሉ አስረን እንድናስረክባቸው ጠይቀውን ስለተቃወምናቸው ጉዳዩን ዳግም ሳያነሡት ቆይተው ነበር። ሆኖም ስንቃወማቸው የነበርነው ወገኖች በሌለንበት ዳግም ጥያቄውን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅርበው ተቃዋሚዎቹ በእስር ተላልፈው እንዲሰጧቸው ተፈቅዶላቸው ነበር። እዚህ ውሳኔ ላይ የተደረሰው አዲስ አበባ በተኪያሄደ ስብሰባ ሲሆን በኤርትራ በኩል የሕዝባዊ ግንባር ለዴሞክራሲና ፍትሕ ጸሐፊ አልአሚን መሐመድ ሰዒድ፣ የመከላከያ ሚኒስትሩ ስብሓት ኤፍሬምና የደኅንነት ኃላፊው አብርሃ ካሳ፣ በኢትዮጵያ በኩል ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ፣ የመከላከያ ሚኒስትር ስዬ አብርሃ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሥዩም መስፍን፣ የደኅንነት ኃላፊው ክንፈ ገብረ መድኅንና በኤርትራ የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበረው አውዓሎም ወልዱ በተገኙበት ነበር። በስብሰባው የተደረሰበት ስምምነት ተቃዋሚዎቹን ከኢትዮጵያ አስወጥቶ ወደፈለጉበት አገር እንዲሄዱ ማድረግ የሚል ቢሆንም ወዲ በርሄ የተባለ በኢትዮጵያ የኤርትራ ኤምባሲ የጸጥታ ቡድን አባል መቀሌ ሄዶ ተቃዋሚዎቹን አስሮ ለመውሰድ እንደተፈቀደለት ለክልሉ ምክትል

አስተዳዳሪ ለአለቃ ጸጋይ በርሄና ለክልሉ ጸሐፊ ለአረጋሽ አዳነ ገልጸላቸው ሁኔታውን እንዲያመቻቹለት ይጠይቃቸዋል። አለቃ ጸጋይና አረጋሽ በነገሩ ተናደው ይህ ሊሆን እንደማይችል ይነግሩትና ፈቃዱን ማን እንደሰጠውም ይጠይቁታል። ወዲ በርሄም በወቅቱ የኢትዮጵያ የደኅንነት ኃላፊ የነበረውን ክንፈ ገብረ መድኅንን መጠየቅ እንደሚችሉ ይነግራቸዋል። እነ ጸጋይ ከሌሎች የመስተዳደሩ አባላት ጋራ ተነጋግረው ተቃዋሚዎቹን አስሮ ለሻዕብያ አሳልፎ መስጠት ትክክል እንዳልሆነ ይስማማሉ። ጸጋይም ለክንፈ ደውሎ ይህ ውሳኔ እንዴት እንደተወሰነና ተግባራዊ እንዲሆን እንደተፈቀደ ይጠይቀዋል። ክንፈ ወበኩሉ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ መቅረብ እንደሌለበትና የትግራይ ክልል ውሳኔውን ግስፈጸም እንዳለበት ለጸጋይ በጥብቅ ያሳስበዋል። ጸጋይም ውሳኔውን እንደማይቀበለውና ጉዳዩን ከመለስ ጋራ እንደሚነጋገርበት ነግሮት ከክንፈ ጋር የነበረው ውይይት ይዘጋል።

ጸጋይ የኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶች አባላትን አስሮ ለሻዕብያ አሳልፎ መስጠቱ ተገቢ እንዳልሆነና እርምጃው ሊያስከትለው የሚችለውን መዘዝ ለመለስ አስረድቶት ውሳኔው መፈጸም እንደሌለበት ያሳስበዋል። ተቃዋሚዎቹን አስሮ ለሻዕብያ አሳልፎ የመስጠቱን ውሳኔ ከመለስ ሌላ ሊያጸድቀው የሚችል ስላልነበረ መለስ ጸጋይን አዳምጦ ሊከተል የሚችለውን መዘዝ በመገንዘብ ሳይሆን አይቀርም ጸጋይን ብዙ ሳይጫነው ዝም ይላል። መለስ ሥራ አስፈጻሚው ውስጥ ጉዳዩን በሚገባ የሚያውቁትና የሚከታተሉት ተወልደ፣ ግለም ሰገድና ገብሩ በሌለንበት የራሱን ፍላጎት ሊያስፈጽሞ ኋላ ላይ ግፋ ቢል ተሳስቻለሁ ለግለት እንደነበር መግመት ይቻላል። ከዚህ ሌላም ወደ ውጭ የተጓዙት የኢሕአዴግ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎችና የትግራይ ክልል አስተዳዳሪ በሌሉበት ቀሪዎቹ የትግራይ መስተዳድር አባላት ምን ያህል ለእርሱ ውሳኔ ተገዥ ሊሆኑ እንደሚችሉ እየፈተሸ የነበረ ይመስላል። ቆይቶ ግን ከክልሉ መስተዳድር አባላት የተነሣውን ተቃውሞና ጉዳዩ በማዕከላዊ ኮሚቴ ወይም በሥራ አስፈጻሚ አባላት ሳይታይ በግሉና በቡድን በአጣዳፊ መወሰኑ ኋላ ላይ መነሣቱ እንደማይቀር የተገነዘበ ይመስላል።

ያም ሆነ ይህ ጸጋይና ሌሎች የመስተዳደሩ አባላት እነዚህን ኢትዮጵያ ውስጥ ጥገኝነት የጠየቁ ሻዕብያን የሚቃወሙ ድርጅቶች አሳልፎ መስጠቱን በርትተው ተቃውመዋል። የሦስቱን ድርጅቶች ማለትም የዴምሐኤ፣ የተሓኤ-ሳማም እና የተሓኤ-ሰባ አባላት አስሮ ለሻዕብያ መስጠት የተቃወሙትም አሳልፎ መስጠቱ ከሞራልም ይሁን ከፖለቲካ አንጻር ኢግባብ አይደለም ከሚል ነበር። እውነትም ተቃዋሚዎቹ ኢትዮጵያን መጠግያ አድርገው ሲኖሩ ከቆዩ ለሻዕብያ አሳልፎ መስጠቱ ያለ ምንም ጥርጣሬ ለሞት ወይም ለዕድሜ ልክ እስራት ይዳርጋቸው ነበር።

ጉዳዩ ከፖለቲካ አንጻርም የተሳሳተ ነበር። እነዚህ ፓርቲዎች የትጥቅ ትግሉ ከማብቃቱ በፊት በኤርትራ ዴሞክራሲያዊ አማራጭ ይሆናሉ በሚል ኢሕአዴግ ሲደግፋቸው የቆዩ ነበሩ። ከትጥቅ ትግሉ በኋላም ኤርትራ ውስጥ የነበረው ሥርዓት አምባገነናዊ ስለሆነ ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ቡደኖች ካሉ ሊደገፉ ይገባቸዋል ተብሎ ከኢሕአዴግ ድጋፍ ያገኙ ነበር። ሆኖም መለስ ይህን የኢሕአዴግ ውሳኔ ከልቡ የደገፈው አይመስልም። ለነገሩ የሻዕብያ መሪዎች መለስን ብቻ ሳይሆን ሁላችንም እነዚህን ቡድኖች እንድናባርር ነጋ ጠባ ይወተውቱን ነበር። መለስ ተቃወሚዎቹን የማስጠለሉን ውሳኔ ከልቡ እንዳልተቀበለው የሚያመለክተው ግን ከድርጅታዊ ውሳኔ ውጭ ከሻዕብያ ጋር ተነጋግሮ ተቃዋሚዎቹን ለማባረርና ለማስረከብ በመስማማቱ ነው:: ቀድሞውንም የእውነተኛ የውስጥ እምነቱ ይህ ቢሆንም ይህን ደፍሮ ለማዕከላዊ ወይም ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አቅርቦ ውሳኔ እንዲሰጥበት አላደረገም ነበር። የመረጠው መንገድ ሊቃወሙኝ ይችላሉ ያላቸው ሰዎች በሌሉበት ተቃዋሚዎቹን አሳልፎ መስጠትና ማስወገድ ነበር።

16. የኢትዮ - ኤርትራ የጋራ ኮሚሽንን መፍረስ ተከትሎ

ሻዕብያዎች ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር ያላደረጉት ሙከራ የለም። የመጀመሪያ ሙከራቸው ኢትዮጵያ ውስጥ እንደልብ እየተንቀሳቀሱ የአገሪቱን ሀብት መዝረፍና ተቀናቃኞቻቸውን ማጥፋት ነበር። ይህ አኪያሄድ እንደማያዋጣቸው ሲገነዘቡ ሕገ ወጥ አኪያሄዳቸውን ሕጋዊነት አልብሰው ለማስፈጸም ሞከሩ። ይህን ለማሳካትም ቀደም ሲል እንደገለጽኩት የኢትዮጵያና የኤርትራ የጋራ ኮሚሽን እንዲቋቋም ተደርጎ ስምምነቶች እንዲረቀቁና እንዲጸድቁ ተደረገ። ሆኖም ሻዕብያዎች ስምምነቶቹን ሽፋን በማድረግ ያለአግባብ ለመጠቀም ስለፈለጉ በወረቀት የሰፈረው ስምምነትም ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም። ከዚህ የተነሣም በሁለቱ አገሮች የኮሚሽን አባላት መካከል በየጊዜው ንትርክና አለመግባባት በርክቶ ሻዕብያዎች ኮሚሽኑ ፈርሶ በጋራ የፓርቲዎች ኮሚቴ እንዲተካ ጠየቁ። በዚህ መሠረትም ከህዝባዊ ግንባር ለዴሞክራሲና ፍትሕ /ህግዴፍ/ እና ከኢሕአዴግ የተውጣጡ አባላት የሚገኙበት የጋራ ኮሚቴ ተቋቋመ። ለዚህ ኮሚቴ በህግዴፍ በኩል፣ 1ኛ/ ዋና ጸሐፊው አልአሚን መሐመድ ሰዒድ፣ 2ኛ/ የፕሮፓጋንዳ ኃላፊው የማነ ገብረ ሚካኤል፣ 3ኛ/ የልማት ድርጅቱ ኃላፊ ሓጎስ ገብረ ሕይወት፣ 4ኛ/ በኢትዮጵያ የኤርትራ አምባሳድር ኃይለ መርቆርዮስ ሲወከሉ፣ በኢሕአዴግ በኩል ደግሞ፣ 1ኛ/ የኢሕአዴግ የፖለቲካ ጽ/ቤት ኃላፊው ተወልደ ወልደ ማሪያም፣ 2ኛ/ የትግራይ አስተዳዳሪ ገብሩ አሥራት፣ 3ኛ/ የትእምት ሥራ አስኪያጅ ስብሓት ነጋ፣ 4ኛ/ በኤርትራ የኢትዮጵያ አምባሳደር አውዓሎም ወልዱ ተወክለን ነበር። ይህ ኮሚቴ በኢትጵያና በኤርትራ መካከል ይከሰቱ የነበሩትን አለመግባባቶች እየተመለከተ ለመንግሥታቱ በማቅረብ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ታስቦ ቢቋቋምም በሂደት ከፍተኛ ተግዳሮቶች አጋጥመውት ብዙም ፈቅ ሳይል ቀረ። የጋራ ኮሚቴው ከየት ተነሥቶ የት እንደደረሰ ከዚህ በኋላ አመለክታለሁ።

16.1 የኮሚቴው የመጀመሪያ ግንኙነት /ግንቦት 19 ቀን 1987 ዓ.ም./

በሁለቱ ድርጅቶች ለኮሚቴው የተወከሉት አባላት ከተሰየመ በኋላ የመጀመሪያው ግንኙነቱ አሥመራ እንዲያኪሄድ፣ ከዚህ በኋላም ኮሚቴው በየሦስት ወሩ በኢትዮጵያና በኤርትራ በፈረቃ እየተገናኘ ሥራውን እንዲያከናውን ተስማማን።[29] በዚህ በመጀመሪያ ግንኙነታችን በሁለቱ አገሮችና ፓርቲዎች ያለውን ሁኔታ በተመለከተ መረጃዎችን ከተለዋወጥን በኋላ በቀጣይነት በምናተኩርባቸው ጉዳዩች ዙሪያም ተነጋግረን ነበር። በኢሕአዴግ በኩል ፓርቲው እያከናወናቸው ስለነበሩት ድርጅታዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም በፓርቲው ስለሚከናወኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በተለይ ደግሞ ፓርቲ፣ መንግሥትና የፓርቲ የንግድ ድርጅቶች ተለይተው ስለሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎችና በወቅቱ እያጋጠሙ ስለነበሩት ችግሮች ገለጻ ቀርቦ ነበር። በህግዴፍ በኩልም በተመሳሳይ በኤርትራ እየተደረጉ ያሉት እንቅስቃሴዎች ተገልጸው መንግሥትና ፓርቲ ተለያይተው እንደማይሠሩና በዚህ ረገድ ከኢሕአዴግ የተገኘው ተሞክሮ ጠቃሚ እንደሆነ ገልጸውልን ነበር።

ስለ ፓርቲዎች አጠቃላይ እንቅስቃሴ ውይይት ከተደረገ በኋላ የሁለቱን የፓርቲ ኩባንያዎች እንቅስቃሴ አስተባብሮና አቀናጅቶ መሥራት እንዲሚያስፈልግና አንዳንድ ሥራዎች በተናጠል ከሚሠሩ በጋራ ቢሠሩ ይበልጥ ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሻዕብያዎች ገለጹ። ለምሳሌ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በማዳበር ረገድ የጋራ ሥራ ሊሠራ እንደሚቻልና በተለይ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ የሚያገለግሉ ሶፍትዌሮች በጋራ ማምረት እንደሚቻል ሐሳብ አቀረቡ። በሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎችም የድርጅት ኩባንያዎቹ በጋራ ሊሠሩ እንደሚችሉ ገለጹ። የቀረቡት ሐሳቦች የኢሕአዴግ ተወካዮች ለነበርነው አዲስና

[29] የህግዴፍና የኢሕአዴግ የፓርቲ ተወካዮች የመጀመሪያው የጋራ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ ግንቦት 19 ቀን 1987 ዓ.ም.

ያልጠበቅናቸው ስለነበሩ ጥናታዊ መነሻ ይዘጋጅና ከዚያ በኋላ ሐሳቦችን በጋራ እናያቸዋለን ብሎ ወሰነ።

ከንግድና ኢንቬስትመንት ውጭም በሌሎች የጋራ ጉዳዩች ላይ አንድ ላይ መሥራት እንደምንችል በሻዕብያዎች ሐሳብ ቀርቦ ነበር። ተሞክሮዎችን መለዋወጥንና የሁለቱን አገሮች የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ደረጃ በደረጃ ማስማማትን *(policy harmonization)* በተመለከተ በጋራ እንሥራ የሚል ጥቅል ሐሳብም ሰንዝረው ነበር። እነዚህ ጉዳዮች ጊዜና ጥናት ስለሚፈልጉ በጽሑፍ ሰፍረው ይቅረቡ በሚል ታለፉ። በዚህ ሂደት በግንኙነቱ ዙሪያ በየበኩላችን መፍትሔ ይሻሉ ያልናቸው ችግሮች ካሉም እንድናቀርባቸው ተስማማን። በነገራችን ላይ ቀደም ሲል በጋራ ኮሚሽኑ ተነሥተው መፍትሔ ያላገኙ ጉዳዮች እንደነበሩና በየጊዜው የሚነሡ በርካታ አወዛጋቢ ጉዳዮች እንዳሉ ይታወቅ ነበር። ኮሚቴው ከፍተኛ የጋራ ራዕይ ኖሮት የጋራ ስምምነት ላይ ከመድረሱ በፊት መፈታት ያለባቸው ችግሮች እንዳሉ ሁለቱ ወገኖች ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። በመሆኑም መጪው የግንኙነት ጊዜ ቀላል እንደማይሆን ተገምቶ ለቀጣዩ ግንኙነት ዝግጅት እንድናደርግ ተስማምተን ተለያየን።

16.2 በድንበር አካባቢ የተፈጠረው ውጥረት

ኮሚቴው ተመሥርቶ እየተነጋገረ ባለበት ጊዜ ቢኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክልል በሆነው በትግራይና በኤርትራ ድንበር አካባቢ በሚገኙ ቀበሌዎችና ጎጠኞች ነዋሪዎች መካከል በየቀኑ የሚነሡ ግጭቶች ነበሩ። ከትጥቅ ትግሉ ጊዜ ጀምሮ ይከሰት የነበረው የከብቶች ዘረፋ በምዕራባዊ ትግራይ ዳግም አገርሽቶ የውጥረቱ አንዱ ምክንያት ሆኖ ነበር። በትጥቅ ትግሉ ጊዜ የምዕራባዊው ቆላ ኤርትራ ወይም የባርካ ተወላጆች የሆኑት ከብት አርቢዎች ከብቶቻቸውን እየነዱ ለም በሆነው የወልቃይት ቆላማ አካባቢ ግጦሽ መሬት ይጠቀሙ ነበር። ይህ ድርጊታቸው ከወልቃይት ከብት አርቢዎች ጋራ ያጋጫቸው ነበር። ውሱን የሆነው የግጦሽ መሬት፣ ለከብት መኖ የሚውሉ ዛፎችና ውሃ የግጭት ምንጭ ነበሩ። ወሺዎች የሚቆጠሩ የባርካ ከብት አርቢዎች፣ ላሞችና በሬዎች ወደዚህ አካባቢ ሲመጡ ለመከልከል ቢሞክርም አልተቻለም። ከደርግ ውድቀት በኋላ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተፈጠረው ድንበር ለነዚህ ከብት አርቢዎች ትርጉም አልነበረውም። ለዘመናት የሕይወታቸው መሠረት የነበረውን የግጦሽ መሬትና ውሃ በመፈለግ በቅርበት ካለው የትግራይ ምዕራባዊ ቆላም አልፈው እስከ ጎንደር፣ ጎጃምና ወለጋ ቆላማ ቦታዎች ይጓዙ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ በየአካባቢው በቋሚነት የሚኖሩ ወገኖች ይህን የግጦሽ አካባቢ በጥንቃቄ ይጠብቁትና ይጠቀሙበት ስለነበር አካባቢው በግጭት የታወቀ ሆኖ ቆይቷል።

በአካባቢው የሚነሣውን ግጭት ተከትሎ የከብቶች ዝርፊያ *(cattle rustling)* በየጊዜው ይከሰት ነበር። በትጥቅ ትግሉ ጊዜም ቢሆን የኤርትራ ከብት ዘራፊዎች የወልቃይትን ከብቶች ዘርፈው ሲሸሹ የወልቃይት ነዋሪዎችም እንዲሁ ዐፋውን ይመልሱ ነበር። ከዚህ የተነሣም በህወሓትና በሻዕብያ መካከል አለመግባባት እየተፈጠረ ዐልፎ ዐልፎ አንዱ አካባቢ ሌላውን እየካሰ መፍትሔ ይገኝ ነበር። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ነጻነቷን ካወጀች በኋላም ተመሳሳይ ችግሮች ሲከሰቱ በውይይት ለመፍታት ቢሞክርም ሊሳካ አልቻለም። የራሱን ድንበር ዘግቶና ጫካዎችን ከልሎ የኢትዮጵያን ተፈጥሮ ሀብት ለመጠቀም መከጀሉ ተቀባይነት አልነበረውም። በዚያን ጊዜ የትግራይ አስተዳደር ይህን የወልቃይት አካባቢ የተፈጥሮ ሀብት በሁለት መንገድ ጥቅም ላይ ለማዋል ወስኖ ነበር። መዘጋ ተብሎ የሚታወቀውን ሰፊ የወልቃይት ቆላማ ክፍል የዱር እንስሳት መጠለያ እንዲሆን በፓርክነት ከተከለለ በኋላ ቀሪውን መሬት የወልቃይት ከብት አርቢዎች እንዲጠቀሙበት ዐቅዶ ነበር። በወልቃይት ቆላማ ስፍራ ዝኆኖች፣ አንበሶች፣ ሰስ፣ ሚዳቋ፣ አጋዝን፣ ወዘተ... በብዛት ይገኙ

ነበር። በአንድ ወቅት በተደረገው ቆጠራ በአካባቢው ከአንድ መቶ ኀምሳ በላይ ዝኆኖች እንደነበሩ ተረጋግጧል። በአካባቢው የነበረው ጫካም ለከብቶች ግጦሽ ብቻ ከዋለ የአገር ሀብት የዱር አራዊት ይጠፋሉ፤ ጫካም ይወድማል፤ የሚል ሥጋት ስለነበርም በወቅቱ አካባቢውን መከለሉ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ተደርጎ ተወስዶ ነበር።

ሻዕብያዎች ይህን የወልቃይትን ጫካ መከለል በበጎ አልተመለከቱትም ነበር። እንዲያውም የኤርትራን ከብት አርቢዎች ለማገድና ከብቶቻቸው በረሐብ እንዲያልቁ ለማድረግ ሆን ተብሎ የተሸረበ ሤራ አድርገው ዐይተውት ነበር። በእርግጥ ይህ አካባቢ ሲከለል ከከብቶች ንክኪ ነጻ ማድረጉ የግድ የሚል ነበር። በዚህ መመሪያ መሠረትም የኤርትራም ይሁኑ የኢትዮጵያ ከብት አርቢዎች አካባቢውን እንዳይጠቀሙ፣ ይህን መመሪያ ከተላለፉም ቅጣት እንደሚበየንባቸው ተደንግጎ ነበር። መመሪያው በጥብቅ ይተገበር ስለነበርም የኤርትራ ከብት አርቢዎች እንደዱሮው ሰተት ብለው ገብተው አካባቢውን ለመጠቀም አይችሉም ነበር። ይህ ሁኔታ ያስቆጣቸው የኤርትራ መሪዎችም የክልሉ ውሳኔ ዳግም እንዲታይ ቢጠ ይቁም ውሳኔው እንደጸና ቀጠለ። ዐልፎ ዐልፎም ከብቶቻቸውን እተከለከለው ቦታ በማስጋጥ ቅጣት የሚጣልባቸው ኤርትራውያን ከብት አርቢዎች አልጠፉም። ወትሮም እንደተለመደው ግን መመሪያው ከወጣ በኋላም የወልቃይት ከብት አርቢዎች የኤርትራን ከብት አርቢዎች ከብቶች መዝረፋቸው አልቀረም። ሻዕብያዎች በየጊዜው ሲነሣ የነበረውን በኤርትራውያን የተዘረፉትን የኢትዮጵያውያንን ከብቶች የመመለስ ጉዳይ ወደጎን ትተው በኢትዮጵያውያን የተዘረፉባቸውን ከብቶች በማንሣት ካሳ እንዲከፈላቸው ይጠይቁ ነበር። የትግራይ መስተዳደርም በኤርትራውያን የተዘረፉት ከብቶች ሳይመለሱና ካሳ ሳይሰጥ ለአንድ ወገን ብቻ የሚሰጥ ካሳ የለም የሚል አቋም ነበረው። ይህ ለጠቡ አንዱ መነሻ ሆኖ ነበር።

ከምዕራብ ትግራይ ሌላ ድንበር አካባቢ ግጭት የነበረው በዓዲ ኢሮብና በዛላንበሳ አካባቢ ነበር። ከዓይጋ ወረድ ብሎ በስተ ምዕራብ በኩል በኤርትራ ድንበር አካባቢ የሚገኘው ዘገልባ ለዘመናት የኢትዮጵያ ግዛትና ኽኢትዮጵያ አስተዳደር ሥር መቆየቱ ይታወቃል። ሻዕብያዎች በኤርትራ መንግሥት ካቋቋሙ በኋላ ግን ይህ አካባቢ የኤርትራ እንጂ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛት እንዳልሆነ እየገለጹ እንዲያውም ከዚህ ዐልፈው በኢሮብ አካባቢ ዓይጋን፣ ወርዓትለን፣ ዓሊቴናንና ሌሎችን አካባቢዎችን ወደ ኤርትራ የሚያካልለው የሙና ወንዝ እንደሆነ ይገልጹ ነበር። ይህ የሻዕብያዎች ምኞት በትግራይ መስተዳደር በኩል ምንም ተቀባይነት ባይኖረውም ሻዕብያዎች የተጠቀሰው አካባቢ የእነርሱ መሆኑን ለማረጋገጥ በትግራይ መስተዳድር ሥር ከነበረው ዘገልባ ድረስ ዘልቀው ዛፎችን መቁረጥና ሰዎችን ማስፈራራት ጀምረው ነበር። ከዚህ ዐልፈውም በአካባቢው የአንድ ኢትዮጵያዊ ሚሊሺያ ሕይወት እንዲያልፍ ምክንያት በመሆናቸው የትግራይ መስተዳደር አካባቢውን በልዩ ትኩረት ይከታተለው ነበር።

ሻዕብያዎች የዛላንበሳ ከተማም እንዲሁ ከፊሉ የኤርትራ ነው በማለት በአካባቢው ሰፊ እንቅስቃሴ ያኪያሂዱ ነበር። ጥበቃዎቻቸውን ለግጭት በሚጋብዝ መልኩ ከተማው ዳር አስፍረው በየቀኑ መጠነኛ ግጭቶች ይከሰቱ ነበር። ከዓዲግራት ወደ ዛላንበሳ የሚወስደው አውራ መንገድ ውሱን ክፍልም የኤርትራ ነው ከማለታቸው በላይ ከዓዲግራት ወደ ዛላንበሳ የሚዘረጋው የኤሌክትሪክ መሥመር ዋናውን መንገድ ተከትሎ እንዳይሄድ ማስጠንቀቅያ ሰጥተው ነበር። ይኸን የሻዕብያዎች ትንኮሳ የተገነዘበው የትግራይ መስተዳደርም ከዓዲግራት ወደ ዛላንበሳ የሚያመራው መንገድ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛት መሆኑ ምንም ባያጠያይቅም ውዝግቡን ለማብረድ የኤሌክትሪክ መሥመሩ መንገዱን ወደ ግራ ትቶ እስከ ዛላንበሳ እንዲዘረጋ አድርጓል። ኢሳያስ ኋላ ላይ ወደ ትግራይ መጥቶ በዚህ ጉዳይ ላይ ስንነጋገርር ጉዳዩ እጅግ እንዳናደደውና እንዳሳዘነው ገልጾ ድርጊቱ የሻዕብያ የበታች ካድሬዎች እንጂ

ከፍተኛው አመራር ምንም እንደማያውቀው ቢገልጽልኝም ካለእርሱ ዕውቀት ምንም ዓይነት ድርጊት ደፍሮ የሚፈጽም የበታች ካድሬ እንደሌለ የታወቀ ነው።

ሌላው አወዛጋቢ የድንበር አካባቢ በዳሎል ወረዳ በራጋይለ ወንዝ ዳር የምትገኘው ዓዲ ሙሩግ የምትባለው ትንሽ የኢትዮጵያ መንደር ስትሆን ጣልያኖች በዚያ አካባቢ የድንበር ሰን ምልክት ተክለውበታል። የተተከለው ችካል መሰል ምልክት ይህችን መንደር ወደ ኢትዮጵያ ቢያካልልም ሻዕብያዎች ድንበር ዳር ያለችው ዓዲ ምሩግንም የዳሎልን ወረዳ ወአጠቃላይም የኤርትራ እንደሆኑ አውጀው ነበር። ዳሎል የኤርትራ ሉዓላዊ ግዛት እንደሆነችም በጂኦግራፊ መማርያ መጻሕፍታቸው ሁሉ አረጋግጠው ዳሎል ያለው ፖታሽ፣ ጂኦ ተርማል ኤነርጂና ሌላ የተፈጥሮ ሀብት ለእድገታቸው መሠረት እንደሚሆን ያስተምሩ ነበር። ይህን ለማለት ያበቃቸውም የትጥቅ ትግሉ ዘመን የህወሓት ሠራዊት በመሻል አገር ወውግያ ተጠምዶ ሳለ አካባቢውን በኃይል መቆጣጠራቸው ነበር። ዓዲ ምሩግ ቀደም ሲል እንደነ ፊታውራሪ ሑሴን ዋሚሳ ያሉ ኢዮጵያውያን ያስተዳድሩት የነበረ ከመሆኑም ወተጨማሪ ህወሓትም ለአጭር ጊዜ እንደ ቤዝ ዐምባ ተጠቅሞበት ነበር። አሁን ባለኝ ግንዛቤ የኢትዮጵያ ድንበር ከዓዲ ምሩግ እንደሚያልፍ ብገምትም ሻዕብያዎች ይህን አካባቢ ወኃይል ተቆጣጥረው ለግጭት መነሻ እንዳደረጉት ግልጽ ነው።

ሻዕብያዎች ከሑመራ አንስተው እስከ ቡሬ ድረስ ያድንበርና የግጦሽ ጥያቄ በማንሣት መለስተኛ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን ሲፈጠሩ፣ በእኛ በኩል ጉዳዩን ከሚመለከታቸው የአካባቢ መስተዳድሮች ጋራ በመነጋገር ለመፍታት ጥረት እያደረግን፣ ያነሷቸው የነበሩትን ውዝግቦች በየአካባቢው በነበሩ አስተዳዳሪዎች አማካይነት ለመፍታት እንሞክር ነበር። ሆኖም ሻዕብያዎች፣ መጠነኛ ግጭት ወይም አለመግባባት ሲፈጠር ጉዳዩን በማጋነን ከፍተኛ ወደል እንደደረሰባቸው አስመስለው ስሞታቸውን ወደ ከፍተኛ የአመራር አካላት ያደርሱ ነበር። እነዚህ ችግሮች ይከሰቱ የነበረው በኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛት ቢሆንም ትክክለኛው ድንበር በይፋ ባለመለየቱ ስለጉዳዩ ከሻዕብያጋ መነጋገሩን አላቋረጥንም ነበር። ሆኖም ሻዕብያዎች ድንበርን ሰበብ አድርገው ይተናኮሱ የነበረው በኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ ወመፍጠር ፍላጎታቸውን ለማሳካት ከነደፉት አጠቃላይ ስትራቴጂያቸው ተነሥተው ነበር።

16.3 የኮሚቴ ስብሰባዎችና ቀጣይ አለመግባባት

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የመጀመሪያው የኢሕአዴገና የህግዴፍ ኮሚቴ ስብሰባ አሥመራ ላይ ከተኪያሄደ በኋላ ቀጣዮቹ ስብሰባዎች በአዲስ አበባና በአሥመራ እየተፈራረቁ ይኪያሄዱ ነበር። በተደረጉት ስብሰባዎች በተለምዶ መጀመሪያ የመረጃ ልውውጥ ተደርጎ ቀጥሎ ደግሞ ሁለቱ አገሮች ስለሚኖራቸው ግንኙነት ውይይት ይኪያሄድ ነበር። ሆኖም እነዚህ ስብሰባዎች ውጤታማ ካለመሆናቸውም ባሻገረ አለመግባባትና ጭቅጭቅ እየበረታ ሄደ። ለዚህም ዋናው ምክንያት መሬት ላይ ያለው የሁለቱ መንግሥታት ግንኙነት በመርሕ ላይ ያልተመሠረተና ግልጽነት የጎደለው መሆኑ ነበር።

ሻዕብያዎች በተደጋጋሚ የግንኙነታችን መሠረት ምንድን ነው? ግንኙነታችንስ ስትራቴጂያዊ ነው ወይስ ስልታዊ? የሚሉ ጥያቄዎች ያነሡ ነበር። ቀደም ሲል እንደገለጽኩት ህወሓት/ኢሕአዴግ ሲያራምደው የነበረው አቋም ሻዕብያ በባሕሪይው ዴሞክራሲያዊ ባለመሆኑ፣ በኢምፔሪያሊዝም ላይ የነጠረ አቋም ባለመያዙና የሚከተለው መሥመር የከበርቴው በመሆኑ ከሻዕብያጋ ያለው ግንኙነት ስትራቴጂያዊ እንዳልሆነ ነበር። እውነቱን ለመናገር ግን ግንኙነታችን ሞቅ ሲል ልክ እንደ አንድ ድርጅት በጋራ የምንሠራበት፣ ግንኙነቱ ሲቀዘቅዝ ደግሞ በሳይነ ቁራኛ የምንተያይበት ሁኔታ ነበር እንጂ

ግንኙነታችን ስትራቴጂያዊ አይደለም የሚለው አቋማችን ግንኙነታችን ላይ ስለሚኖረው ተጽዕኖ በግልጽ ተዘርዝሮ አልተቀመጠም ነበር።

በደርግ ውድቀት ማግስት በህወሓት/ኢሕአዴግ በኩል የርዕዮተ ዓለምና የፖለቲካ አቅጣጫ ለውጥ እንደተደረገ ቀደም ሲል ገልጨዋለሁ። ሶቭዬት ኅብረትንና አሜሪካን በኢምፔሪያሊስትነትና በጠላትነት የሚፈርጀው አቋማችን ተለውጦ አሜሪካን በወዳጅነት የምናይበትና ኢምፔሪያሊዝም የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ ያደበዘዘበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። ከዚህ ሌላም ነገሮችን ከመደብ አንጻር በመመልከት ወደፊት የሚመሠረተው መንግሥት የላብ አደሩንና የአርሶ አደሩን አምባገነንነት ያረጋግጣል ማለታችን ቀርቶ የካፒታሊስትን ሥርዓት ለመገንባት እንደ ቆምን በሕገ መንግሥቱና በሌሎች ዓለም ዐቀፍ ስምምነቶች ገልጸን ነበር። በዚህም መልክ እንከተለው የነበረውን የጭቁን መደብ ተኮር ዴሞክራሲ ቢያንስ ከሕገ መንግሥቱ አኳያ በከበርቴው መደብ ዴሞክራሲ ተክተነው ነበር። ይህን ሁሉ ለውጥ ካደረግን በኋላ የቀረ ነገር ቢኖር አቅጣጫችንን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ብለን መሰየማችን ብቻ ነበር። ስለዚህ ከሻዕብያጋ አሉን ያልናቸው የፖለቲካው ልዩነቶችም የይዘት ሳይሆኑ የስም ብቻ እንደነበሩ እነዚህ ያደረግናቸው የፖለቲካዊ ለውጦች ያሳያሉ። ሻዕብያም ቢሆን የሚያራምደው ፖለቲካ የከበርቴው መሆኑን፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም የሚለው ፅንሰ ሐሳብ ጊዜ ያለፈበት መሆኑንና የጭቁን መደብ ሥርዓት ብሎ ነገር እንደሌለ ያምን ነበር። ሻዕብያ በትጥቅ ትግሉ ወቅት ለዲፕሎማሲ ብሎ በይፋ ያላወጀው ሶሻሊስት ፓርቲ እንደነበረው ቢገልጽም በተግባር የሚራበት የነበረው ርዕዮተ ዓለም ግን የከበርቴው ነበር። ህወሓት/ኢሕአዴግም ማሌሊትንና ኢላአድን የመሳሰሉ ማርክሲስት ፓርቲዎቹን በማፍረስ ራሱን ከላብ አደሩ ርዕዮተ ዓለም አግልሎ ነበር። በመሆኑም ሁለቱ ድርጅቶች በተጨባጭ ከቃላት ያለፈ የርዕዮተ ዓለምም የስትራቴጂም ልዩነት አልነበራቸውም ሊባል ይቻላል።

ሻዕብያዎች ከኢሕአዴግጋ የተወሰኑ የፖለቲካ ልዩነቶች እንዳሏቸው፣ ከስትራቴጂ አንጻር ግን ምንም ዓይነት ልዩነት እንደሌላቸው ይገልጹልን ነበር። ልዩነቶች የሚሏቸውንም በሥጋት ደረጃ ብቻ የሚያነሷቸውን ኢሕአዴግ የሚያራምደውን የብሔር ብሔረሰብ መብት እስከ መገንጠል አቋምና ይህን መሠረት ያደረገውን የፌዴራል የመንግሥት አወቃቀር ነበር። ይህ በኢትዮጵያ የተቋቋመው ፌዴራል ሥርዓት ለግጭትና ለኢ-ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ሊዳርግ ይችላል የሚል ሥጋት እንደነበራቸው በግልጽ ይነግሩን ነበር። ከዚህ ውጭ ሌላ ፖለቲካዊ ልዩነት እንደሌላቸውና ከኛ ጋራ የሚኖራቸው ግንኙነትም ስትራቴጂያዊ ሊሆን እንደሚችል ይገልጹልን ነበር። ሻዕብያዎች በኛ በኩል ያለውን አቋም ለማወቅ በምንገናኝበት አጋጣሚ ሁሉ በተደጋጋሚ ግንኙነታችን ምን ዓይነት ነው? ብለው ሲጠይቁን አብዛኛውን ጊዜ ቁርጥ አድርገን ግንኙነታችን ስትራቴጂያዊ አይደለም ብንላቸው ሊያስከትል የሚችለውን የግንኙነት መሻከር በመገመት መልስ አንሰጣቸውም ነበር። ሆኖም እንከተለው ከነበረው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮተ ዓለም በመነሣት ግንኙነታችን ስትራቴጂያዊ ሊሆን እንደማይችል ብዙዎቻችን በተለይም የኮሚቴው አባላት እናምን ነበር። ኢሕአዴግ ከሚከተለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮተ ዓለም በመነሣትም ሻዕብያን እንደ ተራ ከበርቴ ነው እንል ነበር።

በአንድ ወቅት ሻዕብያዎች የኢሕአዴግ ልኡካን ድብቅ አቋም ሊኖራቸው ይችላል ብለው ጠርጥረው የግንኙነታችን መሠረት ምን እንደሆነ በስምምነት ደረጃ አስፍረን ብንሠራ ይሻላል የሚል ሐሳብ አቅርበው ነበር:: እኛም በዚህ ተስማምተን የስምምነቱን ረቂቅ እንድናዘጋጅ በሻዕብያ በኩል የማነ ገብረ ሚካኤል፣ በኢሕአዴግ በኩል ደግሞ ገብሩ አሥራት ተመደብን። ይህን ሥራ ዳር ለማድረስ ሁለታችን በአዲስ አበባ ሒልተን ሆቴል ተገናኝተን ተወያይተን የረቂቁን ንድፍ *(outline)* የማነ እንዲያዘጋጀውና ንድፉን ካዘጋጀ በኋላ ገብሩ እንዲጽፈው ተስማማን።

በዚህ መሠረት የማነ ገብረ ሚካኤል የስምምነቱን ንድፍ አዘጋጅቶ ላከልኝ። ሆኖም የማነ የጻፈውን ንድፍ ስመለከተው የሻዕብያዎችን ፍላጎት ብቻ ያካተተ ሆኖ ስላገኘሁት የሁለታችንን ፍላጎት ሊያስማማ በሚችል መልኩ አስተካክልኩት። የማነ ካቀረባቸው የረቂቅ ሐሳቦች የለወጥኳቸው፤ 1ኛ/ የሻዕብያና የኢሕአዴግ ግንኙነት ስትራቴጂያዊ ነው የሚለውንና፣ 2ኛ/ ህግዴፍና ኢሕአዴግን ምሰሶ ወይም ማዕከል ያደረገ የአፍሪካ ቀንድ አገሮች ትብብር መኖር አለበት የሚሉትን ነበር። እነዚህን ሁለት የስምምነት ነጥቦች ውርዴ፣ 1ኛ/ ሁለቱ መንግሥታት በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት መፍጠር አለባቸው እና 2ኛ/ ግልጽነትና የጋራ ጥቅምን ያማከለ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ በሚል ከቀየርኳቸው[30] በኋላ ረቂቁን ጻፍኩኝ። ያዘጋጀሁትን ረቂቅም ለተወልደ ወልደ ማሪያም ወሳይቼ አስተያየታቸውን እንዲሰጡን ወደ አሥመራ ተላከ። ረቂቁ የደረሳቸው የሻዕብያ ልኡካን በጣም ተናደው ለተወልደ ወልደ ማርያም መልዕክት ላኩ። ተወልደ ረቂቁን አስቀድሞ ተመልክቶት እንደነበርና የተለየ ሐሳብ እንደሌለው ሻዕብያዎች አላወቁን ነበርና ገብሩ ያረቀቀው የስምምነት ሰነድ ከተነጋገርንበት መንፈስ ውጭ ነው፤ በሁለቱ አገሮች እንዲኖር የምንፈልገውን ግንኙነት ያገናዘበ አይደለም፤ የሚል አስተያየት ለተወልደ ሰጡ።[31] ተወልደም ጉዳዩን ተገናኝተን እንነጋገርበት በሏቸው ሰነዱ ለድርድር ቢቀርብም ሻዕብያዎች የማይፈልጉት ስለነበር ተረስቶ ቀረ። ሻዕብያዎች ከዚህ ሰነድ የፈለጉት ሌላ ነገር ፖሊሲዎቻችንን እናስማማ የሚል ነበር። ይህን ሐሳባቸውን በሰነዱ አካተው የኢትዮጵያን ሀብት ለመዝረፍ የነበራቸውን ጉጉት ተግባራዊ ለሚድረግ ፈልገው ነበር። ሆኖም ረቂቁ የስምምነት ሰነዱ በፈለጉት መንገድ ሳይቀረጽ በጣም አበሳጭቷቸው ነበር።

16.4 ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋራ ውይይት

ኢሳያስ በትግራይ አስተዳደር በአጠቃላይ፣ በተለይ ደግሞ በእኔና በትግራይ በነበሩት የአመራር አባላት ላይ ከፍተኛ ጥላቻ እንደነበረው ከፍ ብዬ ጠቅሼዋለሁ። ኢሳያስ ወደ ትግራይ የሚመጣው በአብዛኛው በመኪና ራሱ እየነዳ ሲሆን የመጣውም በተለይ ከሱዳኑ መሪ አልበሽርጋ ለመወያየትና የየካቲትን በዓል ለማክበር ነበር። ከመለስ ዜናዊምጋ ለመወያየት የመጣበትም የተወሰነ አጋጣሚ ነበር። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት፤ ሱዳን *«ድንበር ተሻጋሪ የአክራሪ እስልምና በማበረታታም ጎረቤቶቿ የሆኑትን ኢትዮጵያንና ኤርትራን ለማተራመስም ትጥር ነበር።»*[32] ከዚህ የተነሣ ሱዳኖች በኤርትራ ኢስላሚክ ጅሃድ በመባል የሚታወቁ አክራሪ ሙስሊሞችን ደግፈው ጦርነት እንዲከፍቱ አድርገዋል የሚል ቅሬታ በሻዕብያዎች ይሰነዘር ነበር። መለስም የሻከረውን የሁለቱን ግንኙነት ለመጠገን በሽርንና ኢሳያስን መቀሌ ድረስ አምጥቶ ለማስታረቅ ሞክሮ ነበር። በዚህ በአንድ አጋጣሚ መነጋገር ሲጀምሩ ኢሳያስ እሳት ለብሶ፣ እሳት ጎርሶ፣ በሽርን በዓረብኛ ሰድቦት ውይይቱን ጥሎ ወጣ። በሽር ክው ብሎ ሁለቱ መሪዎች ምንም ዓይነት ስምምነት ላይ ሳይደርሱ ወደየአገራቸው ተመለሱ።

በሌላ ጊዜ ደግሞ በሽርና ኢሳያስ የተገኙበት ስብሰባ መቀሌ ላይ ተኪያሂዶ ስብሰባው አልቆ ለምሳ ተቀመጥን በሽር፤ *«መቀሌ ከአሁን በፊት ካየኋት ተሻሽላለች፤ የሰው ወዝ ተለውጧል፤ የፈራረሱና ያረጁ ቤቶች ተጠግነዋል፤ የሕዝቡ መንፈስም የተሻለ እንደሆነ ከፊቱ ይነበባል፤ እና ለሠራኸው ሥራ ሁሉ ምስጋና ላቀርብልህ እወዳለሁ፤ ለመሆኑ በገጠርስ ምን እየሠራችሁ*

---

[30] ንሓባራዊ ረብሓ ዝምድናታትና ነደልድል፣ 1988 ዓ.ም.፣ መቐለ፣ 26 ገጽ ረቂቕ ሰነድ፣ /በአማርኛ ሲተረጎም *«ለጋራ ጥቅም ሰንል ግንኙነታችንን እናጠናክር፣ 1988 ዓ.ም.፣ መቀሌ፣ 26 ገጽ ረቂቅ ሰነድ»*

[31] የሻዕብያው የማነ ገብረ ሚኬኤል /የማነ ማንኪ/ ለተወልደ ወልደማሪያም እንደነገረው

[32] Tekeste Negash and Kjetil Tronvoll. 2000. *Brothers at War: Making Sense of the Eritrean-Ethiopian War.* James Currey Ltd, 73 Botley Road, Oxford, p.139.

ነው?» ብሎ ሲጠይቀኝ፤ «በገጠር አንዳንድ የግብርና ልማት እንቅስቃሴዎችን እያካሂደን ነው። ከእንቅስቃሴዎቻችን አንዱም በአስር ዓመታት ውስጥ ዐምስት መቶ አነስተኛና መካከለኛ ግድቦች በመሥራት ሰፊ የመስኖ ልማት ማካሂድ ነው» አልኩት። ይህን ዕቅድ በተለይ የገለጽኩለት ምክንያትም ሱዳኖች ስለ እኛ የውሃ ማቆር ሥራ ያላቸውን አስተያየት ለማወቅም ነበር። በሽር፤ «ዕቅዱ ጥሩ ነው፤ ከተሳካም እጅግ ጠቃሚ ይሆናል፤» የሚል አስተያየት ሲሰጥ ኢሳያስ በመኻል ገብቶ፤ «ገብሩ የምትለው ዕቅድ እጅግ አነስተኛ ነው፤ እኛ ኤርትራ ውስጥ እያንዳንዷን ሸለቆ በመገደብ አጠቃላይ ኤርትራ ውስጥ የሚነርፈውን ውሃ በሙሉ በአስር ዓመት ውስጥ ለማቆር ዕቅደናል። ይህን በተመለከተም አጥጋቢ ሥራ እየሠራን ነው» አለ። የኢሳያስ ጣልቃ ገብነት ቢያስገርመኝም ዕቅዱ እውነት ይሆን ብዬ፤ «ሥራው የሚሠራው በሰው ኃይል ነው በዘመናው መሣሪያ? የደለል ሙላትን ችግርስ እንዴት ለመቋቋም ዕቅዳችኋል?» ብዬ ጠየቅኩት። ኢሳያስም፤ «ሥራውን የምናከናውነው በማሺን ስለሆነ በርካታ ማሺኖች አስገብተናል። የደለል ችግርን መቋቋም ቀላል ነው፤ በግድቡ ላይ የተከማቸውን ደለል በመሣሪያ አማስሎ በቧንቧ ተሰቦ እንዲወጣ ማድረግ ይቻላል። የግድቡን ወለልም በፕላስቲክ ወይም በአስፋልት ለመሥራት ዕቅደናል» አለኝ። ይህ አባባሉ ቀልቤን ስለሳበው፤ «ይህን ነገር ማየት ይቻላል?» ብዬ ስጠይቀው፤ «አዎን ይቻላል፤ መጥቶ ልምድ መውሰድ ይቻላል፤» ብሎ መለሰልኝ።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፣ ሁኔታውን ለማየት አንድ የባለሙያዎችና እኔም የነበርኩበት የአመራር ቡድን ከትግራይ ወደ ኤርትራ ሄደ። ቡድኑ በመሠራት የነበሩትንና ተሠርተውም በጎርፍ የተወሰዱትን ግድቦች በጸሮና፣ በሠራዬና በምጽዋ መንገድ ጎበኘ። ሥራው እጅግ ዝቅተኛ በሆኑ የግንባታ መሣሪያዎችና በጥቂት ባለሙያዎች እንደሚሠራ፤ ትግራይ ውስጥ ይሠራ ከነበረው ሥራም ዝቅ እንደሚል ተገነዘብን። ጉብኝቱ ካበቃ በኋላ፣ የግድብ ሥራውን ይመሩ ከነበሩ የኤርትራ የግብርና ባለሙያዎች ጋራ አሥመራ ላይ ውይይት አኪያሂድን። በዚህ ውይይት ጠቃሚ ይሆናል ብለን ስለፈረሰው ግድብ ችግሮች በርካታ ጥያቄዎች አነሣን። ሆኖም ኤርትራውያኑ ባለሙያዎች እጅግ ተናደው፤ «የኛን ሥራ ለማንኪሰስ ፈልጋችሁ ነው እንጂ ስለፈረሰው ግድብ ከመጠየቅ ይልቅ ስለሌላው ሥራ ለምን አትጠይቁንም?» አሉን። እኛም ፍላጎታችን ልናንኳስሳቸው ሳይሆን የምንሠራው ሥራ እንዳይበላሽብን ከችግሮቻቸው ለመማር እንደሆነ ለማስረዳት ብንሞክርም በጥሩ መንፈስ ሳንለያይ ቀረን። ያም ሆነ ይህ ኢሳያስ መቀሌ ላይ የነገረኝ ውሸት እንደሆነ ተገነዘብኩኝ።

ኢሳያስ ወደ መቀሌ በመጣበት አጋጣሚ ሁሉ ያለውን ቅሬታ ሳያነሣ አይመለስም ነበር። በአንድ ወቅት ኢሳያስ ከመለስ ጋራ ለመገናኘት በሠራዬ በኩል ተጉዞ ዓድዋንና ተምቤንን በመኪና አቋርጦ ወደ መቀሌ ሲመጣ፤ አብሮት ለተጓዘው ለአውዓሎም ወልዱ፣ «ዛሬ መቀሌ ሄጀ ገብሩን እሰድበዋለሁ፤ አልምረውም» ሲል፤ አውዓሎም፣ «ከሰደብከው እኮ እሱም ይሰድብሃል፣ ዝም እሚል አይመስለኝም፤» ይለዋል። ኢሳያስ ጉዞውን ጨርሶ መቀሌ እንደደረሰ ከኔጋ ቀዝቃዛ ሰላምታ ተለዋውጦ የመጣበትን ሥራ ጨርሶ ከመመለሱ በፊት ከመለስ ዜናዊ ጋራ ተነጋግሮ ኖሮ መለስ፤ «ኢሳያስ ካንተጋ የምንወያይበት ጉዳይ አለ ስላለ እናግኘው» አለኝ። ከእርሱ ጋራ በግል የሚያገናኘኝ ምንም ነገር የለም ለማለት ካቅማማሁ በኋላ፣ እስቲ የሚለውን ልስማ ብዬ ላገኘው ተስማማሁ። ኢሳያስ በአጼ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ ወዳረፈበት በደርግ ዘመን የትግራይ አስተዳዳሪ የነበረው ሻለቃ ሙሉጌታ ሓጎስ ወዳሠራው ቪላም አመራሁ።

ኢሳያስ በጠየቀው መሠረት በውይይቱ በመቀሌ የኤርትራ ቆንስል ኃላፊ የነበረው ጄኔራል አብራሃለይ ክፍሌና መለስ ተገኝተው ነበር። ጥብቅ የመንግሥት አሠራር ብንከተል ኖሮ ኢሳያስ ስለእኔ የሚያነሣቸው ጉዳዮች የግል ሳይሆኑ የመንግሥትና የአገር ጉዳዮች ስለነበሩ

መለስ እንደአወያይ መቀመጥ ባልነበረበት። ያም ሆነ ይህ ኢሳያስ ጉዳዩን እንዲያቀርብ ሲጠየቅ፤ «እኔ ከማቀርበው ጉዳዩን በዝርዝር የሚያውቀው በመቀሌ የኤርትራ ቆንስል ኃላፊ ይናገር» አለ። አብረሃሌይም፤ «ትግራይ ውስጥ እኛን የሚያሳስቡና የኤርትራን ነጻነት የሚጋፉ በርካታ ችግሮች እየተፈጠሩ ነው። ሁለት ጎልተው የሚታዩ ችግሮችን ባቀርብ፣ በመጀመሪያ ትግራይ ውስጥ ኤርትራውያን የባንክ ሂሳብ ለመክፈት ጥያቄ ሲያቀርቡ የቀበሌ መታወቅያ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፤ ይህ አሊያሄድ ትክክል አይደለም። ኤርትራውያን የውጭ ዜጎች እንደመሆናቸው መጠየቅ ያለባቸው የኤርትራን መታወቅያ እንጂ የትግራይን የቀበሌ መታወቅያ መሆን የለበትም። በትግራይ የሚኖሩ ኤርትራውያን ዜጎች በኤርትራ መንግሥት የተሰጣቸው መታወቅያ ተቀባይነት ያለማግኘቱም የኤርትራ ዜግነታቸው ተቀባይነት አለማግኘቱን የሚያመለክት ነው» ብሎ ተናገረ። በመቀጠልም፤ «ሽራሮ ውስጥ በትጥቅ ትግሉ ወቅት ከኢዴን ጋራ ተባብራችኋል ተብለው ቤታቸውን የተወረሱ ኤርትራውያን ኤርትራ ነጻ ከወጣች በኋላ ቤታቸው እንዲመለስላቸው መስተዳደሩን ጠይቀው እንደማይመለስላቸው ተነግሯቸዋል። እዚህ ላይም ኤርትራዊ ዜግነታቸውና መብታቸው የተጣሰ መሆኑ ተረጋግጧል። የኢትዮጵያ መንግሥት ወይም ባለሥልጣን የኤርትራውያንን ንብረት መውረስ አይችልም። ይህን ካደረገ ደግሞ የኤርትራ ዜግነት መብታቸውን አልተቀበለም ማለት ነው» አለ።

እኔም ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ መስጠት ነቢረብኝና የሚከተለውን አልኩኝ፤ «በመጀመሪያ ለተነሣው ኤርትራውያን የኤርትራን መታወቅያ ተጠቅመው ኢትዮጵያ ውስጥ የባንክ ሂሳብ መክፈት አለባቸው ለሚለው ጥያቄ የኢትዮጵያ ሕግ ምን እንደሚል ብታውቁት ጥሩ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የባንክ ሂሳብ መክፈት የሚችለው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ብቻ ነው። ኤርትራውያንም በዜግነት ኢትዮጵያውያን ስላልሆኑ በኢትዮጵያ የባንክ ሂሳብ የመክፈት መብት የላቸውም። እንዲያውም ሕጉ በትክክል ሥራ ላይ ይዋል ከተባለ ኤርትራውያን የባንክ ሂሳብ የመክፈት መብት ፈጽሞ እንደሌላቸው እየታወቀ፣ ጉዳዩ ገና ግልጽ አልተብጀለትም በሚል በልዩ ሁኔታ የባንክ ሂሳብ እንዲከፍቱ ተደርጓል። በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የባንክ ሂሳብ መክፈት መከልከል ሲገባቸው ልዩ መብት ተሰጥቷቸው የቀበሌ መታወቅያ ካሳዩ የባንክ ሂሳብ ለመክፈት እንዲችሉ መፈቀዱ የኤርትራውያንን ነጻነትና መብት እንደ መጣስ ተደርጎ መወሰዱ እጅግ የተሳሳተና አግባብ የሌለው አመለካከት ነው፤» አልኩኝ። ለሁለተኛው ጥያቄ መልስ ከመስጠቴ በፊት ደግሞ እንድ ጥያቄ ላንሣ ብያቸው፤ «በትጥቅ ትግሉ ዘመን ሽራሮ ላይ የተወረሱት የኤርትራውያን ቤቶች አልተመለሱም ስትሉ፤ ያኔ የተወረሱ የኢትዮጵያውያን ቤቶች ስለመመለሳቸው የምታውቁት ነገር አለ ወይ?» ብዬ ጠየኳቸው። «ስለዚህ ጉዳይ የምናውቀው ነገር የለም። እኛ የምናውቀው የተወረሱ የኤርትራውያን ቤቶች አለመመለሳቸውንና መብታቸው እንደተነካ ብቻ ነው» ብለው ሲመልሱም፤ «እንግዲያስ ማወቅ ያለባችሁ አሁን ኤርትራውያን የምትሏቸው ዜጎች ቤቶቻቸው የተወረሱባቸው ኢትዮጵያውያን በነበሩበት ጊዜ እንጂ የኤርትራ ዜግነት በያዙበት ጊዜ አይደለም። ስለዚህ፣ የተወረሱት ቤቶች የኢትዮጵያውያን እንጂ የኤርትራውያን አይደሉም። አሁን ቤቶቹ ይመለሱ የሚል ውሳኔ ቢወሰን እንኳን ከኢትዮጵያዊነት ወደ ኤርትራዊነት ዜግነታቸውን ለለወጡት ብቻ በተናጠል የሚወሰንበት ምክንያት የለም። መመሪያው አንድ ወጥ ስለሆነ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያንን አይለይም። እዚህ ላይም እያነሣችሁት ያለው ጥያቄ ኤርትራውያኑ ልዩ መብት ይሰጣቸው የሚል ነው። ይህ ደግሞ ሊሆን አይችልም። ጥያቄያችሁ ትክክለኛ ባይሆንም፤ መጠየቅ የነበረባችሁ የተወረሱ የኢትዮጵያውያን ቤቶች ሲመለሱ የተወረሱ የኤርትራውያን ቤቶች አልተመለሱም ብላችሁ ነበር። ይህን ሳታጣሩ የኤርትራውያን ቤቶች አልተመለሱም ማለታችሁ ስሕተት ነው። በዚህ ረገድም ተጨማሪ ልዩ መብት ይሰጠን

ካላሳችሁ በስተቀር የኤርትራውያን መብት አልተረገጠም፤ ኤርትራውያን ላይም በደል አልተፈጸመም፤» አልኳቸው።

ሌላ የምታነሡት ጥያቄ ካለ ለማዳመጥ ዝግጁ ነኝ ስላቸውም፤ ጥያቄዎቻቸው በዚህ መልክ ይቋጫሉ ብለው ባይገምቱም ለጊዜው መከራከሪያ ስላልነበራቸው ጸጥ አሉ። ኢሳያስም በጣም ተናዶ፤ *«ጉዳዩ ይህ መሆኑን ባውቅ ኖሮ ውይይቱ ባላስፈለገ ነበር። አብርሃሌ፤ ከእንግዲህ ወዲህ የዚህ ዓይነቱን የማይረባና በካድሬ ደረጃ ማለቅ የሚችል ጉዳይ ይዘህ እንዳትመጣብኝ። እኔ ጉዳዩን ስለማላውቀው ትልቅ ፋይዳ ያለው መስሎኝ ነበር ወደዚህ ውይይት የገባሁት፤»* ብሎ ሲል፤ መለስም ይህንኑ በማስተጋባት፤ *«እነዚህን መሰል ችግሮች ከሥር ማለቅ አለባቸው እንጂ በእኛ ደረጃ ልንነጋገርባቸው አይገባም።»* አለ።

ጉዳያቸውን እንዲሁ እነዚህን ችግሮች በማጣቀስ ለማቅረብ ሞከሩ እንጂ ሻዕብያዎች በትግራይ መስተዳደርና በእኔ ላይ የነበራቸው አቋም ያለቀለት ነበር። መስተዳደሩና ገብሩ የኤርትራን ነጻነት አይቀበሉም፤ የኤርትራን ጥቅም ይጻረራሉ፤ ኤርትራውያንን ይበድላሉ፤ የሚሉ ወሬዎች በስፋት ተነዝተው እንደነበር ቀደም ብዬ ጠቅሼዋለሁ። የሻዕብያ መሪዎች ያቀረቧቸው ቅሬታዎች ዓላማ በትግራይ መስተዳድርና በእኔ ላይ ለሚያነሷቸው ክሶች በመለስ ፊት ማስረጃ አቅርበው መስተዳድሩ እንዲነሣላቸውና እነርሱ በሚፈልጉት መስተዳድር እንዲተካላቸው ለማድረግ ነበር። ውስጥ ውስጡን የሚንቀሳቀሱት ይህን ተግባራዊ ለማድረግ እንደነበርም መረጃ ነበረን[33]። ጉዳዩን መለስ ብዬ ሳየው የሚያስገርመው ከኢሳያስና ከአብርሃሌ ጋ ስንከራከር መለስ ዳኛ እንጂ ከኔ ጋራ ወግኖ የአቋሜን ትክክለኛነት ያለመደገፉና ለኤርትራውያን እየተሰጠ ስላለው ልዩ መብት አስተያየት ያለመስጠቱ ነው። ኢሳያስና አብርሃሌ ችግር ብለው ያነሡት ጉዳይ አገራዊ እንጂ ክልላዊ እንዳልሆነ እያወቁ በጉዳዩ ከመለስ ይልቅ ከትግራይ መስተዳደር ጋር ለመከራከር መምረጣቸውም አስገራሚ ነበር። ይህን ያደረጉት የተለየ ጥቅም ለማግኘት የነበራቸውን ፍላጎት ያደናቀፋቸው የትግራይ መስተዳደር እንጂ የፌዴራሉ መንግሥት እንዳልሆነ ተገንዝበው ይመስላል። ያም ሆኖ ይህ መቀሌ ላይ በተነሣው ጉዳይ ኢሳያስም ይሁን መለስ የትግራይን መስተዳድር ለመወንጀል የሚያስችላቸው ጠንካራ መከራከሪያ ባለማግኘታቸው ውይይቱ ለጊዜውም ቢሆን በኢሳያስ ሽንፈት ተቋጨ።

16.5 የሻዕብያ ቅሬታዎች፣ በሼህ አላሙዲና በታምራት ላይኔ ላይ

እንደ ጣልያንና እንደ ሌሎች ቅኝ ገዥዎች ሁሉ ሻዕብያዎች ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ራሷን ችላ እንድትበለጽግ ፍላጎት አልነበራቸውም። በመሆኑም ኤርትራና ኢትዮጵያ ተግባብተው በጋራ እንዲለሙ ከመመኘት ይልቅ *«ባልሽ ከባሌ ይበልጣል ሸሮ ለበድሪኝ»* እንዲሉ ኢትዮጵያ ለእነርሱ የጥሬ ዕቃና የርካሽ ጉልበት አቅራቢ ሆና ኤርትራ የኢንዱስትሪ ሸቀጦችን እያመረተች የበለጸገች አገር እንድትሆን ይመኙ ነበር። ይኸንን የምለው እንዲሁ ከባዶ ተነሥቼ እንዳልሆነ በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ አሳይቻለሁ። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት በ1983 ዓ.ም. ክረምት ላይ ሻዕብያዎች በጠሩት አገራዊ የልማት ኮንፈረንስ ላይ ኤርትራ የአካባቢው የኢኮኖሚ አውራ ሆና እንድትበለጽግ የሚፈልጉ መሆናቸውን በይፋ ሲያውጁ ከተወሰነ ጊዜ በኋላም የሲንጋፖርን አርአያነት እንደሚከተሉ አስታውቀው ነበር። የሲንጋፖር የእድገት ሂደት ለማጥናትና ልምድ ለመቅሰምም አንድ ከፍተኛ

[33] መቀሌ በነበረው የኤርትራ ቆንስላ የስለላ ኃላፊ ሆኖ ሲሠራ የነበረው ንዋቱ የተባለው ተወካያቸው ኤርትራ ውስጥ ለነበረው ወዲ ዓነዱ ለተባለው ነባር ታጋይ የጻፈውን ደብደቤ ጠልፈን ስናነበው፣ የትግራይን መስተዳድር ክቱኛ እንደሚጠሉ አረጋግጠናል። የተጻፈው ደብዳቤ የትግራይ መስተዳድር በኤርትራ ነጻነት እንደማያምንና ሕዝቡም በአመራሩ ተገዶ እንጂ ነጻነታቸውን እንደማይቀበለው ይገልጻል። ወደ ትግራይ መመደቡንም ገሃነም ከመኖርጋ ያመሳስለዋል።

የኤርትራ ልኡካነ ቡድን አሰማርተው ነበር። ምናልባት ይህን ዕቅዳቸውን በአስራ ዘጠነኛውና በኻያኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ቢቀርጹት ኖሮ ምኞታቸው የመሳካት ዕድል በኖረው ነበር። በኻያኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በኻያ አንደኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ግን እንደ ሲንጋፖር መሆን ለኤርትራ ብቻ የተከለለ አልነበረም።

ዘመኑ ቴክኖሎጂ፣ ዕውቀትና ካፒታል በቀላሉና በፍጥነት በዓለም የተሰራጨበት በመሆኑ ያልበለጸጉ አገሮች የዚህ ዓለማዊ እንቅስቃሴ ተጠቃሚ ለመሆን ያላቸው ዕድል ተመሳሳይ ሆኗል። እንዲያውም ከፍተኛ የሰው ኃይልና ዕምቅ የተፈጥሮ ሀብት ያላቸው አገሮች ይበልጥ የዕድሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ኢትዮጵያም ከኤርትራ በጣም በበለጠ መንገድ የዚህ ዕድል ተጠቃሚ ልትሆን እንደምትችል ግልጽ ነበር። ዓለማዊ ሁኔታዎች በእጅጉ እንደተለወጡ ያልተገነዘቡት ሻዕብያዎች የኢኮኖሚ ፖሊሲያቸው ለፍጥጫና ለግጭት እንደሚዳርጋቸውና ከጎረቤቶቻቸው ጋራ ባይተባበሩ ለብቻቸው ለመበልጸግ እንደማይችሉ አልተረዱም ነበር። የተዳከመች ኢትዮጵያን የብልጽግናቸው ምንጭ የሚያደርገው ፖሊሲያቸውም የኢትዮጵያ ተቀናቃኞችና ቅኝ ገዥዎች ለዘመናት ሲከተሉት የነበረው ፀረ-ኢትዮጵያ ፖሊሲ ተቀጥላ ነበር። ኤርትራውያን በረጅሙ የታሪክ ጉዟቸው ከኢትዮጵያ ጋራ ትስስር ፈጥረው በጋራ መበልጸግ ሲችሉ በኢሳያስ የሚመሩት ሻዕብያዎች የጣልያኖችንና የጎረቦችን በተለይ ደግሞ የግብጽን ፈለግ መከተላቸው የሚያዋጣቸው አልነበረም።

ሻዕብያዎች አላሙዲ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያደርገውን የኢንቬስትመንት እንቅስቃሴ ከፍ ብዬ የገለጽኩትን ስትራቴጂያቸው የሚያበላሽ መስሎ ይታያቸው ስለነበር በበጎ አያዩትም ነበር። አላሙዲ ከኤርትራ ይልቅ ኢትዮጵያን የኢንቬስትመንት ማዕከል ለማድረግ የመረጠው እንደሚለው የወላጅ እናቱን አገር ኢትዮጵያን የበለጠ ስለሚወድ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ መጠን ያለው መዋዕለ ንዋይ በኢትዮጵያ አፍሶ፣ በርካታ የመንግሥት የማምረቻና የንግድ ተቋማትን በርካሽ ገዝቶ፣ ወደፊት ሊያካብተው የሚችለው ትርፍም አስቀድሞ አስልቶ ነው። የዚህን መሰል ኢንቬስትመንትም በሌሎች የትውልድ አገሩ ባልሆኑ አገሮች ግለትም በስዊድን፣ በሊባኖስ፣ በሰሜን አፍሪካና በሰሜን አሜሪካ እንዳደረገና ከጊዜ በኋላ ከፍተኛ ትርፍ እንዳገኘ ይታወቃል።

ሻዕብያዎች አላሙዲን ወደ ኤርትራ እንዲገባ በየአጋጣሚው ይወተውቱት ነበር። ኢሳያስ አሥመራ ላይ ከአላሙዲ ጋራ ለሦስት ሰዓታት ያህል ተነጋግሮ በኤርትራም ኢትዮጵያ እንዳደረገው የኢንቬስትመንት እንቅስቃሴን እንዲያስፋፋ ጠይቆት ነበር። አላሙዲ የኤርትራ ገበያ ምን ያኽል ጠባብ እንደሆነ፣ የአገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ፖሊሲም ኢንቬስትመንት እንደማይጋብዝ አሳምሮ ያውቅ ስለነበር ለሻዕብያዎች ተስፋ ሊሰጣቸው አልቻለም። በወቅቱ የኤርትራ ሕዝብ ብዛት ሦስት ሚልዮን እንኳን ካለመሆኑም በተጨማሪ የመግዛት ዐቅሙም በጣም ዝቅተኛ ነበር። አላሙዲ በውይይቱ መጨረሻ አሁኑኑ በተጨባጭ የምትሸጡት ነገር ካላችሁ ልግዛችሁ ሲልም አሥመራ ውስጥ የተሻለ የሚባለውን ኒያላ ሆቴልን በዐምስት ሚልዮን ዶላር ሸጠውለት ገንዘቡን ሰጥቷቸው ሆቴሉን ሳይረከብ ቀርቷል።

አላሙዲ ኤርትራ ውስጥ መዋዕለ ንዋዩን ለማፍሰስ ፍቃደኛ ባለመሆኑ ሻዕብያዎች በኢትዮጵያ የሚያከያሂደውን የኢንቬስትመንት እንቅስቃሴ ለማደናቀፍ ሜራ ጠንሰሰው ስሙን በማጥፋት ከኢትዮጵያ ሊያስወጡት ሞክረዋል። አዲስ አበባ የነበራቸውን የስለላ መዋቅር በመጠቀምም ከእስላማዊ ሥነ-ምግባር ውጭ ናቸው የሚሏቸውን የአላሙዲን ተግባራት ለምሳሌ በሠርግና በጭፈራ ቤት ሲጠጣና ሲጫወት ያነሡትን የቪድዮ ምስል ለላሙዲ ባለሥልጣናት አሳይተዋቸው ነበር። የሳውዲ ባለሥልጣናቱም ቪድዮውን

ከተመለከቱ በኋላ፤ «ከዚህ ሌላ የምታሳዩን ነገር አላችሁ ወይ?» ብለው ጠይቀዋቸው፤ «የለንም» የሚል መልስ ሲሰጧቸው፤ «ይህንማ እኛም እናውቀዋለን፤ አዲስ ነገር አይደለም» ብለው መልሰዋቸዋል። ጉዳዩ እንዲህ ሲወሳ ቀላልና በአላሙዲ ብቻ ያነጣጠረ ይመስላል እንጂ መልእክቱ ግን ከባድ ነው። የአላሙዲ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያን መጥቀሙን ወይም አለመጥቀሙን ወደ ጎን ትተን ሻዕብያ እንዲህ ዓይነት ቀሽም ድራማ ያቀናጀው በኢትዮጵያ ከፍተኛ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት እንዳይኖርና ኢትዮጵያን ሊያበለጽግ የሚችል ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንዲገታ እንደነበር ግልጽ ነው።

የሻዕብያዎች ሜራ በዚህ አላበቃም። የኢሕአድግ እና የህግዴፍ የጋራ ኮሚቴ በሚገናኙበት ወቅትም ሻዕብያዎች ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪ በመምሰል የአላሙዲን ጉዳይ በተለያየ መልኩ ያቀርቡት ነበር። «ኢትዮጵያ ወዳጃችን ነች፤ አብረን ታግለን የመሠረትነው መንግሥት ችግር እንዲገጥመው አንፈልግም፤ የኢትዮጵያና የኤርትራ መንግሥታትም የተሰተካከለና የጠራ አኪያሄድ እንዲኖራቸው እንሻለን። ይህ ሂደት በማይረባ ነገር እንዲቀለበስም አንፈልግም። ይህን እንድንል ያነሣሣን ሥርዓቱ ውስጥ እየተከሰቱ ያሉ መጥፎ አዝማሚያዎች በተለይ እየተንሰራፋ ያለው ሙሰና እጅግ ስላሳሰበን ነው። ጉዳዩን በአመራር ደረጃ ተነጋግረንበት ሥጋታችንን ልንገልጽላችሁ ወስነናል። የሚያሳስቡንንም የሙሰና ችግሮች ለልኡካን ቡድኑ መሪ ለተወልደ ወልደ ማሪያም እንነግረዋለን» ብለውን ነበር።

በዚሁ መሠረት ለተወልደ ስለሙስና መንሰራፋት አብነት ሲሰጡት የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ በከፍተኛ ሙስና ውስጥ እንደተዘፈቀ፣ አላሙዲም በኢትዮጵያ የሙስና «ጋንግሪን» በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለው ነግረውት ነበር። ይህ የአላሙዲ የሙስና ጋንግሪን ጉዳይ ቃሉ ሳይለወጥ በመለስም ከስብሰባዎች ውጭ በተደጋጋሚ ይነገረን ነበር፤ መለስ «ሰውየው ባለሥልጣኖችን ማኖ በማስነካት በአገራችን ሙሰና እንዲንሰራፋ ኢያደረገ ስለሆነ የኢንቬስትመንት እንቅስቃሴው አሉታዊ ገጽታ አለው። ስለዚህ የምናደርገው ግንኙነቱ ገደብ ሊደረግበት ይገባል።» ሲል ይደመጥ ነበር። አንዳንዶቻችን የመለስ አገላለጽ ቃል በቃል የሻዕብያዎች የሚያስተጋባ ስለነበር ምናልባት ሻዕብያዎች በዚህ ጉዳይ ላይ አነጋገረውት አሳምነውት ይሆናል የሚል ጥርጣሬ ነበረን።

ከሻዕብያጋ በጋራ ኮሚቴ አባልነት በተመደብነው አብዛኛዎቻችን በኩል ስለአላሙዲ የነበረው አመለካከት ከመለስና ከሻዕብያዎች የተለየ ነበር። ማንኛውም መንግሥት በአገሩ ኢንቬስትመንት ለማስፋፋት በርካታ ዓለም ዐቀፍ ኩባንያዎችን ማስተናገድ ግድ ይለዋል። እንዲያውም በሙሰና የተካኑና ከፍተኛ ትርፍ የሚዝቁ ድንበር ዘለል (multi-national) ኩባንያዎችም ወደ አገራችን መምጣታቸው እንደማይቀር መንግሥት መቀበል እንዳለበት እናምን ነበር። ታድያ ኩባንያዎቹ አንድ በአንድ እያጠናን እነዚህ ኩባንያዎች የሙሰና ጋንግሪን ስለሚያስፋፉ በአገራችን መሥራት የለባቸውም፤ እነዚህ ደግሞ ከሙሰና ነጻ ስለሆኑ መሥራት ይችላሉ፤ ማለት እንደማንችል ግልጽ ነበር። እንዲህ ምርቱና ግርዱ ለመለየት ብንፈልግ እንኳን ይህን ለማድረግ ዓቅሙም ይሁን ብቃቱ የለንም። ከሞላ ጎደል ሁሉም ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ባለሥልጠኖችን መደለልና በሙሰና መቆጣጠር ከፖሊሲያቸው አንዱ ነው። እንዲያውም ባልበለጸጉ አገሮች የሚያደርጉት የኢንቬስትመንት እንቅስቃሴ ያለ ጉቦና ያለ መደለያ ስለማይሰምርላቸው ጉቦን «ስጦታ» በሚል ስያሜ የኩባንያዎቻቸው ይፋዊ መደበኛ ወጪ አድርገውታል። በዚህ አቅጣጫ የሚሠሩትን ኩባንያዎች አናስገባም ብንል ኢንቬስትመንትን ከማቀጨጭ ሌላ ምንም ፋይዳ የለውም። የአላሙዲን ኩባንያዎችም በዚህ መልክ ማየት አለብን እንጂ፤ የእርሱን በተለየ የምናይበት ሁኔታ ሊኖር አይገባም የሚል አስተያየት ነበረን።

ድንበር ዘለል ኩባንያዎችንና የሙስና እንቅስቃሴያቸውን ካነሣን ዘንዳ በወቅቱ ስለ ሙስና ስንል የነበረውን መግለጹ ተገቢ ነው። ሻዕብያዎችና መለስ አላሙዲ ሙስናን የሚያስፋፋ ጋንግሪን ነው ሲሉን እኛ ደግሞ ሰውየው እንደማንኛውም ጥቅመኛ ሙስናን ሊያስፋፋ ቢችልም እኛ በዋናነት መቆጣጠርና ማጽዳት ያለብን የመንግሥትንና የፓርቲን መዋቅሮች እንጂ ባለሀብቶችን መሆን የለበትም እንል ነበር። ባለሥልጣኖች ራሳቸው ለሙስና የተጋለጡ ከሆኑ ከአላሙዲ ብቻ ሳይሆን ከሌላም ባለሀብት ጉቦ መቀበላቸው አይቀርም። ሙሰኛ ባለሥልጣን በእጁ ያለውን የመንግሥትን መሬት፣ በጀትና ንብረት ሊዘርፍ ይችላል። ስለዚህ ዋና ትኩረታችን የመንግሥት ባለ ሥልጣናትን መቆጣጠርና ማጽዳት ላይ መሆን አለበት እንጂ የውጭም ይሁን የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ላይ መሆን የለበትም የሚል መከራከሪያ እናቀርብ ነበር።

ሌላው ሻዕብያዎች ያሳስበናል ያሉት የታምራት ላይኔ ሙስና ጉዳይ ነበር። በእርግጥ ሻዕብያዎች በሙስናው ገበያ በሰፊው ተሰማርተው ስለነበር የሚያመልጣቸው ነገር አልነበረም። ሆኖም የሻዕብያዎች የሙስና እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ ዐልፎ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ተስፋፍቷል በሚባልበት ሁኔታ የፀረ-ሙስና ትግል ተሟጋቾች ይሆናሉ የሚል እምነት አልነበረንም። ታምራትን በሙስና ሲከሱም መነሻቸው ፖለቲካዊ ሊሆን እንደሚችልም እንገምት ነበር። የሆነው ሆኖ የታምራትን ጉዳይ በይፋ አንስተውልን ስለነበር ጉዳዩን በወቅቱ የኢትዮጵያ ፕሬዚደንት ለነበረው መለስ ዜናዊ አቀረብነው።

መለስ የታምራት በሙስና መጠርጠር ስንነግረው ፈጥኖ አልተቀበለውም። ብዙዎቻችን በከተማ ይነፍስ የነበረው ወሬ ብንሰማም ገና በሚቱ የበላይ አመራሮች ያን ያህል በከፍተኛ ሙስና ሊዘፈቁ ይችላሉ የሚል ግምት አልነበረንም። የታምራት ላይኔና የሌሎች የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የሙስና ችግር በአብዛኛው ይነሣ የነበረው በብአዴኖች በራሳቸው ነበር። መጨረሻ ላይ የታምራትን ሙስና ለማጋለጥ በስፋት የተንቀሳቀሰው ግን አላሙዲ ነበር። አላሙዲ በአንድ ወቅት ለትግራይ መስተዳደር ስልክ ደውሎ ገብሩን ስዬንና ዓባይን ላገኛሁ እፈልጋለሁ ብሎ መቀሌ ድረስ በቻርተር አውሮፕላኑ መጣ።

በመስተዳደሩ ጽሕፈት ቤት ስናገኘውም፤ «ወደዚህ የመጣሁት፣ አገር አለማለሁ ብዬ ስሠራ ታምራት ላይኔ ስምንት ሚልዮን ዶላሬን ቀማኝ፣ ገንዘቡ እንዲመለስልኝ አቤት ለማለት ነው። ስለዚህ ኢሕአዴግ ይህን አቤቱታዬን ሰምቶ መፍትሔ እንዲሰጠኝ እርዱኝ» አለን። እኛም «ገንዘቡን ለምን ሰጠኸው? ገንዘቡ አሁን የት አለ? ገንዘቡን ለመስጠትህስ ምን ማስረጃ አለህ?» ብለን ስንጠይቀው፣ «ገንዘቡን የኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ምንዛሬ ችግር ስላጋጠመው ቡና ሽጠን የምንከፍልህ ስምንት ሚልዮን ዶላር አበድረን ስላለኝ አምኜ ሰጠሁት። ገንዘቡ ስዊስ ባንክ ውስጥ ተልኮ ገቢ ሆኗል። ለዚህም በስሙ ያስተላለፍኩበትን የባንክ ደረሰኝ ለማምጣት እችላለሁ» አለን:: እኛም ማስረጃውን እንዲያመጣ ተስማምተን ተለያየን። ከጥቂት ቀናት በኋላ ማስረጃውን በፋክስ ላከልን። ይህን ማስረጃም ይዘን ከኢሕአዴግ አመራር አባላት ጋራ ተነጋገርን። መለስ ታምራት ይህን አያደርግም የሚል አስተያየት ሲሰነዝር፣ አብዛኛዎቻችን ግን ክሱ እውነት ባይሆንም ማጣራቱ አይከፋም ብለን የደኅንነት ኃላፊው ክንፈ ገብረ መድኅን የተሰጠንን ማስረጃ እርግጠኝነት እንዲያጣራ ተደረገ።

የኢሕአዴግ አመራር በዚህ በአላሙዲ ክስ የተወሰነ ጥርጣሬ ያደረበት አላሙዲ ከማንኛውም የኢሕአዴግ አመራር አባል በላይ ከታምራት ጋራ የጠበቀ ጓደኝነት ስለነበረው ነው:: ኋላ ላይ ግን እኛ በማናውቀው ምክንያት መጣላታቸውን ሰማን። በመሆኑም አላሙዲ ታምራትን ለመጥለፍ ያደረገው ሤራ ሊሆን ይችላል የሚል ጥርጣሬ ነበረን። በበኩሌ አሁንም ቢሆን የዚህ ዓይነቱ ሕገ ወጥ የገንዘብ ልውውጥ በአንድ ጠቅላይ ሚኒስትርና

በአንድ ባለሀብት መካከል እንዴት ተኪያሂደ? ጥፋተኛውስ ታምራት ብቻ ነው ወይ? የሚል ጥርጣሬ አለኝ። የሆነው ሆኖ ክንፈ የሰነዱን ትክክለኛነት ካረጋገጠ በኋላ ጉዳዩ ለኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚና ለብአዴን አመራር ቀርቦ በታምራት ላይ ክስ ተመሠረተ። ምንም እንኳን የሻዕብያዎች ለኢትዮጵያ ሥርዓት መቆርቆር ቢያጠራጥርም ሻዕብያዎች የሰጡት ጥቆማ ትክክል ሆኖ በመገኘቱ ግዳይ እንደጣሉ ቆጠሩት።

16.6 የሻዕብያና የኢትዮጵያ ግንኙነት ይበልጥ መሻከር

ሻዕብያዎች በኤርትራ ጊዜያዊ መንግሥት ካቋቋሙ በኋላ የወሰዱት ኢትዮጵያውያንን በገፍ የማባረር እርምጃ ሥጋትና ጥላቻን ያዘለ እንደነበር ቀደም ብዬ በዚሁ ምዕራፍ ገልጬዋለሁ። ይህ ስሜታቸው ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን በቅኝ ገዥነት ከሚፈርጀውና በኢትዮጵያ የነበረውን ሥርዓት ከሕዝቡ ከማይለየው የፖለቲካ አቋማቸው የመነጨ ነበር። ቀደም ሲል በታሪክ ለደረሰባቸው ግፍና ችግር ሁሉ፣ ለኋላ ቀርነታቸውና ለኑሯቸው ቀውስ ኢትዮጵያውያንን በደፈናው ዋና ተጠያቂዎች ያደርጓቸው ነበር። ከኢትዮጵያውያንም በተለይ አማራንና ትግራዋይን በጠላትነት ይፈርጁ ነበር። አማራውን ሥልጣን ተጠቅሞ በኤርትራ ላይ ግፍ እንደፈጸመ ዋና ጠላት፣ ትግራዋዩንም በአማራው ቅኝ ግዛት ሥር እንዲወድቁ እንዳሜረ ተባባሪ ጠላት ያዩት ነበር። ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ ጋራ በፈዴሬሽን ለመወሐድ በሕዝብ ድምጽ ሲወስኑ ዋናዎቹ ተዋንያን ኤርትራውያን ሳይሆኑ ሠርገው የገቡ የትግራይ ተወላጆች ነበሩ ብለው ያምኑ ነበር። በእርግጥ ኤርትራ በእግሊዝ አስተዳደር ሥር ሳለች የኤርትራና የኢትዮጵያን መዋሐድ የሚደግፉ ኤርትራውያን ከትግራይ ተወላጆች ጋራ ይንቀሳቀሱ ነበር። ዐልፎ ዐልፎም ለሚያደርጉት የትጥቅ እንቅስቃሴ ትግራይን እንደደጀን ይጠቀሙባት ነበር። ሆኖም ወሳኙ የውሕደት ድምጽ የተገኘው ከኤርትራውያን ከራሳቸው በተለይም ከደገኞቹ ነበር። ኋላ ላይ ነገሮች ተበላሽተው ከአንድነት የተገኘ ፋይዳ የለም የሚል አቋም ላይ ደረሱ እንጂ የሠራዬ፣ የአካሉግዛይ፣ የሐማሴንና አንዳንድ የባርካ ተወላጆች በወቅቱ የነበራቸው አቋም «አንድነት ወይም ሞት» የሚል ነበር።

ሻዕብያዎች በኢትዮጵያውያን ላይ በተለይ ደግሞ በትግራይ ሕዝብ ላይ የጥላቻ ቅስቀሳ ከማካሂዳቸውም በላይ ያለፈ ታሪክን በመጥቀስ የትግራይ ሕዝብ ታሪካዊ ባላንጣቸው እንደሆነ ይገልጹ ነበር። ኤርትራን ያስተዳድሩ የነበሩት የአጼ ዮሐንስ ጀኔራል ራስ አሉላ ኤርትራዊውን ራስ ወልደ ሚኬኤልን አታለው እጃቸውን እንዲሰጡ ካደረጓቸው በኋላ ለእስርና ለግዞት እንደዳረጓቸው፣ ሌሎች ለነጻነት የቆሙ ኤርትራውያንም እንደፈጁ ይተርኩ ነበር። ይህን ሲሉ ዘመኑ የመሳፍንት እንደነበርና በመሳፍንቶች መካከል የግዛት ማስፋፋትና ማጠናከር ፉክክር እንደነበር የዘነጉት ይመስላል። ከአጼ ቴዎድሮስና ከአጼ ተክለ ጊዮርጊስ ቀጥሎ ኢትዮጵያን ለመግዛት የታሪክ አጋጣሚ ያገኙት የትግራይ ተወላጆች ኃይላቸውን አጠናክረው በኤርትራና በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል የነበሩትን መሳፍንት ለመቆጣጠርና ለማስገበር ከፍተኛ ጥረት እንዳደረጉ ታሪክ ይመሰክራል። በዚህ ሂደትም እንደነ ራስ ወልደ ሚኬኤል ያሉ ኤርትራውያን በቁጥጥር ሥር ውለው ለግዞት ተዳርገዋል። ወቅቱ አውሮፓውያን አፍሪካን ለመቀራመት እንቅስቃሴ ያደረጉበት ስለነበርም ኤርትራ ነጻነቷን ጠብቃ ልትቆም የምትችልበትና ከጣልያኖች ቅኝ ግዛት የምታመልጥበት ሁኔታ አልነበረም። እንዲያውም እነ ራስ አሉላ ኤርትራን ያካተተችውን ኢትዮጵያ ከጣልያኖች ወረራ ለማዳን ብዙ መሥዋዕትነት ከፍለዋል። በዚህም ይሁን በሌሎች ቅኝ ገዥዎችን የመመከት ታሪካዊ እንቅስቃሴዎችም በርካታ ኤርትራውያን አሳትፈዋል።

በህግዴፍና በኢሕአዴግ የተቋቋመው የጋራ ኮሚቴ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ኤርትራውያን በንግድና በኢንቬስትመንት ዘርፍ ያለ ምንም ገደብ እየተንቀሳቀሱ በኤርትራ የሚኖሩም ኢትዮጵያውያንም ይህን መብት ሊያገኙ ይገባል ብለው በተደጋጋሚ ቢጠይቁም ሻዕብያዎች በሰበብ ባስባብ ጥያቄውን ወደ ጎን ይገፉት ነበር። ሆኖም ጉዳዩ መሠረታዊ ስለነበር በሁለቱ ድርጅቶች መካከል የማያግባባ ነጥብ ሆኖ ቀጠለ።

ኢትዮጵያ የኤርትራ ወደቦችን በነጻ ልትገለገልባቸው ቀርቶ ገንዘብም ከፍላ በቀልጣፋ መንገድ ልትጠቀምባቸው አልቻለችም ነበር። እንዲያውም የምጽዋ ወደብ ለትግራይና ለሰሜን ጎንደር ቅርብ ስለነበር የነዚህን አካባቢዎችን ከኤርትራ ጋር የመወዳደር ዓቅም ለማቅጨጭ ከዓሰብ በተለየ መልኩ በምጽዋ ወደብ ከጠቅላላ ገቢ ሸቀጦች ዋጋ 1.5 ከመቶ ክፍያ ተጥሎ ነበር። ይህ በመሆኑም በወቅቱ ዓሰብ ከመቀሌ ከ800 ኪሎ ሜትር በላይ ስትርቅ፣ ምጽዋ ደግሞ ከመቀሌ 395 ኪሎ ሜትር ስትርቅ በምጽዋ ወደ መቀሌ ለሚገቡ ሸቀጦች ይከፈል የነበረው ቀረጥ ከፍ በመደረጉ በዓሰብ በኩል ከሚገባው ሸቀጥ ልዩነት አልነበረውም። ይህም ጉዳይ በኢሕአዴግ ልኡካን አማካይነት ለሻዕብያ ቀርቦ አጥጋቢ መልስ ሳያገኝ ቀርቶ የኤርትራን ወደቦች መጠቀም አስቸጋሪ ሆኖ ቀጠለ::

ሻዕብያዎች ኤርትራ በነበሩ በአገራቸው እድገትና ልማት ለመሳተፍ በሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ላይ ጥብቅ የስለላ ክትትል ያደርጉ ነበር። በተለይ እነዚህ ኢትዮጵያውያን የተሰባሰቡባቸው «የኢትዮጵያ ኮምዩኒቲ» እና የትልቁ ቅርንጫፎች ሻዕብያዎች የስለላ ድርጅቶች ይሆናሉ በሚል በሥጋትና በጥርጣሬ ያይዋቸው ነበር። በአንድ ወቅት ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋራ የአምባሳድር አውዓሎምን ባሕርይ አንሥተን ስናወራ፣ «እንደሌሎች በየመጠጥ ቤቱ የማይገኝ፣ ከመኖሪያ ቤቱና ከሥራ ቦታው ውጭ የትም የማይሄድ፣ ብቻውን በአንድ ትልቅ ቤት ተዘግቶ የሚቀመጥ ነው፣» ብለን ስንል፣ ኢሳያስ፤ «አውዓሎም የዋዛ እንዳይመስላችሁ ቤቱ ቁጭ ብሎ ሰላዮችን እያሰማራ እያንዳንዷን የኤርትራ እንቅስቃሴ ይከታተላል» ሲለን በከፍተኛ ደረጃ እየሰለላችሁን ነው ለማለት እንደፈለገ ገባን። በኢትዮጵያውያን ላይ ብርቱ ክትትል ያደርጉ የነበሩትም ከዚህ የተሳሳተ ግምታቸው ተነሥተው ሊሆን ይችላል::

እኔ እስከማውቀው ድረስ የኢሕአዴግ አመራር፣ በተለይ መለስ ዜናዊ፣ የሚቆጣጠረው አገራዊው የደኅንነት መዋቅር በኤርትራ ላይ ምንም ዓይነት ስለላ እንዳያኪያሂድ መመሪያ ተላልፎ እንደነበር ነው። ይህን ጉዳይ በኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚና ምክር ቤት ባንነጋገርበትም መለስ የሚመራው የደኅንነት ክፍል መመሪያው እንደተሰጠው የፌዴራል ደኅንነት አባላት የነበሩት ነግረውን ነበር። ለዚህ እግድ የተሰጠው ምክንያት በኤርትራ ላይ የስለላ መዋቅር ከዘረጋን ወደማይፈለግ ውዝግብ ልንገባ እንችላለን የሚል ሥጋት ነበር:: ኤርትራውያን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰላዮቻቸውንና የኮምዩኒቲ አባሎቻቸውን በኢትዮጵያ አሰማርተው ጓዳችንን ሲበረብሩ እኛ የተለየ ፖሊሲ መከተላችን ንዝህላልነትንና ለአገር ያለመቆርቆርን ያመለክት ነበር።

ሻዕብያዎች በኢትዮጵያ የኤርትራን ማኅበረሰብ እያደራጀን ነው በሚል ሽፋን ከፍተኛ የድርጅትና የስለላ መዋቅር ዘርግተው እንደነበር ጓላ ላይ የተገኙ ሰነዶች በግልጽ አረጋግጠዋል። ያም ሆኖም ኤርትራ ውስጥ ኢሕአዴግም ይሁን ህወሓት የፓርቲ አባላት እንዳይመለምሉና እንዳያደራጁ ተከልክለው፣ መደራጀት የሚቻለው በኮምዩኒቲና በልማት ማኅበር ብቻ እንደሆነ ተገልጾ ነበር:: ሻዕብያዎች ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራና ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ የሚደረገውን እንቅስቃሴ በየኬላው ባስቀመጧቸው የስለላና የኢሚግሬሽን ቡድኖች አማካይነት ይመዘግቡ ነበር፤ እጅግ የተጠናከረና አስቸጋሪ ቁጥጥርም ያደርጉ ነበር። ችግሩን እንዲያስወግዱ ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብላቸውም ለመስማት ዝግጁ

አልነበሩም። በአንጻሩ በኢትዮጵያ በኩል በተለይ መጀመሪያ ላይ የነበረው ፍተሻና ቁጥጥር ልል ሆኖ ቆይቶ ኋላ ላይ ግን እልህ የተሞላበት እሰጥ አገባ ውስጥ ተገብቶ ለሻዕብያ ዐጸፋ መስጠት ተጀምሮ ነበር። ከዚህ የተነሣም አለመግባባትና መካረር እየተባባሰ ሄደ።

17. የኢትዮጵያና የኤርትራ ግንኙነት በጦርነቱ ዋዜማ

17.1 የህወሓት/ኢሕአዴግ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መዳከም

ህወሓት በ1985 ዓ.ም· ከፍተኛ ግምገማ ካካሂደ በኋላ ውስጣዊ እንቅስቃሴው እየቀዘቀዘ ሄደ። ግምገማው የበላይ አመራር አባላትን ሳይነካ መካከለኛና ዝቅተኛ አባላት ላይ ማተኮሩና አመራሩ ራሱን በሚገባ ሳይፈትሽ የታችኛውን አባል መምታቱ ፍትሐዊ አይደለም የሚሉ አባላት ተበራክተው ነበር። በወቅቱ በአመራር ደረጃ የነበረው ችግር በአግባቡ ያለመምራት እንጂ የሥነ-ምግባር ችግርም ነው ብለን አላስቀመጥንም ነበር። በዚህ የግምገማ አካሂያሄድና በአመራሩ አቋም የተከፉ በርካታ ታጋዮች ድርጅቱ ከእንግዲህ አብቅቶለታል፤ አመራሩ የታገልንለትን ዓላማ ትቶ የራሱ ኑሮ በማመቻቸትና ጥቅሙን በማስጠበቅ ላይ አተኩሯል፣ ፍትሕ መረጋገጥ ተስኖታል የሚለውን አመለካከታቸውን እያጠናከሩ ሄዱ። ይህ በታጋዩና በአመራሩ መካከል የተፈጠረው መራራቅ ድርጅቱን ሕይወት ካለው የፖለቲካ እንቅስቃሴ አርቆ በአፈጻጸምና በአሠራር እርምትና ቁጥጥር ወደሚያተኩር እንቅስቃሴ ለውጦታል።

ህወሓት መዳከም ጎልቶ የወጣው በ1985 ዓ.ም· በተደረገው ሰፊ ድርጅታዊ ግምገማ ቢሆንም ድርጅቱ ቀደም ብሎም ቆሞላቸው የነበሩትን መሠረታዊ ዓላማዎችና መርሖዎች ትቷል የሚል አስተያየት ይሰነዘር እንደነበር ከላይ ገልጨዋለሁ። ድርጅቱን በአመለካከት እንዲዳከም ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ሲከተለው የነበረውን ማርክሲስት ርዕዮተ ዓለም እርግፍ አድርጎ ትቶ በምትኩ የጠራና የነጠረ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ አቅጣጫ ሊከተል አለመቻሉ ነበር። ድርጅቱ በአንድ በኩል ማሌሊት ሲያራምደው የነበረውን ማርክሲስት ርዕዮተ ዓለም ትቶ የማሌሊት ዱካ እንኳ እንዳይገኝ እየተንቀሳቀሰ በሌላ በኩል ደግሞ ፍጹም ሊተገበር የማይችለውን በካፒታሊዝም የሚመራ አብዮታዊ ዴሞክራሲ አራምዳለሁ ማለቱ አባላቱን በአጠቃላይ ውዥንብር ውስጥ ከቷቸው እንደነበር ቀደም ብዬ አብራርቻለሁ።

ህወሓት/ኢሕአዴግ ውስጥ የተከሰተው የርዕዮተ ዓለምና የፖለቲካ አመለካከት ችግር በአባላቱ ብቻ ሳይሆን በአመራሩም ደረጃ መንጸባረቁ አልቀረም። ሚቹ ገብረ መስቀል ኃይሉ በተደጋጋሚ ያነሣው ለነበረው ድርጅቱ ወዴት ወዴት እያመራ ነው? ለሚለው ጥያቄ እኔም መልስ አልነበረኝም። አብዮታዊ ዴሞክራሲ ያለ ማርክሲያዊ ሌኒናዊ ፓርቲ አመራር እውን እንደማይሆን፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በላብ አደሩ መሪነትና በአርሶ አደሩ አጋርነት ብቻ ተግባራዊ እንደሚሆን፣ ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገው ጉዞ ያለማቋረጥ በሚደረግ አብዮታዊ ሽግግር እንጂ በካፒታሊዝም ግንባታ እንደማይረጋገጥ፣ ለሚያውቀው ሁሉ አዲሱ አካሂያሄድ ውዥንብር ውስጥ እንደሚያስገባው ጥርጣሬ የለውም። እንደ ገብረ መስቀል በተከታታይነት አይሁን እንጂ አንዳንድ የህወሓት አመራር አባላትም ተመሳሳይ ጥያቄ ማንሣታችን አልቀረም። በጉዳዩ ተወያይተን አጥጋቢ መልስ ስላልተገኘበት በድርጅቱ የተከሰተው የአመለካከት ውዥንብር እየተባባሰ ሄደ።

ገብረ መስቀል ዓይነተኛ አብዮታዊ ስለነበር ከደርግ ውድቀት በኋላ ስንከተለው በነበረው የፖለቲካ አቅጣጫ ፍጹም ደስተኛ ካለመሆኑም ባሻገር የግል ሕይወቱን ከእምነቱ ጋራ

አጣጥሞ ለመምራት ተቸግሮ ነበር። ገብረ መስቀል ትግራይ ውስጥ በዓዲ አሕፈሮም በሚገኘው በስምዕጭ ዘላ ጎጥ ተወልዶ ከአጎቱ ጋራ ለመማር በልጅነቱ ወደ ወልድያ ተልከ ከነ ሼክ አላሙዲጋ ቢማርም ገና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለ የአሜሪካ የነጻ ትምህርት ዕድል አግኝቶ ወደ አሜሪካ ሲያቀና ሼኽ አላሙዲ ደግሞ ወደ ሳውዲ ዓረብያ አመራ። አላሙዲ በልጽጎ ቢልዮኔር ሲሆን ገብረ መስቀል ትምህርቱን እርግፍ አድርጎ ትቶ ታጋይ ሆነ። ሁለቱ አብሮ አደጎች ለብዙ ዓመታት ተለያይተው በደርግ ውድቀት ማግስት አዲስ አበባ ላይ ተገናኙ። አላሙዲና ገብረ መስቀል ልጅነታቸውን እያስታወሱ ለብቻቸው ሲያወጉ፣ አላሙዲ ገብረ መስቀልን «ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?» ብሎ ይጠይቀዋል። ገብረ መስቀልም ገንዘብ፣ ቪላ፣ መኪና ወይም ሌላ ጥቅም አልጠየቀም። «እኔ የምፈልገው በአገራችን ኢንቨስትመንት እንድታሰፋፋ ነው፤» አለው።

አላሙዲ በገብረ መስቀል መልስ ተገርሞ «ይሽንጋማ አንተ ባትለኝም አደርገዋለሁ። እየጠየኩሽ ያለሁት በግል የማደርግልሽን ነው» ሲለው ገብረ መስቀልም ምንም እንደማይፈልግ ገለጸለት። ከጊዜ በኋላ አንድ የወልድያ ልጅ ሲያገባ ሠርግ ላይ ተገኝንተው አላሙዲ ለወዳጆቹ ስጦታ ሲያበረክት ለገብረ መስቀልም አንድ ሳምሶናይት ሻንጣ ይሰጠዋል። ገብረ መስቀል ሳምሶናይቱን ሳይከፍተው ቤቱ ከደረሰ በኋላ ሲያየው አንድ መቶ ሺሕ ብርና የተለያዩ የውጭ አገር የገንዘብ ኖቶችን የያዘ ሆኖ ያገኘዋል። ገብረ መስቀል ይህን ገንዘብ ሲያገኝ ብዙም ሳይደሰት፣ ኻያ ሺውን ከአዲስ አበባ ትግራይ እስከሚደርስ ለሚያውቃቸው ለተቸገሩት ሁሉ ሁለት ሁለት ሺሕ ብር እያደለ ሄደ። ቀሪውን ገንዘብ ደግሞ ለኢሕአዴግ ጽሕፈት ቤት አስረከበ። ገንዘቡ ከየት እንዳገኘው ሲጠየቅም ታሪኩን ተናገረ። ገብረ መስቀል ይህን ያደረገው በቂ ገንዘብ ስለነበረው ሳይሆን ሲታገልም ይሁን ከዚያ በኋላ የሚከተለው ርዕዮተ ዓለም በግሉ ለመበልጽግ ስለማይፈቅድለት ነበር። በርካታ የህወሓት/ኢሕአዴግ ባለሥልጣኖች ቪላ ቤቶችን እያማረጡ እርስ በእርስ ሲፎካከሩና ዘመናዊ መኪና ለመያዝ ሲሽቀዳደሙ፣ ገብረ መስቀል በስጦታ የተሰጠውን ገንዘብ ለድርጅቱ ሰጥቷል። የብዙዎቹ የድርጅት አባላት ሀብት ለማካበት መሯሯጥና በዝርፊያ መሰማራት ህወሓት/ኢሕአዴግ ያጋጠመውን የአስተሳሰብ ውሽንብር ያመለክት ነበር። ገብረ መስቀል በአንዳንድ ታጋዮች ዘንድ እንደ «ጉዱ ካሳ» ተደርጎ እየታየ ያነሣቸው የነበሩት ጥያቄዎች ጊዜ እንዳለፈባቸውና እውነታውን እንደማያንጸባርቁ ታይተው ይጣጣሉ ነበር። ሆኖም ጥያቄዎቹ የገብረ መስቀል ብቻ ሳይሆኑ የበርካታ ታጋዮችም ነበሩ።

በ1988 ዓ.ም. የዓድዋ መቶኛ ዓመት ሲከበር የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ የድርጅቱን እንቅስቃሴዎች ለመገምገምና አዳዲስ ዕቅዶችን ለማውጣት ስብሰባ አካሂደዱ ነበር። በዚህ ስብሰባ ከተነሡት ጉዳዮች አንዱ የሴቶችን እንቅስቃሴ መዳከምና ይህን ለማስተካከል መደረግ ስላለባቸው እንቅስቃሴዎች ነበር። በዚህ አጋጣሚ ገብረ መስቀል የሴቶች እንቅስቃሴ ለምን ተዳከመ? የሚል ጥያቄ አንሥቶ ችግር ሰሩ አድርገን እንየው፣ ችግሩ የአሠራር፣ የአመራር፣ የአደረጃጀት፣ ወዘተ... ሳይሆን ከመሠረታዊ የአስተሳሰብ መዛባት የሚመነጭ ነው ይል ነበር። ችግሩ በፊት ስናራምደው የነበረውን የግራ ፖለቲካ እርግፍ አድርገን ስንተወው የወንዶች ትምክሕትና የበላይነት በከፍተኛ ደረጃ ማቆጥቆጡ ነው ይልም ነበር። ታድያ ለገብረ መስቀል የተሰጠው መልስ «አንተ ጥያቄውን የምታነሣበትን አቅጣጫ በሌላ ጊዜ እንነጋገርበት፣ አሁን ባለው ማዕቀፍ ችግሩ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንሞክር» የሚል ነበር። ገብረ መስቀልም ከቅን አስተሳሰብ በመነሣት ጉዳዩ ሌላ ጊዜ ይነሣል ብሎ ጥያቄውን ለጊዜው ወደ ጎን ተወው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የሴቶች እንቅስቃሴ ለመቀዝቀዙ ምክንያት ይሆናሉ የተባሉ ችግሮች ተዘርዝረው ዋነኛው ችግር የሴቶቹ ማኅበር አመራር ድክመት ነው ተባለ። ይህ ችግር

በሁሉም የሥራ መስኮች የተሰማሩ ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን ቢመለከትም ዋና ለጊዜው ዓላማ የሆነው የሴቶቹ አመራር ነበር። መለስና አንዳንድ የድርጅቱ የአመራር አባላት የሴቶችን ማኅበር አመራር በመለወጥ ለማኅበሩ ሕይወት እንሰጠዋለን ሲሉም በስብሰባው የነበርነው የአመራር አባላት በሙሉ የመፍትሔው ፍቱንነት ቢያጠራጥረንም እነ መለስ ባቀረቡት ሐሳብ ተስማማን። ኋላ ላይ የህወሓት ሥራ አስፈጻሚ ስብሰባ ሲኪያሄድ ይህ የማኅበሩን አመራር የማስተካከሉ ውሳኔ ምን ማለት ነው? ሁሉን የሴቶች አመራር አባላት ጠራርገን በአዲስ ከተካናቸው ችግር አይፈጠርም ወይ? በማኅበሩ አብዛኞዎቹን የአመራር አባላት አዳስ አድርገን ነባሮቹንም ብናካትት አይሻልም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችና ሐሳቦች ቀረቡ። ለዚህ የተሰጠው መልስ ግን በማኅበሩ ለረጅም ጊዜ የቆዩትን የአመራር አባላት ተክተን ጥቂት ዓመታት የሠሩትን እንዲቆዩ ልናደርግ እንችላለን የሚል ነበር። ከነጭራሹም ማኅበሩ ሲቋቋም የነበሩት «ኦሮጌ ደም» የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸው አሮጌ ደምን ካስወገድን ማኅበሩ ሕይወት ሊዘራ ይችላል ተባለ። በዚህም ሐሳብ ፖሊትቢሮው ተስማምቶበት የሴቶች ማኅበር አመራር መለወጡ ተግባራዊ ሆነ።

ከላይ የተገለጸውን በተመለከተ ቢያንስ ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎችን ማንሣት ይቻላል። አንደኛው ፖሊት ቢሮው የሴቶቹን ማኅበር ድርጅታዊ ነጻነት ረግጦ በሚፈልገው መንገድ ለማስተካከል መወሰኑ ማኅበሩ ነጻ ህልውና የሌለው መሆኑንና ነጻ ህልውን ስላጣም ሕይወት ለመዝራት እንደማይችል አለመገንዘባችን ነው። ሁለተኛው ችግር ደግሞ በአመራር ውስጥ ለረጅም ጊዜ መቆየት የሚፈጥረው መዳከም የሴቶች አመራርን ብቻ ሳይሆን ማዕከላዊ ኮሚቴውንና ፖሊትቢሮውንም እንደሚመለከት አለመገንዘባችን ነው። በህወሓት አመራር ውስጥ ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ፣ ለኻያ አንድ ዓመታት የማዕካላዊ ኮሚቴ አባላት የሆኑና ከ1971 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ፣ ለአስራ ሰባት ዓመታት የአመራር አባላት ሆነን የቆየን ጥቂት አልነበርንም። ይህ ሆኖ ሳለ አሮጌውን ደም የማስወገዱ ሴቶች ማኅበር ላይ ብቻ ማነጣጠሩ አኪያሄዳችንን አጠያያቂ አድርጎት ነበር።

አሁን መለስ ብዬ ሳየው ይህ ውሳኔ በ1980 ዓ.ም. በተኪያሄደው የሴቶች ኮንፈረንስ ፌሚኒስት ተብለው በአመራሩ የተመቱትን በተለይ ደግሞ በመለስ ጥርስ የገቡትን ሴት የአመራር አባላት ለመጥረግና በምትካቸው ታማኞችን ለመተካት የተወጠነ ነበር። ውሳኔው ያነጣጠረው በእነ አረጋሽ አዳነ፣ የውብማር አስፋው፣ ሮማን ገብረ ሥላሴና መብራት በየነ ላይ ነበር። ውሳኔው ዴሞክራሲያዊ መርሕን የተጻረረ ከመሆኑም ባሻገር በማኅበሩ ግልጽ ጣልቃ ገብነት መደረጉ ለጊዜው መፍትሔ ተደረጎ ቢወሰድም የህወሓት አመራር በብዙ ነባር ታጋይ ሴቶች ዘንድ ታማኝነት እንዲያጣ አድርጎታል። በ1985 ዓ.ም. የተደረገው አጠቃላይ የድርጅቱ ግምገማ ኢፍትሐዊነት አብዛኛውን ታጋይ እንዳቆሰለ ሁሉ በ1988 ዓ.ም. የተኪያሄደው የሴቶች ሁለተኛ ጉባኤም በሴቶች ማኅበር የታቀፉትን ነባር ሴት አባላት ልብ አቁስሏል። የተፈጠረው ስሜትና ቅሬታም በእነእርሱ ብቻ ሳይወሰን እነእርሱን ያምኑና ይከተሉ በነበሩትም ሁሉ ተንጸባርቋል።

በወቅቱ የህወሓት/ኢሕአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ በሚያኪያሂዳቸው ስብሰባዎች ብቻ ሳይሆን በጉባኤዎችም የአመለካከት ጥራት ችግር ይከሰት ነበር። በደርግ ውድቀት ማግስት የተደረጉ የድርጅት ጉባኤዎች የሞቀ የሐሳብ ፍጭት ያልተደረገባቸው በአሠራርና በአፈጻጸም ላይ ያተኮሩ ነበሩ። በተለምዶ ጉባኤ ተብለው ቢሰየሙም አገሪቱንና ሕዝቡን ወደ ፊት የሚያራምዱና አንገብጋቢና መሠረታዊ ጥያቄዎች የሚነሡባቸው አልነበሩም። ለምሳሌ የአገራችንን ደኅንነትና ጸጥታ በአስተማማኝ መንገድ ለማስጠበቅ ምን ዓይነት አቅጣጫ መከተል አለብን? የአገራችን የቅርብና የሩቅ ጠለቶች እነማን ናቸው? እነዚህንስ እንዴት መከላከል ይቻላል? የባሕር በር ባለቤት አለመሆናችን የሚፈጥርብን ሳንካ ምንድን ነው? የባሕር በር ባለቤት ለመሆን ምን ማድረግ አለብን? በተለይ ወሰን ተሻጋሪ በሆኑ ወንዞቻችን

ላይ ያለን ሉዓላዊነት እስከምን ድረስ ነው? እነዚህን ወንዞች ድህነትና ረሀብ ለመቀነስ ልንጠቀምባው እንችላለን ወይ? የአገራችን የኢንዱስትሪ እድገት እንዴት ሊፋጠን ይችላል? ፖሊሲያችን ምን መምሰል አለበት? ዓለም ዓቀፍ ተቋማት በእድገታችን ላይ የሚያደርሱትን ተጽዕኖ እንዴት ልንቋቋመው እንችላለን? የአገራችን የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ምን ይመስላል? የምንከተለው የፓርቲና የመንግሥት አደረጃጀት እውን ዴሞክራሲን ሊያረጋግጥ የሚችል ነው ወይ? ነጻ ፍርድ ቤቶች፣ ነጻ የሲቪል ማኅበረሰብ፣ ነጻ ዓቃቤ ሕግ፣ አንዱ ሌላውን ሊቆጣጠር የሚችልበት የመንግሥት ተቋም፣ በሌሉበት ዴሞክራሲንና መልካም አስተዳደርን ማስፈን ይቻላል ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች በጉባኤዎቹ አልተነሡም ነበር። በጉባኤዎቹ ግንዛቤ ያላገኙ ጉዳዮች ደግሞ በማዕከላዊ ኮሚቴውና በሥራ አስፈጻሚው ትኩረት ያገኛሉ ብሎ ማሰብ ዘበት ነው።

ከመብትና ዴሞክራሲ አንጻር በወቅቱ በነበርኩበት በትግራይ መስተዳድር ላይ የሚነሡ በርካታ ጥያቄዎች ነበሩ። ከነዚህ ጥያቄዎች አንዱ መስተዳድሩ የግል ጋዜጦችን እንቅስቃሴ ይከለክላል የሚል ሲሆን ጉዳዩ ከአጠቃላዩ አገራዊው ሁኔታ ተለይቶ የሚታይበት ሁኔታ ነበር። በሕግ ደረጃ ነጻ ፕሬስና ነጻ ሲቪል ማኅበረሰብ ቢፈቀዱም ኢሕአዴግ ከሚከተለው ወገናዊ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮተ ዓለምና ፖለቲካ አንጻር እየተመዘኑ እንደጠላት በሚፈረጁት ላይ ከፍተኛ ጫናና ወከባ ይደርስባቸው ነበር። ኢሕአዴግ አመለካከት እውነተኛ የመረጃ ምንጮች «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» እና «ወይን»፣ አዲስ ዘመንና ኢትዮጵያን ሄራልድ፣ ሬድዮ ፋና፣ ድምጺ ወያነ፣ የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥንን የመሳሰሉት የፓርቲና ልሳኖች ነበሩ።

ከነዚህ ውጭ የነበሩት የሚድያ ተቋማት እንደጠላት ወይም በጠላትና በወዳጅ መኻል እንደሚዋዥቁ ይታዩ ነበር። የድርጅቱ እምነት ይህ ሆኖ እያለ በሕገ መንግሥቱ የሰፈሩ የግል ሚድያ እንዲቋቋም የሚፈቅዱ ድንጋጌዎች ስለነበሩ በበርካታ አሳሪ የሕግ አንቀጾች ተተብትበው የግል ፕሬስ እንዲቋቋም ተፈቅዶ ነበር። የግል ፕሬሶች በሕግ ቢቋቋሙም አጠቃላይ የፖለቲካ ምኅዳሩ ግን ለእነርሱ ምቹ ስላልነበር ብዙዎቹ ጫናውን መሸከም አቅቷቸው ይከስሙ ነበር። በኢሕአዴግ አመራርና አባላት አመለካከትም ይህ አኪያሄድ ጠላትን ለማቸነፍ የሚደረግ የመደብ ትግል አካልና የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የበላይነት ግረጋገጫ አንዱ የትግል አቅጣጫ ነበር። የትግራይ መስተዳድርም ይሁን እኔ በግሌ ስንከተለው የነበረው አቅጣጫ ይኸው ነበር። ምናልባት ትግራይ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ቤዝ ዐምባና የህወሓት መሠረት ስለነበር ጫናው እዚያ ይበረታ ነበር ይባል እንደሆነ እንጂ የተለየ መመሪያና አቅጣጫ ኖሮን በግል ፕሬሱና በሚድያው ላይ የከፈትነው ጦርነት አልነበረም። በግል ፕሬሱና ሚድያ ሲኪያሄድ የነበረውና አሁንም እየተኪያሄደ ያለው ጦርነት ኢሕአዴግ ዐቀፍና አገር ዐቀፍ ባሕርይ ያለው ነው። ለነገሩ ብዙ ዲፕሎማቶችና የውጭ ዜጎች ባሉባት አዲስ አበባ ጫናው ደከም ያለ ነበር ካልተባለ በስተቀር አስተሳሰቡና መመሪያው ግን ከአንድ የእዝ ማዕከልና ምንጭ የሚቀዳ ነበር። አሁን ሳጤነው በአብዮታዊ ዴሞክራሲ እምነታችን ምክንያት የመረጃ ፍሰትን ገድበን የአገራችንን የአስተሳሰብ እድገት በመሳተታችንና በማጫጨታችን እጸጸታለሁ።

ሌላው የትግራይ መስተዳደር ላይ የሚነሣው ጥያቄ መስተዳድሩ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን አያስተናግድም እንዲያውም በክልሉ ዝር የሚል ተቃዋሚ የለም የሚለው ነበር። እንደ ግል ፕሬሱ መገደብ ሁሉ ይኸም ከፍ ብዬ ከገለጽኩት አብዮታዊ ዴሞክራሲ እምነታችን የመነጨ ነበር። ኢሕአዴግ ተቃዋሚዎቹ እንዲከስሙ ያደርጋል እንጂ ከነአርሱ የተሻሻ አስተሳሰብ ስላለኝ በአስተሳሰቤ የበላይነት አሸንፋለሁ የሚል እምነት አልነበረውምም አሁንም የለውም። በመሆኑም ተቃዋሚዎቹን ለማቸነፍ በዴሞክራሲያዊ መርሕ ላይ ያልተመሠረቱ የተለያዩ አግባቦችን በመጠቀም ለመዘረር ይሞከር ነበር። ይህ አኪያሄድ በሁሉም የአገሪቱ

ክፍሎች ቢሠራበትም ይህን ለማድረግ የተሻለ ዓቅም በነበረበት በትግራይ ጠንከር ያለ ነበር። ኢሕአዴግ ተቃዋሚዎችን ለመድፈቅና ለማጥፋት ከሚጠቀምባቸው ስልቶች ጥቂቶቹን ለመግለጽ ያክል፤ 1ኛ/ በደጎንነቶች አማካይነት በእያንዳንዱ የተቃዋሚ አመራርና አባል ላይ ጥናት በማኪያሄድ ለመግዛትና ድርጅቱን ለመከፋፈል መሞከር፣ 2ኛ/ ተቃዋሚው ድርጅት በጎብረተሰቡ እንዲጠላና እንደጠላትነት እንዲታይ እንደየ ሁኔታውና እንደየ አካባቢው ነፍጠኛ ነው፤ ትምክሕተኛ ነው፤ ጠባብ ነው፤ ጎሰኛ ነው፤ መላው አማራ ነው፤ ኢዴጎ ነው፤ አነግ ነው፤ የደርግ ቅሪት ነው፤ በማለት ማጥላላት፣ 3ኛ/ ተቃዋሚዎችን በወንጀል እየከሰሱ ማጉላላት፣ ማሰቃየት፣ ማሰርና እንዲሰደዱ ማድረግ፣ 4ኛ/ የተቃዋሚው ድርጅት አባላት ከማኅበረሰቡ እንዲገለሉ ለማድረግ ጎረቤቶቻቸውን ጭምር በመቀስቀስ ለቅሶ እንዳይደረሱ፣ በሰርግና በተዝካር፣ በደቦና በሌላ የትብብር ሥራ እንዳይገኙ ማድረግ፣ 5ኛ/ የመንግሥት ድጋፍ ማለትም የምግብ እርዳታ፣ ብድር፣ ማዳበሪያ፣ ወዘተ... እንዳያገኙ ማድረግ፣ ነበሩ።

የተጠቀሱት ተቃዋሚዎችን የማዳከምና የማጥፋት ስልቶች በመላ አገሪቱ በሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ድርጅቶችና አባሎቻቸው ላይ ይፈጸሙ ነበር። እነዚህ ተቃዋሚን የማጥፋት ስልቶች የግድ ከአመራሩ መመሪያ እየተሰጠና ዕቅድ እየወጣ የሚተገበሩ ሳይሆኑ በየደረጃው ያለው ካድሬ ከድርጅቱ አስተሳሰብና አጠቃላይ አቅጣጫ ተነሥቶ ሥራ ላይ የሚያውላቸው ነበሩ። ዐልፎ ዐልፎ ከመርሕ በመነሣት ሳይሆን እነዚህ ስልቶች ከውጭ ለጋሽ መንግሥታት ጥያቄ ሊያስነሡ ይችላሉ ከሚል ከላይ ለመከልከል ቢሞከርም አባሉና ካድሬው የህልውናውና የሥጋት ምንጭ አድርጎ ያያቸው ስለነበር በራሱ ውሳኔ ስልቶቹን ተግባራዊ ያደርጋቸው ነበር። እዚህ ላይ ችግሩን በታችኛው አባልና ካድሬ ለመላከክ ብዬ ሳይሆን ዋናው የችግሩ ምንጭና ተጠያቂው የበላይ አመራሩና የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እምነት ሆኖ የስልቶቹ አፈጻጸም ግን መዋቅራዊ ሰንሰለት ያልተከተለ እንደነበር ለማመልከት ነው።

ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማዳከም እንጠቀምባቸው ከነበሩት ስልቶች አንድ ሁለቱን ዘርዘር ባለ መልኩ ብናያቸው ጠቃሚ ይመስለኛል። ትግራይ ውስጥ ይንቀሳቀሱ ከነበሩት ተቃዋሚዎች የተሻለ ማኅበራዊ መሠረት የነበረውና ህወሓትን ሊቀናቀን ይችል የነበረው ኢዴጎ ነበር። ድርጅቱም በሰላማዊና ሕጋዊ አግባብ ትግሉን ለመቀጠል ወስኖ የሽግግሩ መንግሥት ካቋቋሙት ድርጅቶች አንዱ ነበር። የኢዴጎ ዋና መሠረት ትግራይና ሰሜን ጎንደር በመሆኑም ኢዴጎ ከመጀመሪያው ምርጫ ጀምሮ በእነዚህ አካባቢዎች ህወሓት/ኢሕአዴግን ለመፎካከር ሲሞክር ብዙ ችግሮች አጋጥመውታል። ቀደም ሲል እንደገለጽኩት ኢዴጎ ከ1967 እስከ 1970 ዓ.ም. ከህወሓት ጋር ጦርነት ገጥሞ ስለነበር ኢሕአዴግ በጦርነቱ የፈጸመውን ጥፋት መሠረት በማድረግ በጎብረተሰቡ ተቀባይነት እንዳያገኝ ከፍተኛ ቅስቀሳ ያኪያሂድ ነበር። ድርጅቱ በትጥቅ ትግሉ ጊዜ በርካታ አርሶ አደሮችን እንደጨፈጨፈ፣ በውንብድናና በዝርፊያ ብዙ ንብረት እንዳወደመ፣ ወዘተ... ከመግለጽ ዐልፎ እያንዳንዱን አባል በወንጀል ማኖ ለማስነካትና በሕግ ለማስጠየቅም ሞክሯል። ጊዜውን በትክክል ባላስታውሰውም በዓዲግራት ለምክር ቤት ይወዳደር በነበረው የኢዴጎ አባል ላይ መስተዳድሩና የጸጥታ አባላት የሽረቡትን ተንኮል መጥቀስ ይቻላል። አንድ የደጎንነት አባል ሆን ብሎ የኮንትሮባንድ ነጋዴ መስሎ ካላሽኒኮቭ ጠመንጃ በርካሽ ዋጋ እንዲገዛው ይጠይቀዋል። የጠመንጃው ዝቅተኛ ዋጋ ያጓጓው የኢዴጎ አባል ጠመንጃውን ለመግዛት ይስማማና አንድ ቦታ ይቀጣጠራሉ። በቀጠሮው ሰዓት ጠመንጃውን ይዘው የተገኙት ግን የኮንትሮባንድ ነጋዴዎች ሳይሆኑ በደጎንነት አባላቱ የተላኩ ሰዎች ነበሩ። ሰውየው ከሻጮቹ እጅ ጠመንጃውን ሲረከብ አስቀድመው አድፍጠው የተዘጋጁ

የጸጥታ አባላት እጅ ከፈንጅ ይይዙትና ለምክር ቤት ሊወዳደር የተዘጋጀው ሰው መጨረሻው እስር ቤት ሆነ።

ሌላው መብራህቱ ጌጤ የሚባል የኢዴጎ አባልና የዶግዓ ተምቤን ተወላጅ በመቀሌ በድርጅቱ ጽሕፈት ቤት ተወካዮች አንዱ ነበር። ሰውዬው በገጠር ከሚኖሩ የኢዴጎ አባላትጋ እየተገናኘ መዋቅሩን በማስፋት ረገድ ጠንክሮ ይሠራ ነበር። ይህን የተገነዘቡ የህወሓት ካድሬዎችና የጸጥታ ሰዎችም የሰውየውን ያለፈ ታሪክ ሲያጠኑ በአንድ ወቅት በነፍስ ግድያ ወንጀል ተጠርጥሮ እንደነበር ፍንጭ ያገኛሉ። በዚህ ተጠቅመውም መብራህቱ ገድሎታል የተባለውን ሰው ቤተሰቦች ክስ እንዲመሠርቱበት ያደርጓቸዋል። የሟቹ ቤተሰቦች በመሠረቱት ክስ ምክንያትም መብራህቱ ጌጤ ወህኒ ይወርዳል፤ የኢዴጎ ጠንካራ ተቃውሞም ይገታል። ይህን ተግባር የፈጸሙትን ማብራሪያ እንዲሰጡኝ ስጠይቃቸው መብራህቱ ወንጀሉን በትክክል እንደፈጸመና እንዲሁ እነርሱ የለጠፉበት የፈጠራ ክስ እንዳልሆነ ነግሩኝ። ሰውየው በማይሆን ክስ ታስሮ ሊሆን ይችላል የሚል ጥርጣሬ ቢኖረኝም ጉዳዩ ምስክሮች ቀርበውበት እየተጣራ ስለነበር ጣልቃ ለመግባት አልፈለኩም። ለማንኛውም ወንጀሉ ለዓመታት ሳይነሣ ቆይቶ በምርጫው ወቅት መነሣቱ ከጀርባው አንድ ደባ እንዳለ ያጠራጥራል። ያኔ በኢዴጎና በሌሎች ተቃዋሚዎች ከነበረን አመለካከት አንጻር ግን፤ ነገሩ የፈጠራ ቢሆንም እምብዛም ተግቼ የምከታተለው የነበረ አይመስለኝም።

ሌላው ተቃዋሚዎችን ለማዳከም የሚደረገው እንቅስቃሴ የአመራር አባላቱንና ከፍተኛ ኃላፊዎችን መቆጣጠር ነበር። በዚህ ረገድም በትግራይ የነበሩ የኢዴጎ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች በየጊዜው በህወሓት ይገዙ እንደነበር አውቃለሁ። ለክብራቸው ስል ስማቸውን መግለጹ ተገቢ ባይሆንም ሁለት የማውቃቸው የኢዴጎ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች ገንዘብ እየተሰጣቸው ምስጢር በማቀበልና ዕቅዶችን በማኮላሸት ይሳተፉ ነበር። ከዚህ የተነሣም ኢዴጎ በአካባቢው ያደርግ የነበረው እንቅስቃሴ ተዳክሞ። ትግራይ ከነበረው ዓቅም አንጻር ቁጥጥሩና አፈጻጸሙ ይጠብቅ እንደሆነ እንጂ፤ ይህ የኢሕአዴግ አሠራር በሌሎች ክልሎችም ተግባራዊ ነበር። ከኢዴጎ አባላት ሌላ በክፍያ መዝገብ ስማቸው የሰፈረ አሁን ድረስ ተቃዋሚዎች ነን እያሉ የሚንቀሳቀሱ የማውቃቸው አሉ። የነዚህን ሰዎች ተቀጣሪነት ያወቅኹት በኢሕአዴግ አመራር አባልነቴ ሳይሆን ቅርበት ከነበረኝ የደኅንነት አባላት ነውና አሁንም የነዚህን የማውቃቸውን ሰዎች ስም ላለመጥቀስ መርጫለሁ።

ህወሓት/ኢሕአዴግ በዐፍላ ዘመኑ ይመካበት የነበረውን የአስተሳሰቡ የበላይነትና ተቃዋሚን በአስተሳሰብ የበላይነት ላቸንፍ እችላለሁ የሚለውን አቋሙን ትቶ የአስተሳሰብ ድኽነት ካጋጠመው በኋላ ትኩረቱ ሁሉ አስተዳዳራዊና ጸጥታዊ ቁጥጥርን ማጥበቅ ላይ ሆኗል። እመራዋለሁ፣ ቆሜለታለሁ የሚለው ሕዝብ ሳይቀር ይህን የኢሕአዴግ ዝቅጠት ሳያስተውለው አልቀረም፤ ባይሆንማ ሕዝቡ «ሳም እሳት ወለደች፤ እንዳትልሰው አቃጠላት፤ እንዳትተወው ልጅ ሆነባት» የሚለውን አባባል ባላነሣ ነበር::

በአጠቃላይ የህወሓት/ኢሕአዴግ ሥርዓት የቆመው በተምታታና በተጭበረበረ አስተሳሰብ ላይ እንጂ በጠራና ወጥ በሆኑ አስተሳሰብ ላይ ባለመሆኑ የዓለማ አንድነትና ጽናት፣ ተነሳሻነትና ልበ ሙሉነት ጠፍቶ ወደፊት መራመዱ ቀርቶ ባለበት የረጋበት፣ እንዲያውም ወደ ኋላ የተጎተተበት ሁኔታ ሊፈጠር ችሏል። ድርጅቱ በትጥቅ ትግሉ ዘመን የነበረው ሕዝብ የማንቀሳቀስ ዓቅም እንኳ ተመናምኖ ሥልጣኑን የሙጥኝ በሚል አባዜ ተጠምዷል። ይህ ድክመቱና ለዓላማው ትኩረት አለመስጠቱም ከውስጥና ከውጭ ሊገጥመው የሚችለውን ችግር በሐሳብ የበላይነት እንዳይቋቋም እያደረገው ነው።